# ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

## ወደ ፡ ጐጃም ፡ ስለ ፡ መግባት ።

ከጥቂት ፡ ቀን ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ አቸፈር ፡ ከተባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ስንደርስ ፡ ጠላት ፡ ያልታሰበ ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ ጣለብን ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የደረሰብን ፤ የአደጋው ፡ ወሬ ፡ ምንም ፡ ደስ ፡ ባያሰኝና ፡ አሰቃቂም ፡ ቢሆን ፡ ሳላወጋው ፡ ላልፍ ፡ አልፈቅድምና ፡ ባጭሩ ፡ ልገልጸው ፡ እወዳለሁ ።

ዳንግላ ፡ የነበረ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ አዛዥ ፡ ኰሎኔል ፡ ቶሬሊ ፡ የሚባለው ፡ ከነጦሩ ፡ ከዳንግላ ፡ አቸፈር ፡ ዝብስት ፡ ከተባለው ፡ ቀበሌ ፡ የገባን ፡ ዕለት ፡ ጠዋቱን ፡ ደርሶ ፡ ኖሮ ፡ አገሩንና ፡ መንገዱን ፡ በማናውቀው ፡



ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ መኰንን ፡ (ቢትወደድ) ።

በኛ ፡ ላይ ፡ በድንገት ፡ ደርሶ ፡ ሊይዘን ፡ አስቦ ፡ ነበር ። የአቸፈር ፡ አርበኛ ፡ መሪ ፡ የሆኑ ፡ ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ መኰንን ፡ በመጀመሪያ ፡ መጥተው ፡ ጳግሜ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተገናኝተን ፡ ስንነጋገር ፡ የጠላት ፡ አይሮፕላን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይመላለስ ፡ ጀመረ ። ምክንያቱንም ፡ ብንጠይቃቸው ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ የአይሮፕላን ፡ ማንዣበብ ፡ የሚታየው ፡ እስ



ካሁን ፡ ባጠናነው ፡ ጦር ፡ ከኋላው ፡ ባስከተለ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ አሁን ለማረጋገጥ ፡ ወዳፋፍ ፡ ሰው ፡ ልኬያለሁና ፡ መልክተኛው ፡ እስኪመለስ ፡ ምሳችሁን ፡ እኔ ፡ ቤት ፡ ተጋበዙልኝ ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁን ። በምሳ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ መኰንን ፡ ቤት ፡ ሄደን ፡ በሩን ፡ ገባ ፡ ስንል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መጣና ፡ ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ ጦር ፡ መጣ ፡ ስለተባለ ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ ሄዱ ፡ ብሎ ፡ ነገረን ፤ ወዲያው ፡ የአርበኞች ፡ መሰብሰቢያ ፡ የጥሩምባ ፡ ድምፅ ፡ በየበኩሉ ፡ ይሰማ ፡ ጀመረ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለምሳ ፡ የተጠራነው ፡ ሰዎች ፡ ያ ፡ ቀበሌ ፡ ሽብር ፡ ስለሆነ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከበራፉ ፡ ላይ ፡ ሳንገባ ፡ ወደሰፈራችን ፡ ተመለስንና ፡ ጓዛችንን ፡ አንስተን ፡ ለመሄድ ፡ ስናስብ ፡ በማናውቀው ፡ መንገድና ፡ አገር ፡ ወዴት ፡ እንሂድ ፡ የጠላትስ ፡ ጦር ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ የመጣው ፤ ማንን ፡ እንጠይቅ ፤ ዝም ፡ ብለን ፡ እንዳንቀመጥ ፡ ይደርስብን ፡ ይሆናል ፤ እንዳንሄድ ፡ እሱ ፡ ላይ ፡ እንወድቅ ፡ ይሆን ፤ እያልን ፡ ብናስብም ፡ መጨነቅን ፡ ብቻ ፡ አትርፈን ፡ ቆመን ፡ ሳለ ፤ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የየራሱን ፡ ጓዝ ፡ ቦታ ፡ ካስያዘ ፡ በኋላ ፡ ከፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ ዘንድ ፡ ተልከናል ፡ ብለው ፡ ቀኛዝማች ፡ ተገኝ ፡ ብሩና ፡ አቶ ፡ ልሳነወርቅ ፡ የሚባሉ ፡ አርበኞች ፡ መጡና ፡ መንገድ ፡ ሊመሩን ፡ መታዘዛቸውን ፡ ነገሩን፤ ጠምአድሮ ፡ ጠም ፡ የዋለ ፡ ሰውነት ፡ ከላይ ፡ ዝናብ ፡ ከታች ፡ ጭቃና ፡ ቆንጥሩ ፡ አላላውስ ፡ አለን ፤

ሐሳብ ፡ እንዳንሰጥ ፡ አገሩ ፡ አይታወቅም ፤ ሆኖም ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ሌሊት ፡ አለመኃዙን ፡ ስለአወቀን ፡ አረፍ ፡ ብሎ ፡ በማለዳ ፡ መሄድ ፡ የተሻለ ፡ መሆኑ ፡ ተመረጠና ፡ በዚያች ፡ ቦታ ፡ አርፈን ፡ በሥጋት ፡ ላይያለውን ፡ ሌሊት ፡ እንደምንም ፡ አሳለፍነው ። ወገግ ፡ ሲል ፡ ከሌሊቱ ፡ ጭምር ከነበርንበት ፡ ሥፍራ ፡ አንድ ፡ እርከን ፡ ወረድንና ፡ በበረሃው ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ለአይሮፕላን ፡ ተገን ፡ ለማድረግ ፡ ሄድን ፤ ከዋሻውም ፡ ደርሰን ፡ ዕቃ ፡ ማራገፍና ፡ ማግባት ፡ ስንጀምር ፡ ጦሩ ፡ ዘልቋል ። ለጠላት ፡ ጦር ፡ መሪ ፡ ሆነው ፡ የመጡትም ፡ ይህን ፡ መደበቂያ ፡ ሁሉ ፡ አጥርተው ፡ የሚያውቁ ፡ አርበኞች ፡ የነበሩ ፡ የፊታውራሪ ፡ ዘለቀ ፡ ሊቁ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ቢሆንም ፡ የጦሩን ፡ አመጣጥና ፡ አመራር ፡ አጥርቶ ፡ መረዳት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለነበረ ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ የተሰጠንን ፡ ሰው ፡ አፋፍ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ሁኔታውን ፡ አይቶ ፡ እንዲመጣ ፡ ስንልከው ፡ ተመልሶ ፡ እስኪመጣና ፡ እስኪነግረን ፡ ጦሩ ፡ የማያዳርሰው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የተኩስ ፡ ምልክት ፡ እንዲያደርግ ፡ ነግረነው ፡ ሄዶ ፡ ነበር ። መላክተኛውም ፡ እስኪመለስ ፡ ጦሩ ፡ የማያዳርስው ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝቦ ፡ ኖሮ ፡ ተቃርቧልና ፡ አምልጡ ፡ ለማለት ፡ የሚያሻውን ፡ የተኩስ ፡ ርችት ፡ አሰማን ፤

## አቸፈር ፡ ዝብስት ፡ ላይ ፡ ጠላት ፡ አደጋ ፡ እንደጣለብን ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ያልታሰበ ፡ ድንገተኛ ፡ ነገር ፡ ገጠመን ፤ ይኸውም ፡ ጦር ፡ መጣላችሁ ፡ አምልጡ ፡ አሉን ። መሪያችን ፡ የለም ፡ መንገዱን ፡ አናውቀው ፡ ወዴት ፡ ብንሄድ ፡ ነው ፡ ከጠላት ፡ የምናመልጠው ፡ አልታወቀም ፤ መጨነቅ ፡ ብቻ ፡ ሆነ ። ሆኖም ፡ በየት ፡ በኩል ፡ እንደምንሄድ ፡ አቅጣጫውን ፡ ብቻ ፡ ከመሪያችን ፡ ጋራ ፡ ሳለን ፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ ተነጋግረን ፡ ነበርና ፡ ያን ፡ አቅጣጫ ፡ ይዞ ፡ መሄድ ፡ የተሻለ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ በማለት ፡ አሰብንና ፡ መጓዝ ፡ ስንጀምር ፡ ለጠላት ፡ ምቹ ፡ በሆነ ፡ ገላጣ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ደረስን ፤

ጠላትም ፡ የሚፈልገውን ፡ በግላጭ ፡ አገኘና ፡ በእጅ ፡ ቦንብና ፡ በመትረየሱ ፡ ከሩቅም ፡ በመድፍ ፡ እያሻገረ ፡ መድረሻ ፡ መራመጃ ፡ አሳጣን ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በግራም ፡ ሆነ ፡ በቀኝ ፡ ያለው ፡ መንገድ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሆነብን ። ስለዚህም ፡ ዓይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ ወደፊት ፡ ከመሄድ ፡ በስተቀር ፡ ወደኋላ ፡ መመለስን ፡ ሳናስብ ፡ ስንሄድ ፡ መንገድ ፡ በሌለበት ፡ እልም ፡ ካለው ፡ ጫካና ፡ ገደል ፡ ደረስን ፤ ምን ፡ ይደረግ ፡ ከጠላት ፡ እጅ ፡ ለማምለጥ ፡ ብቻ ፡ የቻልነውን ፡ ያህል ፡ አደረግንና ፡ ገደሉን ፡ በመንከባለልም ፡ ሆነ ፡ በመንፏቀቅ ፡ አለፍንና ፡ ከረባዳው ፡ መሬት ፡ ስንደርስ ፡ ጊዜው ፡ ዝናም ፡ ነበርና ፡ መሬቱ ፡ ጭቃ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የሄድንበትን ፡ መንገድ ፡ ጠላት ፡ ተከታትሎ ፡ በፈለጋችን ፡ እንዳይደርስብን ፡ አሰበን ፤ በስተፊታችንም ፡ አንድ ፡ ወንዝ ፡ አገኘንና ፡ በወንዙ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በመጓዝ ፡ ፈለጋችንን ፡ ማጥፋት ፡ ይሻላል ፡ በማለት ፡ መከርንና ፡ ወንዝ ፡ ለወንዝ ፡ ሁለት ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ያኸል ፡ ሄድን ። በኋላ ፡ ከውሀው ፡ ውስጥ ፡ ወጥተን ፡ አንድ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ አረፍ ፡ አልንና ፡ እንደገና ፡ ለመጓዝ ፡ ስናስብ ፡ ብርድ ፡ ረሀብ ፡ በውሀ ፡ ውስጥ ፡ የተዘፈዘፈ ፡ ጫማ ፡ እንደምን ፡ አድርጎ ፡ ያስኪያድ ፡ ሁሉም ፡ ችግር ፡ ሆነና ፡ ቆመን ፡ ስናመነታ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ከተለየነው ፡ መሪያችን ፡ ተገናኘን ።

ወዲያው ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ሆነን ፡ ጥቂት ፡ እንደተጓዝን ፡ ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ የሀገሩ ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑ ፡ የተኩስ ፡ ድምፅ ፡ ሰምተው ፡ ለእርዳታ ፡ የመጡ ፡ አምስት ፡ ሽፍቶች ፡ አገኘንና ፡ ስናነጋግራቸው ፡ የነበረን ፡ ተስፋ ፡ በአምስት ፡ ሺህ ፡ ወታደር ፡ ውስጥ ፡ እንዳለን ፡ ያህል ፡ የሚገመት ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ ጠላት ፡ በዚህ ፡ ሥፍራ ፡ አይደርስም ፡ ቢደርስም ፡ ለመቼም ፡ ቢሆን ፡ ሊደርስ ፡ በማይችልበት ፡ መዘዋወሪያ ፡ ሥፍራ ፡ እያዘዋወርን ፡ ወደ ፡ ታሰበው ፡ ቦታ ፡ እናደርሳችኋለን ፡ እያሉ ፡ በልበ ፡ ሙሉነት ፡ ያለምንም ፡ ሥጋት ፡ ያነጋግሩን ፡ ስለነበረ ፡ ነው ። እኛም ፡ የሰዎቹን ፡ ቆራጥነት ፡ ተመልክተንና ፡ የነገሩንን ፡ ሁሉ ፡ በቶሎ ፡ አመንና ፡ የኛም ፡ ልብ ፡ ሙሉ ፡ ሆነ ። ከጓዛችን ፡ ከተለያየን ፡ ከ፫ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡



መላክተኛ ፡ አስቀደምንና ፡ ብንከተል ፡ ጠላት ፡ እኛን ፡ ፈልጎ ፡ አጥቶ ፡ እዚያ ፡ የደረሰበትን ፡ አገር ፡ መንደር ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ አቃጥሎ ፡ መመለሱን ፡ ሰማን ። ወደዚያውም ፡ ተከታትለን ፡ ስንደርስ ፡ ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ የተቃጠለውን ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ ግድግዳ ፡ አቁመው ፡ ጣራውም ፡ ግድግዳውም ፡ ሣር ፡ ለብሶ ፡ ደረስንና ፡ ጠላት ፡ ያስጣለንን ፡ ምሣ ፡ በዚሁ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተጋበዝን ።

## ጉታ ፡ ላይ ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀንበሬና ፡ ከሌሎችም ፡ አርበኞች ፡ ጋራ ፡ እንደተገናኘን ።

ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ጉዞዋችን ፡ ምን ፡ እንደሚሻል ፡ ስንነጋገር ፡ ከፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ የተሰጠን ፡ ምክር ፡ አሁኑኑ ፡ ተነስተን ፡ ወደፊታችን ፡ መጓዝ ፡ ግድ ፡ ያስፈልገናል ፡ የሚል ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ጠላት ፡ የተመለሰው ፡ አባርሬ ፡ ቈረጡን ፡ አሳልፈ..ያቸው ፡ መጣሁ ፡ እያለ ፡ ነውና ፡ ሳያስበው ፡ አሁን ፡ ካላለፍን ፡ በኋላ ፡ የመመለሳችሁን ፡ ወሬ ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ያስቸግረናል ፡ ሲሉ ፡ ገለጹልን ። እኛም ፡ ድካማችንን ፡ ሳናስብ ፡ ምክራቸውን ፡ ተቀበልንና ፡ ወዲያውኑ ፡ ተነስተን ፡ ጉዞ ፡ ቀጠልን ፡



ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ።

ጠላት ፡ ጠዋት ፡ በለቀቀው ፡ ሰፈር ፡ እኛ ፡ ማታ ፡ እንደደረስን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ዳንግላ ፡ ገብቶ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ እኛንም ፡ ወደ ፡ መጣንበት ፡ ወደ ፡ ሙተማ ፡ አባሮ ፡ መመለሱን ፡ የምሥራች ፡ አድርጎ ፡ ሲሰ

ብክ ፤ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ዓባይን ፡ ተሻግረን ፡ ጉታ ፡ ከተባለ ፡ ቀበሌ ፡ ከታወቁት ፡ የአርበኞች ፡ መሪ ፡ ከነበሩት ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ ተገናኝተን ፡ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ አስነበብን ። የአዋጁም ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በምዕራፍ ፡ ፲፭ ፡ ተጽፎ የሚገኘው ፡ ነው ፤ ከአዋጁ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ የምሥራች ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ መትረየስና ፡ የጠመንጃ ፡ የግባት ፡ ተኩስ ፡ ተተኰሰ ፤

ኰሎኔል ፡ ቶሬሊ ፡ እሱ ፡ ቋራን ፡ አሳልፌ ፡ መተማ ፡ አድርሼ ፡ መጣሁ ፡ እያለ ፡ ሲፎክር ፡ እኛ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ ከአርበኞች ፡ መሪዎች ፡ ጋራ ፡ ተገናኝተን ፡ ግባት ፡ ያስተኰስነው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በመሆኑ ፡ አሳፈርነውና ፡ ወዲያው ፡ ጠሩን ፡ አስከትቶ ፡ መጣና ፡ አቸፈርን ፡ በሙሉ ፡ አቃጠለው ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከሆነው ፡ ነገር ፡ የማልዘለው ፡ አንድ ፡ ታሪክ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ ያንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ንግግር ፡ ነው ፤ አስቀድሚ ፡ ከጻፍኳቸው ፡ ዕለታት ፡ ባንደኛው ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ጠላት ፡ ሰፍሮበት ፡ በለቀቀው ፡ አገር ፡ ከአንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ባላገር ፡ ቤት ፡ ደረስን ። ሽማግሌውም ፡ ባላገር ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እያለ ፡ ሲያስተናብር ፡ ፈታውራሪ ፡ እያሌው ፡ መኰንንያን ፡ ባላገር ፡ ስሙን ፡ ጠርተው ፡ አንተ ፡ ባንዳ ፡ እዚህ ፡ እኛን ፡ ያስተናገድህ ፡ እየመሰልክ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ዘንድ ፡ መላክተኛ ፡ ልከህ ፡ ይሆናል ፤ እመንገድ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ያገኘን ፡ እንደሆን ፡ ተመልሼ ፡ ነው ፡ የምለበልብህ ፡ አሉት ። ያም ፡ ሽማግሌ ፡ ባላገር ፡ ቀበል ፡ አድርጎ ፡ የመለብለቡ ፡ ነገር ፡ ከሁላታችሁም ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ነው ፡ የንፃነት ፡ ባንዲራ ፡ መመለሱን ፡ ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነት ፡ ያድርገው ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ። ይህም ፡ የሚያሳየው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ የባላገር ፡ ጉዳት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንደነበረ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጉታ ፡ በተባለ ፡ ቀበሌ ፡ ገበርማ ፡ ከምትባል ፡ ሥፍራ ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ቆሞ ፡ ኰሚቴዎቹም ፡ ቤት ፡ ሠርተው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤታቸውን ፡ በዚያው ፡ አቁቋመው ፡ ከአርበኞች ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ እየተላላኩ ፡ በማጽናናት ፡ በስብከትም ፡ እየረዱ ፡ ሲሠሩ ፡ አገኘንና ፡ እኛም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሠፈራችንን ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ አደረግን ፤ በዚያም ፡ ቦታ ፡ የተገኙት ፡ የኰሚቴ ፡ አባሎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

፩ ፤ አቶ ፡ ጊላ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (ባሬ ፡ ደጃዝማች) ፡
፪ ፤ ካፒቴን ፡ ከበደ ፡ ወልደ ፡ ሰማያት ፡
፫ ፤ አቶ ፡ ገብሬ ፡ መታፈሪያ ፡
፬ ፤ ልጅ ፡ ይገባሐል ፡
፭ ፤ አቶ ፤ አዳነ ፡ ነበሩ ።



በዚህም ፡ በተባለው ፡ ሥፍራ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ዕረፍት ፡ አደረግንና ፡ ሥራ ፡ በምንጀምርበት ፡ ጊዜ ፡ ከሰራቅ ፡ ወዲህ ፡ ተቋርጦ ፡ የነበረው ፡ ሐሳብ ፡ እንደገና ፡ እንግሊዛዊው ፡ ኰሎኔል ፡ ዘንድ ፡ ተንቀሳቀሰና ፡ አሁንም ፡ የሥራ ፡ ኃደኝነት ፡ ለቆ ፡ የበላይነትን ፡ የሚያሳይ ፡ ፕላን ፡ ሠርተው ፡ አቀረቡ ። በፕላኑ ፡ አናት ፡ ላይ ፡ የኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ሥልጣን ፡ ሆነና ፡ ለአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ዝቅ ፡ ያለች ፡ አንድ ፡ ቅርንጫፍ ፡ አመሩለትና ፡ ሥራው ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ሌሎቹን ፡ ሰዎች ፡ በሙሉ ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ ደለደሉና ፡ በቀጥታ ፡ የኰሎኔሉ ፡ ታዛዦች ፡ እንዲሆኑ ፡ አደረጉ ፤ እንድንስማማበት ፡ ፕላኑን ፡ ይዘው ፡ ቀርበው ፡ አነጋገሩኝ ፤ ፕላኑንም ፡ እያሳዩ ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ እንግዲህ ፡ የፕሮፓጋንዳ ፡ ሠራተኛ ፡ ነህ ፡ እንጂ ፡ በሚሰጠው ፡ የገንዘብና ፡ የመሣሪያ ፡ እርዳታ ፡ ውስጥ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሀብት ፡ ስለሆነ ፡ ያንተ ፡ ምክርና ፡ ሐሳብ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ፡ አሉ ። አብረው ፡ የነበሩትንም ፡ ሠራተኞች ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ የሚሠሩ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ የኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድን ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ተቀባይ ፡ እንዲሆኑ ፡ በፕላኑ ፡ ላይ ፡ ተመልክቷል ። በቃልም ፡ አስረዱኝ ፡ እኔም ፡ በትዕግሥት ፡ ካዳመጥኳቸው ፡ በኋላ ፡ እንደሚከተለው ፡ መለስኩላቸው ። የነገሩኝን ፡ ነገር ፡ ሰማሁ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ በገንዘብና ፡ በመሣሪያ ፡ እኛ ፡ ሕዝቡን ፡ ስናባብል ፡ አንተ ፡ በደረቁ ፡ ስበክ ፡ ነው ፡ የምትሉኝ ፤ ሐሳቡ ፡ በጣም ፡ ገብቶኛል ፡ ብዬ ፡ መልስ ፡ በሰጠኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ ምስጢሩ ፡ እንደታወቀባቸው ፡ ገባቸውና ፡ በማፈርና ፡ በመቅበጥበጥ ፤ ያለገንዘብ ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ አድርግ ፡ ማለቴ ፡ ሳይሆን ፡ ሐምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ላንተ ፡ በተለይ ፡ እንዲሰጥ ፡ አድርጌአለሁ ፤ እያሉ ፡ ይቀባጥሩ ፡ ጀመር ። ለጊዜው ፡ እኛ ፡ የምንረዳበት ፡ አጥተን ፡ ብድር ፡ ስንፈልግ ፡ ላንተ ፡ ሃምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ እሰጣለሁ ፡ ማለታቸውን ፡ የማምን ፡ አድርገው ፡ በመገመታቸው ፡ በጣም ፡ ተገረምኩ ፡ ልጣላቸውና ፡ ላጠቃቸው ፡ ስችል ፡ በገዛ ፡ አረሟ ፡ እባብ ፡ ይዛ ፡ ታስፈራራለች ፡ የሚሉትን ፡ የአባቶች ፡ ምሳሌ ፡ አስብኩና ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይም ፡ የተጣለብኝን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደራ ፡ በማሰብ ፡ ጭምር ፡ ነገሩን ፡ ቸል ፡ አልሁና ፡ እሺ ፡ ገንዘቡ ፡ ሲመጣ ፡ ይሰጡኛል ፤ ሠራተኞቼን ፡ ከወሰዷቸው ፡ ራሴ ፡ መሥራት ፡ ስላለብኝ ፡ ወረቀት ፡ ቀለም ፡ ቢሰጡኝ ፡ አመሰግናለሁ ፡ ስል ፡ በአቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ አስተርጓሚነት ፡ ነገርኋቸው ።

ከዚህ ፡ ንግግር ፡ በኋላ ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማና ፡ አቶ ፡ አሰጋኸኝ ፡ አርአያ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጡና ፡ እኛ ፡ እኰ ፡ የኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድን ፡ ቃል ፡ ሰምተን ፡ ወደዚህ ፡ መቅረባችን ፡ እንግሊዞችን ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ ጉዞዋችሁ ፡ ላይ ፡ እንዳታስቀይሟቸው ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ከግርማዊነታ

ቸው ፡ የተቀበልነውን ፡ ትእዛዝ ፡ በማክበርና ፡ በመጠበቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እንዳሁኑ ፡ ንግግር ፡ የመለያየት ፡ ሐሳብ ፡ ያለበት ፡ ከሆነ ፡ ከነሱ ፡ ተለዩ ፡ ቢሉን ፡ የምንለይ ፡ ነንና ፡ ሐሳብዎን ፡ ገልጠው ፡ ይንገሩን ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁኝ ፤ እኔም ፡ ለጥያቄያቸው ፡ መልስ ፤ እዚያው ፡ ሆናችሁ ፡ ቁም ፡ ነገራችሁን ፡ ሳትለቁ ፡ ሥራችሁን ፡ እየሠራችሁ ፡ በፍሬው ፡ ነገር ፡ እንገናኝ ፡ እንጂ ፡ ሥራችሁን ፡ ለቃችሁ ፡ መምጣት ፡ አያስፈልግም ፡ ስል ፡ አስጠነቀቅኋቸው ።



አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ።

እኔም ፡ በዚያው ፡ ቀበሌ ፡ በሀገሩ ፡ ባህል ፡ ሥራዩን ፡ በመቀጠል ፡ ወደ ፡ አርበኞች ፡ መላላክን ፡ በጀመርኩ ፡ ጊዜ ፡ ባሠራር ፡ ቅድሚያ ፡ አገኘሁ ። ከአርበኞች ፡ መሪዎች ፡ ጋራ ፡ ስጻጻፍ ፡ የነበረውንም ፡ ወደፊት ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ እገልጻለሁ ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የምጽፈው ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ስለተፈጸሙት ፡ ሥራዎች ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተላከውን ፡ ማስታወሻና ፡ የሥራ ፡ መግለጫ ፡ ራፖር ፡ ነው ።



ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

መድኃኒ ፡ ዓለም ፡ ጤና ፡ እስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኩ ፡ ባሪያዎ ፡ የረገጡትን ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ።

በጐጃም ፡ ወረዳ ፡ እንደተመለከትኩት ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ረቂቅ ፡ ጽፈን ፡ በቀለም ፡ ተገልብጦ ፡ እኔ ፡ እስክፈርምበት ፡ የሚያስቸኩል ፡ ሥራ ፡ ተገኝቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ስለሄድኩ ፤ በዝርዝር ፡ የጻፋትን ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ ፈርሞበት ፡ ከዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋራ ፡ እንዲልከው ፡ አድርጌአለሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የተጻፉት ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ መልሳቸው ፡ በቶሎ ፡ እንዲመጡልን ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አሳስባለሁ ።

መስከረም ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
ያለሀኬት ፡ ባሪያዎ ፡
ከበደ ፡ ተሰማ ፤

## ማመልከቻ ።

ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤

ከግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ እንደታዘዝኩት ፡ ሁሉ ፡ ሰራቆ ፡ ላይ ፡ እንደደረስን ፡ በየመንገዱ ፡ ያየሁትንና ፡ የሰማሁትን ፡ ለሥራም ፡ ጠቃሚ ፡ የመሰለኝን ፡ ሁሉ ፡ ዘርዝሬ ፡ የጻፍኩትን ፡ ማመልከቻ ፡ ይዞ ፡ የሄደ ፡ መልክተኛ ፡ በደህና ፡ መድረሱን ፡ በራዲዮ ፡ እንደተገኘ ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ነግረውኛልና ፤ ማመልከቻው ፡ እግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ደርሶ ፡ ሥራ ፡ ተሠርቶበታል ፡ ስል ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

ከሠራቆ ፡ በኋላ ፡ ያለውን ፡ የጉዞዎቻችንን ፡ አኳኋንና ፡ ለሥራም ፡ የሚያስፈልግ ፡ የመሰለኝን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እጽፋለሁ ፤

ስለ ፡ አደጋ ፡ ስጋት ፡ በበረሃ ፡ ስለሆነ ፡ የተጓዝነው ፡ በአሥራ ፡ አንድ ፡ ቀናችን ፡ በጳጉሜ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አቸፈር ፡ ውስጥ ፡ ዝብስት ፡ የምትባለው ፡ አገር ፡ ከፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ ግዛት ፡ ደረስን ፡ ከሰራቆ ፡ እስከ ፡ ዝብስት ፡ የሰፈርንባቸው ፡ ሥፍራዎች ፡ ስም ፡ ስማቸው ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ተሸንፋ ፡ ወንዝ ፤ ኳኳ ፡ ባኩሊት ፤ ወምበሪት ፡ ማርያም ፡ ወምበሬ ፤ ጋጅጌ ፤ ብራዊ ፡ ሸመለጃዊ ፡ ወይም ፡ በለስ ፡ ወንዝ ፤ ፍረሐ ፡ ቢዘራና ፡ ዝብስት ፡ ናቸው ።

ሸንፋና ፡ በለስ ፡ የሚባሉትን ፡ ወንዞች ፡ ድልድይ ፡ ሠርተን ፡ ተሻግረናቸው ፡ እስከ ፡ ዝብስት ፡ ድረስ ፡ ያየነው ፡ አገር ፡ እልፎ ፡ እልፎ ፡ የባህር ፡ ማሽላ ፡ ይገኝበታል ፡ እንጂ ፡ የእህል ፡ ሌላ ፡ ዘር ፡ በጭራሽ ፡ የለውም ፤ ከሰራቆ ፡ ስንነሳ ፡ የ፳ ፡ አጋሰሶች ፡ ጭነት ፡ ጓዝ ፡ ይዘን ፡ ተነሳን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በበረሃው ፡ ከብቱ ፡ እየደከመና ፡ እየሞተ ፡ ስለተቀነሰ ፡ ባንዳንድ ፡ አጠገባቸው ፡ በሰፈርንባቸው ፡ መንደሮች ፡ ጓዝ ፡ እየተውን ፡ የአሥር ፡ አጋሰሶች ፡ ጭነት ፡ ጓዝ ፡ ብቻ ፡ ይዘን ፡ ዝብስት ፡ ለመድረስ ፡ ቻልን ፤

አደጋ ፡ የማያሰጋ ፡ ቢሆን ፡ ኑሮ ፡ በአለፋ ፡ በኩል ፡ የአራት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ነበር ፤

ዝብስት ፡ ስንደርስ ፡ ለጊዜው ፡ ፊታውራሪ ፡ አያሌውን ፡ አላገኘናቸውም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ቀደም ፡ አድርገን ፡ ከባኩሊት ፡ አቶ ፡ አሰጋኸኝን ፡ ልከነው ፡ ስለነበረ ፡ እነበሩበት ፡ እሥሩ ፡ ደብር ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ስለጠራቸው ፡ በግስጋሴ ፡ መጥተው ፡ ጠዋት ፡ በማግሥቱ ፡ ጳግሜ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ተገናኘን ፤ የኛን ፡ ወደ ፡ ዝብስት ፡ መምጣትና ፡ የፊታውራሪ ፡ አያሌውን ፡ ባገር ፡ አለመኖር ፡ ጠላት ፡ ሰምቶ ፡ ኑሮ ፡ ከዳንግላና ፡ ከአለፋ ፡ ከሁለት ፡ ፊት ፡ ጦር ፡ አስከትቶ ፡ አደጋ ፡ ሊጥልብን ፡ ሲመጣ ፡ የ፫ና ፡ ፬ ፡ ሰዓት ፡ መንገድ ፡ ሲቀረው ፡ ወሬው ፡ ስለተሰማ ፡ ለኛና ፡ ለዕቃችን ፡ ስወር ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ አድርገውልን ፡ ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ ጦሩ ፡ ወዳለበት ፡ ቦታ ፡ ሄዱ ፤ ለጊዜው ፡ የጦሩ ፡ አመጣጥ ፡ የተሰማው ፡ በድንገት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በግምባር ፡ ገጥመው ፡ ሊዋጉት ፡ አልቻሉም ፡ ነበርና ፤ ዘወር ፡ ብለው ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ያዙ ፡ አገሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እኛን ፡ እስከሚቻለው ፡ ድረስ ፡ ፈልጎ ፡ ካጣን ፡ በኋላ ፡ የፊታውራሪ ፡ አያሌውንና ፡ ያሽከሮቻቸውን ፡ ቤት ፡ አቃጥሎ ፡ ሲመለስ ፡ አርበኞችዎ ፡ በየቦታው ፡ ሥፍራ ፡ ይዘው ፡ ቆይተው ፡ ብዙ ፡ ጐዱት ።

የዳንግላውም ፡ ወደ ፡ ዳንግላ ፡ የአለፋውም ፡ ወደ ፡ አለፋ ፡ በመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ ያጋጠማቸውን ፡ የባላገር ፡ ከብት ፡ እየነዱ ፡ ሄዱ ፤

ፊታውራሪ ፡ አያሌውም ፡ የተቃጠለባቸውን ፡ ቤት ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ከጠዋት ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ አሠርተው ፡ ለምሳ ፡ ጋበዙን ፤ ከማብሃሮውም ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ስላልጎደለ ፡ ትላንትና ፡ ቤታቸው ፡ ተቃጥሎ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ፤

መስከረም ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ከዝብስት ፡ ወደ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሳን ፤ ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ በሰውም ፡ በከብትም ፡



እርዳታ ፡ ጓዛችንን ፡ አስነስተው ፡ ለጦርም ፡ እንዳንሰጋ ፡ የሚበቃ ፡ ወታደር ፡ አስከትለው ፡ ከኛው ፡ ጋራ ፡ ተጓዙን ፤

መንገዳችን ፡ በግሥጋሴ ፡ ስለነበረ ፡ ራዲዮውን ፡ ከአቶ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ጋራ ፡ ዝብስት ፡ ትተነው ፡ ሄድን ፤ ዳግም ፡ ካፒቴን ፡ ክሩሽሌ ፡ የሚባሉት ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መልክተኛ ፡ ወደ ፡ በላያ ፡ ሄደው ፡ የበላያን ፡ አኳኋንና ፡ የአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ የተባለውን ፡ ሜዳ ፡ እንዲመረምሩና ፡ እንዲመጡ ፡ ብለው ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ስለነገሩኝ ፡ ከፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ ዘበኛ ፡ ጨምረን ፡ ከዝብስት ፡ ወደ ፡ በላያ ፡ ሄዱ ።

ዝብስት ፡ እንደደረስን ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ በድንገት ፡ ደርሶብን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እርዳታ ፡ እንዲሰዱ ፡ ወደ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፌላቸው ፡ ነበርና ፡ ደብዳቤው ፡ እንደደረሳቸው ፡ አከታትለው ፡ የጦር ፡ ርዳታ ፡ ስለላኩ ፡ በመንገዳችን ፡ ላይ ፡ የ፫ ፡ ፊታውራሪ ፡ ጦር ፡ አገኘን ፤ ፊታውራሪ ፡ አይንግዳ ፤ ፊታውራሪ ፡ አደመና ፤ ፊታውራሪ ፡ ሞገስ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻም ፡ እስከ ፡ ዓባይ ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ በሰልፍ ፡ ተቀበሉን ፡ ሕዝቡ ፡ እንዲተሰበሰበ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጥተናቸው ፡ ያዋጁ ፡ ቃል ፡ ለሕዝቡ ፡ ተነበበለት ፤

አባይን ፡ ስንሻገር ፡ ጊዜው ፡ መሽቶብን ፡ ነበርና ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጋራ ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ለመነጋገር ፡ አልቻልንም ፤ የቦደንሐና ፡ በምትባል ፡ ደብር ፡ በጉታ ፡ ውስጥ ፡ አድረን ፡ በማግሥቱ ፡ የ፫ ፡ ሰዓት ፡ መንገድ ፡ ከሄድን ፡ በኋላ ፡ ናዳ ፡ ማርያም ፡ ላይ ፡ ሰፈር ፡ አደረግን ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈውን ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ተነጋግረንበት ፡ እንደሚከተለው ፡ ተስማምተናል ፤

፩ ፤ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ከሱዳን ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ የሚገባበትን ፡ መንገድ ፤

፪ ፤ ለዚህ ፡ ለሚገባው ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ መቀመጫ ፡ ላደጋ ፡ የማያሰጋ ፡ ሥፍራ ፡ መምረጥ ፤

፫ ፤ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የሚመጡበትን ፡ ጊዜና ፡ ሥፍራ ፤

፬ ፤ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ወታደር ፡ አሰባስብ ፤

፭ ፤ የእህልና ፡ የሌላም ፡ የምግብ ፡ ነገር ፡ አሰባስብ ፤

፮ ፤ ስለ ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ሥራ ፤

፯ ፤ የኢትዮጵያና ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መልክተኞች ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ሆነው ፡ ስለሚሠሩበት ፡ ሥፍራ ፡ (ሄድ ፡ ኳርተር) ።

ከሥራ ፡ ሁሉ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ወደዚህ ፡ እንዲገባ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ የሚመጣበትን ፡ መንገድ ፡ ለማዘጋጀት ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከተለውን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ተነጋግረን ፡ ተስማምተንበታል ።

(ሀ) ፤ መጀመሪያ ፡ እስከ ፡ ኅዳር ፡ ወር ፡ እኩሌታ ፡ ድረስ ፡ የደጋው ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ቆላ ፡ ለመውረድ ፡ የማይፈቅድ ፡ በመሆኑ ፡ ከኅዳር ፡ በፊት ፡ መሣሪያ ፡ ለማምጣት ፡ ወደ ፡ ቆላ ፡ አገር ፡ የሚወርድ ፡ ሰው ፡ ለማግኘት ፡ የማይቻል ፡ ስለሆነ ፤ ሁለተኛ ፡ የአለፋው ፡ ሕዝብ ፡ ለኢጣልያን ፡ እማኝ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በቆላውም ፡ ቢሆን ፡ ከዝብስት ፡ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ ያለው፡ መንገድ ፡ ለጓዝ ፡ ማመላለሻ ፡ የማያስጋ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመናገር ፡ የማይቻል ፡ ስለ ፡ ሆነና ፡ የአለፋው ፡ መንገድ ፡ ከተከፈተ ፡ ከኅዳርም ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ቢሆን ፡ መሣሪያ ፡ ለማምጣት ፡ እስከ ፡ ሰራቆ ፡ ድረስ ፡ ለሰው ፡ መላክ ፡ ስለሚቻል ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ በፍጥነት ፡ የአለፋን ፡ መንገድ ፡ ሊያስከፍቱ ፤

(ለ) ፤ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ወደ ፡ አለፋ ፡ ከመዝመታቸው ፡ በፊት፡ ወደ ፡ አለፋ ፡ ሲዘምቱ ፡ ከቡሬ ፡ ዳሞት ፡ ጠላት ፡ ጦር ፡ በጀርባ ፡ እንዳይጭን ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽን ፡ እንዲጠይቁ ፡ ጠይቀናቸው ፡ የተቆረጠውን ፡ ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ለማስታወቅ ፤

(ሐ) ፤ የአለፋ ፡ ሕዝብ ፡ በጦርነትና ፡ ወንድም ፡ ለወንድም ፡ ደም ፡ በመፋሰስ ፡ ከሚያምን ፡ እንደ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ትእዛዝ ፡ በሰላም ፡ እንደሚያምን ፡ መሞከር ፡ የሚያስፈልግ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መጀመሪያ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ የአለፋን ፡ ባላባቶች ፡ በወረቀት ፡ ጽፈው ፡ እንዲጠይቁ ፤ በሰላም ፡ መንገድ ፡ የማይሆን ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ የለንምና ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ እንዲሄዱበት ፤

(መ) የጦሩም ፡ አካሄድ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይሆናል ፤

ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ መኰንን ፡ ያቾፈርን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በግምባር ፡ ይሄዳሉ ፤ መሐሉን ፡ አቾፈር ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ አለፋ ፡ አፋፍ ፡ ድረስ ፡ ሲያስፈልግም ፡ አለፋ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ራሳቸው ፡ የጉታ ፡ የሰከላንና ፡ የአንክሻን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ይሄዳሉ ፤ በስተግራ ፡ በኩል ፡ የዳንግላን ፡ ምሽግ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሞገስ ፡ ፊታውራሪ ፡ አደመና ፡ ፊታውራሪ ፡ አይንግዳ ፡ ያገው ፤ የኳኩራንና ፡ የዱርቤቴን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ከበው ፡ ይጠብቃሉ ፤ በስተቀኝ ፡ በኩል ፡ የባህር ፡ ዳሩ ፡ እንዳይወጣ ፡ ፊታውራሪ ፡ አልጣሁ ፤ ፊታውራሪ ፡ መኰንን ፤ ፊታውራሪ ፡ ታዬና ፡ ፊታውራሪ ፡ ዘገዬ ፡ የሜጫን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ የባሕር ፡ ዳር ፡ ዳንግላ ፡ የከሚዮኑን ፡ መንገድ ፡ ይጠብቃሉ ፤ የቁንዝላው ፡ ይኸንን ፡ ያህል ፡ የሚያስፈራ ፡ ጦር ፡ ስለሌለው ፡ ጥቂት ፡ በአቾፈር ፡ ጦር ፡ ተቀንሶለት ፡



እንዲጠብቀው ፡ ወይም ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ ታስቦበት ፡ ሌላ ፡ ከቦ ፡ የሚጠብቀው ፡ ጦር ፡ ይታዘዛል ።

ሠ/ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ጦር ፡ አስከትቶ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ ለመነሳት ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ግንኙነት ፡ አድርገን ፡ የቆረጥነውን ፡ ካስታወቅናቸው ፡ ከስምንት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ጦሩ ፡ ይዘምታል ፤

የአለፋ ፡ መንገድ ፡ ከተከፈተ ፡ በኋላ ፡ ዝብስትን ፡ ከአደጋ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ እርግጠኛው ፡ የማያስጋ ፡ ከጠላት ፡ ምሽግ ፡ ሁሉ ፡ የራቀ ፤ በጥቂት ፡ መሣሪያና ፡ ወታደር ፡ ሊጠበቅ ፡ የሚቻለው ፡ ቦታ ፡ የበላያ ፡ ነው ፤ መሣሪያ ፡ እስከ ፡ በላያ ፡ ድረስ ፡ ከመጣ ፡ ከኅዳር ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ እስከ ፡ በላያ ፡ ድረስ ፡ ወርዶ ፡ ያመጣል ፤

መሣሪያው ፡ በላያ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ከጠላት ፡ እጅ ፡ ይወድቃል ፡ ብለን ፡ እንዳንሰጋ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አረጋግጠዋል ፤

ይህ ፡ መንገድ ፡ ተከፍቶ ፡ የሚበቃ ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የሚመጡበትን ፡ ጊዜና ፡ ሥፍራ ፡ ወስነን ፡ ለመቁረጥ ፡ አልተቻለም ። እንደዚሁም ፡ ይህ ፡ መንገድ ፡ ተከፍቶ ፡ በጃችን ፡ የሚበቃ ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ካልገባ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ያህል ፡ ወታደር ፡ እህልና ፡ ማንኛውንም ፡ የምግብ ፡ ነገር ፡ ለማሰብሰብ ፡ አይቻልም ።

ስለ ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ሥራ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ለሚሠሩት ፡ የፕሮፓጋንዳ ፡ ሥራ ፡ እንዲረዳቸው ፡ በየጠላት ፡ ምሽግና ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ የተደረገውንና ፡ የሚወራውን ፡ እርግጠኛ ፡ ወሬ ፡ መሰብሰብና ፡ ማስታወቅ ፡ ዳግም ፡ ለኢጣልያን ፡ እማኝ ፡ የሆኑትን ፡ ስማቸው ፡ የታወቀውን ፡ ሰዎች ፡ ታሪክ ፡ ጠይቆ ፡ ማወቅና ፡ ማስታወቅ ፤

ስለ ፡ መሥሪያ ፡ ቦታ ፡ (ሄድ ፡ ኳርተር) ፡ ለአደጋ ፡ የማያሰጋና ፡ ለሁሉም ፡ አማካይ ፡ የሚሆነው ፡ ስፍራ ፡ ወንድማገ ፡ ወይም ፡ ባቅራቢያው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ስለነገሩን ፡ ሄደን ፡ እንድናየው ፡ ተነጋግረንበት ፤

መስከረም ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ አባይን ፡ ሳንሻገር ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ከነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ ከወምበርማ ፡ ወዲህ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ እንዲገናኙን ፡ ጽፈላቸው ፡ ነበርና ፡ መልሱ ፡ ስለ ፡ ዘገየብን ፡ ሥራ ፡ እንዳንፈታ ፡ ወደፊት ፡ መንገዱን ፡ ቀጥለን ፡ መልስ ፡ እንጠብቃለን ፡ በማለት ፡ መስከረም ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ተሰናብብተን ፡ ጉዞ ፡ ጀመርን ። እኔ ፡ ለጻፍኩላቸው ፡ መልስ ፡ በመስከረም ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤያቸው ፡ መስከረም ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ሰከላ ፡ ጊሽ ፡ አባይ ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ ደረሰን ፤

መስከረም ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ከቀኑ ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ ጅግርታ ፡ ዮሐንስ ፡ ላይ ፡ ተገናኘተን ፤ ከ፳፱ የሚበልጥ ፡ ጦር ፡ ተከትሎዋቸው ፡ በሰልፍ ፡ ተቀበሉን ፤ የግርማዊነትዎን ፡ ደብዳቤ ፡ ስጥተናቸው ፡ ለሕዝቡ ፡ አዋጁን ፡ ከአነበብንለት ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሥራችን ፡ ጉዳይ ፡ ንግግር ፡ ጀመርን ፤ በሰፊው ፡ ከተነጋገርን ፡ በኋላ ፤ ሌቱን ፡ አስቤበት ፡ መልሱን ፡ ነገ ፡ ጠዋት ፡ አስታውቃችኋለሁ ፡ ብለውን ፡ አደርን ፤



ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ።

ጠዋት ፡ በነገታው ፡ መስከረም ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ በጽሕፈት ፡ የሰጡን ፡ መልስ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተልኳል ፤ ተነጋግረን ፡ ከተስማማንበት ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ የአለፋን ፡ መንገድ ፡ ለመክፈት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ወደ ፡ አለፋ ፡ ሲዘምቱ ፡ የቡሬውን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ያግዳሉ ፤ ለዚሁም ፡ ከቡሬ ፡ ወደ ፡ እንጀባራ ፡ በሚሄደው ፡ በካሚዮን ፡ መንገድ ፡



ፈጣም ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ የተሠራውን ፡ ቲሊሊ ፡ የሚባለውን ፡ ድልድይ ፡ ማስፈረስ ፡ አንደኛው ፡ ሥራቸው ፡ ስለሆነ ፡ ከማርቆስ ፡ ወደ ፡ ቡሬ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ገባ ፡ የሚባል ፡ ወሬ ፡ ስለደረሰ ፡ በኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ምክር ፡ ድልድዩን ፡ አስፈርሰዋል ።

የአለፋው ፡ ሥራ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ በደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በኩል ፡ ከወምበርማ ፡ እስከ ፡ ሬሳሪስ ፡ ያለውን ፡ መንገድ ፡ ለመክፈት ፡ ሁለቱ ፡ ደጃዝማቾች ፡ ፈቅደዋል ፤

እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ መንገዶች ፡ ይልቁንም ፡ ከወምበርማ ፡ እስከ ፡ ሬሳሪስ ፡ የተባለው ፡ መንገድ ፡ ከተከፈተ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ያለችግርና ፡ ያለስጋት ፡ ወዳገሩ ፡ ለመግባት ፡ ይችላል ፤ ከግርማዊነትዎ ፡ መምጣት ፡ በፊት ፡ ግን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የታሰቡት ፡ ወታደሮች ፡ ሙሉ ፡ መሣሪያቸውን ፡ እንደያዙና ፡ ሌላም ፡ በቂ ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲገባ ፡ ማስፈለጉን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አሳስባለሁ ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ እኛ ፡ ሄደን ፡ ባናየው ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽና ፡ ከሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ የቦታውን ፡ አኳኋን ፡ እንዳገኘነው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ መግቢያ ፡ ለጊዜው ፡ በሐሳባችን ፡ ውስጥ ፡ ያለውና ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ካየነው ፡ ሥፍራ ፡ ሁሉ ፡ የተሻለ ፡ የመሰለን ፡ ወምበርማ ፡ ነው ፤ ይኸንንም ፡ ሥፍራ ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ሄደው ፡ እንዲያዩት ፡ ተነጋግረንበታል ፤ የቦታውንም ፡ አኳኋን ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ በተላከው ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በሰጡን ፡ ማስታወሻ ፡ ወይም ፡ መልስ ፡ ውስጥ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ይረዳዋል ፤ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጫካ ፡ ስላለበት ፡ ለአውሮፕላን ፡ አደጋ ፡ አያስጋም ፤ የጠላትም ፡ ጦር ፡ እንዳይገባ ፡ በጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ ሊታገድ ፡ ይቻላል ፤ ከዚህ ፡ በፊትም ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ገብቶበት ፡ አያውቅም ፤ ለመግባትም ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አቅቶት ፡ ተመለሰ ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ በጫካ ፡ የተከበበ ፡ ለአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ የሚሆን ፡ ሰፋፊ ፡ ሜዳ ፡ አለበት ፡ ይባላል ፤ ከወደምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ከባቢው ፡ ዐባይ ፡ ነው ፤ በዐባይም ፡ በኩል ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ጠላት ፡ ለመግባት ፡ ሞክሮ ፡ አቅቶት ፡ ተመልሷል ፤ በተረፈ ፡ አገሩ ፡ ባቅራቢያውም ፡ ያሉት ፡ አገሮች ፡ በእህል ፡ ረገድ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሊኖርበት ፡ ይችላል ፤ በያይነቱ ፡ እህል ፤ ነጭ ፡ ጤፍ ፤ ቅቤ ፤ ሥጋ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንደልብ ፡ ይገኝበታል ።

አስቀድሞ ፡ ባይዘጋጅም ፡ እንኳን ፡ ለጊዜው ፡ ለሁለትና ፡ ለሶስት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ለሁለት ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ የሚበቃ ፡ እህል ፡ ለመስጠት ፡ እችላለሁ ፡ ብለው ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተውናል ፤ ይኸውም ፡ እህል ፡ ለወደፊት ፡ ካገር ፡ የሚጠየቅ ፡ ሳይሆን ፡ አሁን ፡ በጐተራቸው ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ነግረውናል ።

ይህ ፡ ሥራ ፡ በቶሎ ፡ እየተከናወነ ፡ እንዲሄድና ፡ ለሕዝቡም ፡ የማጽናኛ ፡ ስብከት ፡ እንዲሆን ፡ በማለት ፡ ሁለቱ ፡ ደጃዝማቾች ፡ ተገናኝተው ፡ ያለፈውን ፡ ቅያሜ ፡ ይቅር ፡ ተብበለው ፡ በተስማማንበት ፡ የሥራ፡ ጉዳይ ፡ እንዲመካከሩ ፡ ለማገናኘት ፡ መስከረም ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ተመለስኩ ፤ ይኸውም ፡ የደጃዝማች ፡ ነጋሽን ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ካገኘሁ ፡ በኋላ ፡ ነው ፤ ለጥቅምት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ አሸፋ ፡ ጉንድል ፡ ላይ ፡ እንዲገናኙ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻን ፡ ቀጥሬአቸው ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽንም ፡ ለመቅጠር ፡ ወዳሉበት ፡ ሄጃለሁ ። ይኸውም ፡ ግንኙነት ፡ ስለ ፡ አለፋ ፡ የቆረጥነውንና ፡ የተስማማንበትን ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ እንዳያዘገየው ፡ ከግንኙነቱ ፡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ አለፋ ፡ ይሄዳሉ ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽም ፡ የቡሬን ፡ ጦር ፡ ይጠብቃሉ ፤

ስለዚህ ፡ ከጥቅምት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የአለፋ ፡ ጦርነት ፡ ይጀመራል ፡ ስል ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ፤

ከዚህ ፡ ጋራ ፡ በያለበት ፡ አርበኞቻችን ፡ በጠላት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ እየጣሉ ፤ መንገድ ፡ እየቆረጡ ፤ ወደ ፡ ጠላት ፡ ምሽግ ፡ እህል ፡ ፈረስ ፡ ቅቤና ፡ ማር ፡ እንዳይገባ ፡ እያደረጉ ፡ የጠላትን ፡ ሐሳብና ፡ ፕላን ፡ እንዲያሰናክሉና ፡ ያለውን ፡ ጥይትና ፡ ቤንዚን ፡ እንዲጨርስ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ከብዙ ፡ አርበኞች ፡ ጋራ ፡ ተነጋግረናል ።

እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ እንደሚገባ ፡ ለመሥራት ፡ የሚቻለው ፡ በቀለብና ፡ በደምብ ፡ የቆመ ፡ ወታደር ፤ ሲኖር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሕዝብና ፡ ፋኖ ፡ የሚዋጋው ፡ በፈቃዱ ፡ ስለሆነ ፡ በግድ ፡ ለማዘዝ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ በፍጹም ፡ ተከቦ ፡ እህልና ፡ ፈረስ ፡ ማርና ፡ ቅቤ ፡ እንዳይገባ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ፡ ብለው ፡ ሊያረጋግጡልን ፡ አልቻሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አይደረግም ፡ ብለው ፡ ይሉናል ፤ ስለዚህ ፡ አንዳንድ ፡ በካሚዮን ፡ መንገድ ዳርና ፡ በምሽግ ፡ አጠገብ ፡ ላሉት ፡ አርበኞች ፡ አንዳንድ ፡ ደህና ፡ አድርገን ፡ በዘብ ፡ ልናስጠብቀው ፡ በሚያስፈልግ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ላሉት ፡ አርበኞች ፡ ለሃምሳ ፤ ለመቶ ፡ ለሶስት ፡ መቶ ፡ ወታደር ፡ እንደስፍራውና ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ አስፈላጊነትና ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ ቀለብ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ ተነጋግረንበታል ፤ ላንድ ፡ ወታደር ፡ በወር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ያስፈልገዋል ፡ ብለን ፡ የጠየቅናቸው ፡ ሁሉ ፡ አሥር ፡ አሥር ፡ ብር ፡ ገመቱ ፤



፩ ከልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀና ፡ ከልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ ጋር ፡ በቶሎ ፡ ተገናኝተን ፡ እንደዚሁ ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ከተነጋገርን ፡ በኋላ ፡ የመሥሪያ ፡ ቤታችንን ፡ (ሄድ ፡ ኳርተር) እንመርጣለን ፡ ብለን፡ የነበርነው ፡ መስከረም፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ለጻፍኩላቸው ፡ ደብዳቤ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ መልስ ፡ አላገኘሁም ። ከልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ እስክገናኝ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ለመላላክ ፡ አልቻልንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የግርማዊነትዎን ፡ አዋጅ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ እስከሚቻላቸው ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ እንዲልኩ ፡ በብዙ ፡ ልኬላቸዋለሁ ፤ ለልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውና ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ላሉት ፡ ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬም ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ሳይንትና ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ እንዲልኩት ፡ እንደዚሁ ፡ ልኬላቸዋለሁ ። ወደ ፡ በጌምድር ፡ አርበኞችም ፡ ጽፌ ፡ ገና ፡ መልስ ፡ አላገኘሁም ።

፪ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ ከወሎ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ መጥተው ፡ እነብሴ ፡ ላይ ፡ ከልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ ጋራ ፡ ስለሆኑ ፡ ተገናኝቼ ፡ ላነጋግራቸውና ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ በተለይ ፡ ለሚዘጋጀው ፡ ወታደር ፡ እርሳቸውን፡ ዋና ፡ አድርጎ ፡ ለማዘጋጀት ፡ አስቤአለሁና ፡ ለዚሁ ፡ ሃሳብ ፡ ተወስኖ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲላኩላቸው ፡ ስል ፡ እመለከታለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲተገብትና ፡ ሥራውም ፡ እንደሚገባ ፡ እንዲሠራ ፡ በማለት ፡ ነው ፡

---

፩ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ፡ አባታቸው ፡ አቶ ፡ ዘለቀ ፡ ጐጃም ፡ በረንታ ፡ ከተባለ ፡ ቀበሌ ፡ የሚወለዱ ፡ ናቸው ። ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረበት ፡ ጊዜ ፡ በጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የአርበኝነት ፡ ሞያ ፡ ከጀመሩት ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ አንደኛው ፡ ናቸው ። በአርበኝነት ፡ ዘመናቸውም፡ በውስጣቸው ፡ ብዙ ፡ አርበኞች ፡ ይተዳደሩና ፡ ይመሩ ፡ ነበር ። በውስጣቸው ፡ ለሚተዳደሩትም ፡ አርበኞች ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ሳይቀር ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ አፈንጉሥ ፡ እያሉ ፡ ይሾሙ ፡ ነበር ። እንደዚሁ ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ በሚያደርጉበት ፡ ጊዜ ፡ ወንድማቸውን ፡ እጅጉ ፡ ዘለቀ ፡ የሚባለውን ፡ ደጃዝማች ፡ ብለው ፡ ሲሾሙት ፡ «ጋሼ ፡ ስሙን ፡ ሁሉ ፡ ጨረስከው ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ልትባል ፡ ነውን? ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ «ለእኔ ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ ምን ፡ ያስፈልጋል ፡ እናቴ ፡ በላይ ፡ ብላኝ ፡ የለም ፡ ወይ» ፡ አሉት ፡ ይባላል ። በአካባቢያቸው ፡ የነበሩት ፡ ልዑል ፡ በላይ ፡ እያሉ ፡ ሲጠሩዋቸው ፡ በጽሑት ፡ ያሉት ፡ አጼ ፡ በተልበቱ ፡ እያሉ ፡ ይጠሩዋቸው ፡ ነበረ ። በአስተዳደሩ ፡ ተፈርተውና ፡ ተከብረው ፡ ትእዛዛቸውም ፡ በደምብ ፡ የሚፈጸም ፡ ነበር ።

፪ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ በወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የአልቡኮ ፡ ተወላጅ ፡ ባላባት ፡ ናቸው ። ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረበት ፡ ጊዜ ፡ በትውልድ ፡ አገራቸው ፡ ሳሉ ፡ የጠላትን ፡ አስተዳደር ፡ በመጥላት ፡ እቢታቸው ፡ የሚመላለሰውን ፡ የጣሊያን ፡ ጀኔራል ፡ ገድለው ፡ ሀብትና ፡ ርስታቸውን ፡ ቤታቸውን ፡ ማለት ፡ መላ ፡ ንብረታቸውን ፡ ትተው ፡ ከወሎ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ተሻግረው ፡ ጐጃም ፡ ካሉ ፡ አርበኞች ፡ ከነልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ (ራስ) ፡ ጋራ ፡ ተቀላቅለው ፡ የአርበኝነት ፡ ተግባራቸውን ፡ ሲፈጽሙ ፡ ቆይተዋል ። እኛም ፡ ከግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ታዝዘን ፡ ቀዳሚ ፡ መላክተኛ ፡ ሆኜ ፡ ጐጃም ፡ በገባሁበት ፡ ጊዜ ፡ ሞጣ ፡ እውራጃ ፡ ከልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ (ራስ) ፡ ከልጅ ፡ ደበበ ፡ ወዳጆ ፡ ከቀኛዝማች ፡ ሽፈራው ፡ ረታ ፡ ከቀኛዝማች ፡ አበሻ ፡ መጃሉ ፡ ጋራ ፡ አግኝቻቸው ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ላለው ፡ ሥራ ፡ ዋና ፡ ረዳት ፡ ሆነውኝ ፡ አብረን ፡ እየተዘዋወርን ፡ ሠርተዋል ። ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀም ፡ ዘንድ ፡ ሄጄ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይለዩ ፡ አብረውኝ ፡ ሄደው ፡ በኋላም ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ሲመጡ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ መተከል ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ የተቀበሉ ፡ ታማኝ ፡ አገልጋይ ፡ ናቸው ። ግርማዊነታቸው ፡ ዳሞት ፡ ሲደርሱ ፡ በሳይንት ፡ በኩል ፡ ወደወሎ ፡ ተልከው ፡ ቀድመው ፡ ሄደዋል ።



ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ ።

እንጂ ፡ ወረቀት ፡ እስኪመጣ ፡ እንዲጠብቁ ፡ ሳላደርግ ፡ እንደተገናኘን ፡ ተነጋግሬ ፡ ሥራውን ፡ እንዲጀምሩ ፡ ለማድረግ ፡ ነውና ፡ ያሰብኩት ፡ ነገሩ ፡ የተቆረጠ ፡ ሆኖ ፡ እንዲታሰብበት ፡ አመለክታለሁ ። ሁለተኛ ፡ የወለጋውን ፡ ፩ ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴን ፡ እዚሁ ፡ ስላገኘኋቸው ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ እንዲይዙ ፡ ለማድረግ ፡ አስቤያለሁና ፡ የተወሰነ ፡ ሳይሆን ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ የሚመሩ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲደርሳቸው ፡ አመለክታለሁ ። እርሳቸውንም ፡ ቢሆን ፡ ለጊዜው ፡ ደብዳቤው ፡ እስኪደርሳቸው ፡ ድረስ ፡ የማያቆይ ፡ ሥራ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ እንዲሠራ ፡ ለማድረግ ፡ አስቤአለሁና ፡ እንዲታወቅ ፡ ደብዳቤው ፡ እስኪመጣላቸው ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ እንዳያልፍ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ቃል ፡ በቴሌግራም ፡ ቢመጣላቸው ፡ መልካም ፡ ነው ።

---

፩ ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ፤ በወለጋ ፡ ጉድሩ ፡ በራስ ፡ ደምሰው ፡ ውስጥ ፡ ጕንደፌ ፡ ተብለው ፡ በሚጠራው ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ በማይጨው ፡ ዘመቻ ፡ ከቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ ደምሰው ፡ ጋራ ፡ በራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ መሪነት ፡ ዘምተው ፡ የነበሩ ፡ ከማይጨው ፡ ዘመቻም ፡ በኋላ ፡ ወለጋ ፡ እግባት ፡ አገራቸው ፡ ገብተው ፡ ሳለ ፡ እንሻለሁ ፡ መስፍንና ፡ (ራስ) ፡ ብላታ ፡ ታከለ ፡ (ደጃዝማች) ፡ ግራዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፡ (ደጃዝማች) ፡ በአርበኝነት ፡ ሲዘዋወሩ ፡ ወለጋ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በአርበኝነት ፡ ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ ተደባልቀው ፡ የሠሩ ፡ ወደጎጃምም ፡ ሲሻገሩ ፡ አብረው ፡ ተሻግረው ፡ እነሱ ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ ሲሄዱ ፡ እሳቸው ፡ ጐጃም ፡ ስለቀሩ ፡ ቀዳማዊ ፡ መልክተኛ ፡ ሆኜ ፡ ጐጃም ፡ በገባሁበት ፡ ጊዜ ፡ በዳሞት ፡ ክፍል ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ ጋራ ፡ ያገኘኋቸው ፡ ናቸው ።



ስለ ፡ ፩ አቶ ፡ ጊላ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወደዚያ ፡ መምጣት ፡ ተነጋግረን ፡ እንዲሄዱ ፡ ከቆረጥን ፡ በኋላ ፡ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ ተመካከረን ፡ እዚህ ፡ ሆነው ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ጥቅሙ ፡ የበለጠ ፡ መስሎ ፡ ስለታየን ፡ እርሳቸው ፡ የታዘዙትን ፡ ሥራ ፡ አቶ ፡ አሥጋኸኝ ፡ ይዞ ፡ እንዲሄድና ፡ እርሳቸው ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠሩ ፡ አድርጌአለሁ ። የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ከገባ ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ የቆዩ፡ ስለሆኑ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የነበረውንና ፡ ያለውን ፡ እርግጠኛ ፡ አኳኋንና ፡ የኾነን ፡ አርበኞች ፡ ግምት ፡ ጃንሆይ ፡ ከርሳቸው ፡ ቢያገኙት ፡ ለወደፊት ፡ ሥራዎ ፡ የሚረዳ ፡ መስሎ ፡ ስለታየኝ ፡ አንድ ፡ ረጅም ፡ ማመልከቻ ፡ ጽፈው ፡ ባቶ ፡ አሥጋኸኝ ፡ እጅ ፡ እንዲልኩ ፡ ጠይቄአቸው ፡ እሺ ፡ ብለውኛል ።

እስረኞቹ ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ፤ አንደኛው ፡ ቢሾና ፡ የሚባለው ፡ ወታደር ፡ (ሶልዳቶ) ፡ ከሚጠብቃቸው ፡ ዘበኛ ጋራ ተጣልተው ፡ ዘበኛው ፡ በጥይት ፡ ገደለው ፡ ብለው ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ነገሩኝ ፡ ስለርሱም ፡ አሟሟት ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አንድ ፡ ማመልከቻ ፡ ጽፈው ፡ ባቶ ፡ አሥጋኸኝ ፡ እጅ ፡ እንዲልኩ ፡ ጠይቀናቸው ፡ እሺ ፡ ብለዋል ።

፪ ቲኔንቲ ፡ አልፎንሶ ፡ ፖሎ ፡ ግን ፡ ያለው ፡ አሁን ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እርሱንም ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ክርስትና ፡ አንስተውት ፡ የክርስትና ፡ ስሙንም ፡ ሣህለ ፡ ማርያም ፤ አሰኝተውታል ። እርሱም ፡ በኑሮው ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎታል ።

---

፩ አቶ ፡ ጊላ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (ፊታውራሪ) ፡ የትውልድ ፡ አገራቸው ፡ ኤርትራ ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ጐጃም ፡ ገዥ ፡ በነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ከሱዳን ፡ መጥተው ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ሲኖሩ ፡ ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረበት ፡ ጊዜም ፡ የጐጃም ፡ ሕዝብ ፡ ለጠላት ፡ እንገዛም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ አርበኝነት ፡ በተሰማራበት ፡ ጊዜ ፡ ከጠላት ፡ ተለይተው ፡ እስከመጨረሻው ፡ በምክር ፡ እየረዱ ፡ ከቢትወደድ ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ ጋራ ፡ የቆዩ ፡ ጉታ ፡ ለተቋቋመው ፡ ኰሚቴም ፡ ዓይነተኛ ፡ አባል ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ። እኔም ፡ ጐጃም ፡ ስደርስ ፡ በኰሚቴው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ቢታቸውን ፡ ሠርተው ፡ ከኰሚቴው ፡ ሠራተኛ ፡ ከነካፒቴን ፡ ከበደ ፡ ወልደ ፡ ሰማያት ፡ ልጅ ፡ ደግባሕልና ፡ አቶ ፡ ገብሬ ፡ መታፈሪያን ፡ ጭምር ፡ ያገኘኋቸው ፡ ናቸው ። ኰሚቴውንም ፡ ያቋቋሙት ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ሎሬንሶ ፡ ታዕዛዝና ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ አቶ ፡ አሥጋኸኝ ፡ አርአያ ፡ ከግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተልከው ፡ ወደ ፡ አርበኞች ፡ ዘንድ ፡ ጐጃም ፡ መጥተው ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። የኰሚቴው ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባር ፡ በየጊዜው ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ የሚደረገውን ፡ ተጋድሎ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ማስተላለፍና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የሚገኘውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ለአርበኞች ፡ እንዲደርስ ፡ ማድረግ ፡ ነበር ።

፪ ቲሌንቲ ፡ ፖል ፡ አልፎንሶ፤ የኢጣሊያን ፡ ወታደር ፡ የነበረ ፡ ምርኮኛ ፡ እደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ ዘንድ ፡ የነበረ ፡ ነው ። እንደተማረከ ፡ ወገንና ፡ ጥግ ፡ እንዲሆኑት ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽን ፡ ክርስትና ፡ ያንሱኝ ፡ ብሎ ፡ አንስተውት ፡ ነበርና ፡ ለማታለል ፡ ያደረገው ፡ እንዳይሆን ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግበት ፡ ታስቦ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሰው ፡ ግርማዊነታቸው ፡ እስከተመለሱበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ጋራ ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

በየመንገዱ ፡ ፖስታ ፡ ተቀባይ ፡ መልክተኛ ፡ ማቆም ፡ ለጊዜው ፡ አልተቻለም ፤ በየመንገዳችን ፡ የተገናኘናቸውን ፡ ሹማምንቶች ፡ ኃላፊ ፡ እንዳናደርጋቸው ፡ ፖስታ ፡ ሲመጣ ፡ በፍጥነት ፡ አለማስተላለፋቸውን ፡ ስለተረዳነውና ፡ ፖስታውን ፡ ባንድ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሳያስተላልፉት ፡ ስምንትና ፡ አሥር ፡ ቀን ፡ ስለሚያስቀምጡት ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ተቀባባይ ፡ መልክተኛ ፡ ከማድረግ ፡ በቀጥታ ፡ የሚመላለሱ ፡ ደምበኛ ፡ ፖስተኞች ፡ ማቆም ፡ የተሻለ ፡ መስሎ ፡ ስለታየንና ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ የሠለጠኑና ፡ የታመኑ ፡ ከዚህ ፡ በፊትም ፡ ከነአቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ ጋራ ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ወደዚህ ፡ በቶሎ ፡ እንዲላኩልን ፡ ባለፈው፡ ማመልከቻዬ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አመልክቼአለሁ ። አሁን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሀንግቼ ፡ ያልጻፍኩዋቸውን ፡ ጭምር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ስማቸውን ፡ እጽፋለሁ ።

አለቃ ፡ ክፍሌ ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ ቸኮል ፡ አቶ ፡ ዓለሙ ፡ ገብሬ ፡ አጋፋሪ ፡ ላቀው ፡ አቶ ፡ አብረሃና ፡ አቶ ፡ ኩምሳ ።

አቶ ፡ ፍቱይ ፡ ሐጎስና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ የመጣው ፡ ኃይሌ ፡ የሚባለውን ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ አስበናቸዋልና ፡ እንዲላኩልን ፡ አመለክታለሁ ።

እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በጣም ፡ የደከሙና ፡ ያገለገሉ ፡ መሆናቸውን ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ ስላመለከተኝ ፡ ፖስታ ፡ ማመላለስን ፡ ዝቅተኛ ፡ ሥራ ፡ አድርገውት ፡ ቅር ፡ እንዳይላቸው ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ፖስታ ፡ ማመላለስ ፡ ትልቅ ፡ ኃላፊነትና ፡ ታማኝነት ፡ ያለበት ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ መሆኑንና ፡ የድካማቸውም ፡ ዋጋ ፡ ተረስቶ ፡ እንደማይቀር ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ አፍ ፡ ቢሰሙ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነው ።

አሁን ፡ እኛ ፡ በመጣንበት ፡ መንገድ ፡ ፖስተኛ ፡ በግሥጋሴ ፡ ከጉታ ፡ ተነስቶ ፡ እስከ ፡ መተማ ፡ ድረስ ፡ ከ፲፫ ፡ እስከ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ይገባል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ደጋውን ፡ በአለፉ ፡ በኩል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በ፰ና ፡ በ፱ ፡ ቀን ፡ ከጉታ ፡ መተማ ፡ ይገባል ፡ ስለተባለ ፡ ማነኛውም ፡ ሥራችን ፡ ሁሉ ፡ የሚፋጠነው ፡ የአለፋና ፡ የወምበርማ ፡ ሬሳሬስ ፡ መንገዳችን ፡ ከተከፈተ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

አዲስ ፡ አበባ ፤ አሥመራ ፤ ምጥዋንና ፡ የቀሩትንም ፡ የኢጣልያ ፡ ቢንዚንና ፡ የጦር ፡ መጋረያ ፡ የተቀመጡባቸውን ፡ ከተማዎች ፡ የእንግሊዝ ፡ አውሮፕላኖች ፡ በየጊዜው ፡ በቦምብ ፡ መደብደባቸውን ፡ እንሰማለን ፡ ኢጣልያኖች ፡ በጋዜጣ ፡ ይጽፉታል ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ቦምብ ፡ መጣሉን ፡ የሚያወሩ ፡ የኢጣልያን ፡ ጋዜጣ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተልኳል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በጐጃም ፡ ላይ ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ ባለመደረጉና ፡ ከሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ ጋር ፡ መጋሪያ ፡ ለመቀበል ፡



የወረዱት ፡ የደጃዝማች ፡ መንገሻና ፡ የደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ሰዎች ፡ እስከ ሁን ፡ ድረስ ፡ ወዳገራቸው ፡ ባለመመለሳቸው ፡ በጐጃም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የኢጣልያን ፡ ኃይል ፡ እንደምናስበው ፡ ሊቀነስ ፡ አልተቻለም ።

ከየምሽጉ ፡ እየከዱ ፡ የሚመጡ ፡ አንዳንድ ፡ ሐማሴኖችና ፡ ባንዳዎች ፡ በምሽግ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የኢጣልያን ፡ ወታደርና ፡ ባንዳ ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ከሆነማ ፡ ለምን ፡ አውሮፕላኖች ፡ እዚህ ፡ መጥተው ፡ ቦምብ ፡ ወይም ፡ ውጡ ፡ የሚል ፡ ያዋጅ ፡ ወረቀት ፡ አይበትኑም ፡ እያሉ ፡ ያወራሉ ፡ ይላሉ ፤ ከሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ጋራ ፡ የወረዱትንም ፡ ሰዎች ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ በመንገድ ፡ አግኝቷቸው ፡ ብዙዎቹ ፡ አልቀዋል ፤ የተረፉትም ፡ ተበታትነው ፡ ጥቂቶች ፡ ሱዳን ፡ አገር ፡ ገብተዋል ፤ እነርሱንም ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ወደሌላ ፡ አገር ፡ ለጦርነት ፡ ወስዶዋቸዋል ፡ እየተባለ ፡ ስለሚወራ ፡ የነርሱ ፡ በቶሎ ፡ መመለስ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል።

ሁለተኛ ፡ የረዳታችን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ አውሮፕላኖች ፡ በጐጃም ፡ ላይ ፡ ያዋጅ ፡ ወረቀት ፡ ቢበትኑ ፤ ባንዳንድ ፡ በታወቁ ፡ ምሽጎች ፡ እንደ ፡ ዳንግላ ፤ ማርቆስ ፤ ባሕር ፡ ዳርና ፡ ቡሬ ፡ ላይ ፡ ቦምብ ፡ ቢጥሉ ፡ በጐጃም ፡ በሙሉ ፡ እንደሚያወራው ፡ ባንድና ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ ሁሉ ፡ ፈርሶ ፡ ጐጃም ፡ በሙሉ ፡ ከጠላት ፡ እጅ ፡ ነፃ ፡ ትወጣለች ፡ እኔ ፡ ግን ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ይህንን ፡ ያኽል ፡ ባይሆን ፡ እንኳን ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አርበኞች ፡ መንፈስ ፡ ይበረታል ፡ የሚወላወልም ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ባንድ ፡ ሐሳብ ፡ ይጸናል ፤ ብዙም ፡ ባንዳ ፡ እየከዳ ፡ ወደኛ ፡ ይመጣል ፤ ከግርማዊነትዎ ፡ መምጣት ፡ በፊት ፡ የጠላት ፡ ኃይልም ፡ በጣሙን ፡ ይመነምናል ። ስለዚህ ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ መምጣት ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ አውሮፕላኖች ፡ እንዲመጡ ፡ በጣም ፡ እንዲታሰብበት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አመለክታለሁ ። ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውና ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ እቦዬ ፡ በንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ «ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ያንድነትና ፡ የመተባበር ፡ ኮሚቴ» ፡ የጻፉትን ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲታሰብበት ፡ ኮሚቴው ፡ ወደኛ ፡ ያስተላለፈውን ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ልኬአለሁ ።

እንደተመለከትኩት ፡ በጐጃም ፡ ወረዳ ፡ አርበኛው ፡ ሕዝብም ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ጠላታችንም ፡ አደጋ ፡ ይጥሉብኛል ፡ በማለት ፡ ይሰጋል ፤ እንጂ ፤ አደጋ ፡ ይጥልብናል ፡ ብለው ፡ አርበኞችዎ ፡ አይሰጉም ። ነገር ፡ ግን ፡ አርበኞችዎ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ይጐድላቸዋል ፤ ይኸውም ፡ ስምምነትና ፡ ፍቅር ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ እንደደረስኩ ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አድርጌ ፡ የጀመርኩት ፡ የሚቻል ፡ ቢሆን ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በስምምነት ፡ የማይሆን ፡ ሲሆንና ፡ ከመሪዎቻቸው ፡ እየተለዩ ፡ እራሳቸውን ፡ በሥራችን ፡ እንታወቅበታለን ፡ የሚሉ ፡ አርበኞች ፡

ብዙ ፡ ስለሆኑ ፡ ለጊዜው ፡ ከመሪዎቻቸው ፡ እንዳይጣሉ ፡ እየመከርኩ ፡ እንዲቆዩ ፡ ለማድረግ ፡ አስቢአለሁና ፡ ወደፊት ፡ ይኸንን ፡ ለመስለው ፡ አኳኋን ፡ የሚሻለውን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ አስበውበት ፡ እንዲላኩብን ፡ አሳስባለሁ ፡ እኔም ፡ አሁን ፡ ተስፋ ፡ እየሰጠሁና ፡ እየመከርኩ ፡ እንዲቆዩ ፡ ለማድረግ ፡ ያሰብኩበት ፡ ምክንያት ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አርበኛ ፡ ከሁለት ፡ ፊት ፡ ያጣ ፡ እንደሆነ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ይገባል ፡ በማለት ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ማሞ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ጐጃም ፡ ቡሬ ፡ ዳሞት ፡ መጥቶ ፡ ከኢጣልያኖች ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚሠራ ፡ ለደከሙት ፡ ለጠላቶቻችን ፡ ጉልበት ፡ ሆኖ ፡ ስላስቸገረ ፡ ለመላላክ ፡ አስቢአለሁና ፡ ምናልባት ፡ ጥያቄዬን ፡ ተቀብሎ ፡ የሚወጣ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ምን ፡ እንደሚደረግለት ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ታስቦ ፡ እንዲላኩብኝና ፡ የሚቻልም ፡ ቢሆን ፡ አኳኋኑን ፡ አይቼ ፡ እልክለታለሁና ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲጻፍለት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አሳስባለሁ ።

ካርቱን ፡ ክሩሽሌ ፡ የበላይን ፡ አኳኋን ፡ መርምረው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ እንዳስታወቁን ፡ እበላይ ፡ ላይ ፡ ለአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ የሚበቃ ፡ ሜዳ ፡ የለም ።

ደጃዝማች ፡ ነጋሽና ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ሲገናኙ ፡ እንዲፈርሙበት ፡ ያሰብኩት ፡ የስምምነት ፡ ውል ፡ ግልባጩ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተልኳል ።

ጥቅምት ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
ታማኝ ፡ አገልጋይዎ
(ስለ ፡ አባቸ ፡ ከበደ) ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡

## ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ የቀረበ ፡ ማስታወሻ ።

፩ ፤ በሱዳን ፡ አገር ፡ የተከማቸው ፡ የመሣሪያና ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ የሚገባበት ፡ መንገድ ፡ የአንድ ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ ይዞ ፡ ያው ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ወታደር ፡ ያስፈልገዋል ፡ እንጂ ፡ በወምበራ ፡ በኩል ፡ ቶሎ ፡ ይገኛል ፡ ጠረፉም ፡ ዓባይና ፡ ጋላ ፡ ነው ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ኃይል ፡ ቢያገኝም ፡ የሚያልፍበት ፡ የለም ፤

፪ ፤ ገንዘቡና ፡ መሣሪያው ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ አደጋ ፡ ሳያገኘው ፡ የሚቀመጥበት ፡ ቦታ ፡ ዓባይና ፡ ጋላን ፡ አካባቢ ፡ አድርጎ ፡ በታች ፡ በኩል ፡ ኩባርና ፡ በአገው ፡ በኩል ፡ አዘና ፡ በዳሞት ፡ በኩል ፡ ጓጉሣና ፡ ወንበርማ ፡ ለማናቸውም ፡ አስፈላጊ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ለጠላት ፡ ጦር ፡ የማይመች ፡ መሆኑን ፡ ጊዜ ፡ ይመሰክርል



ናል ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እግሩ ፡ ደቅድቆት ፡ አያውቅም ፤ ለአውሮፕላንም ፡ ቦታው ፡ አይመችም ፤ ለእግር ፡ ጦርም ፡ ትንሽ ፡ ጦር ፡ ያቆመዋል ።

፫ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ የአለፋን ፡ መንገድ ፡ ለመክፈት ፡ ጦር ፡ ሲጭን ፡ ጠላት ፡ ከወደጀርባ ፡ ከቡሬ ፡ ጦር ፡ እንዳይወጣ ፡ መጀመሪያ ፡ የቴሊሊን ፡ ድልድይ ፡ ማፍረስ ፡ ነው ፡ ፪ኛ ፡ ከመንገድ ፡ በላይና ፡ ከመንገድ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ዘበኛ ፡ ማጠንከር ፡ ነው ፤

፬ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ መላክተኛ ፡ ተቀምጠው ፡ የሚሠሩበት ፡ ቦታ ፡ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤

፭ ፤ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የሚመጡበት ፡ ጊዜና ፡ ሥፍራ ፡ አስተድሞ ፡ የበቃ ፡ መሣሪያ ፡ ሲገኝ ፡ የወንበራን ፡ በር ፡ ከፍተን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በጻፍናቸው ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ እንዲገኙልን ፤

፮ ፤ ወለጋ ፡ አሞሩ ፡ ሆሮ ፡ ይባንቱ ፤ ጉድሩ ፡ ማናቸውም ፡ የሸዋና ፡ የጋላ ፡ ጠረፍና ፡ መሸጋገሪያው ፡ ቅርብ ፡ አማካይ ፡ ስለሆነ ፡ ሕዝቡም ፡ በጠዋትና ፡ በማታ ፡ ስለተገናኘ ፡ የጋላም ፡ ሕዝብ ፡ በቶሎው ፡ የሚሰበክልን ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በጻፍናቸው ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ሲገኙ ፡ ነው ፤

፯ ፤ ከዓባይ ፡ ወዲህ ፡ ማዶ ፡ ላለው ፡ ሕዝብ ፡ የመሣሪያ ፡ ልክ ፡ በክሉ ፡ ውስጥ ፡ ለማለት ፡ በጻፍናቸው ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ተቀምጠን ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ የጋላን ፡ ባላባቶች ፡ ማናቸውንም ፡ ለመሥራት ፡ እንችላለን ፤ እነሱም ፡ ስለቦታ ፡ ቅርበት ፡ በቶሎ ፡ ተረድተው ፡ መሣሪያ ፡ ለመቀበልና ፡ ሥራቸውን ፡ ለመሥራት ፡ ፈቃደኛ ፡ ይሆናሉ ።

፰ ፤ የወንበራ ፡ በር ፡ ከተከፈተ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ለሚፈልጉት ፡ ግንኙነት ፡ ቦታው ፡ ይመቻል ፤

፱ ፡ ጠረፉ ፡ በጌምድር ፡ ይሆናል ፡ ዙሪያውም ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ ይበዛበታል ፡ ልባችን ፡ አይጠጋውም ፡ እንጂ ፡ ደጋ ፡ ዳሞት ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ ልጃምበራ ፡ ያለውም ፡ ኃይል ፡ አለበት ፤ ግን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከጠላት ፡ አልዳኑም ።

፲ ፤ ጠረፋቸው ፡ ለስብከት ፡ የማይመች ፡ ነው ፤

፲፩ ፤ የኛ ፡ ኃይል ፡ የበረታ ፡ እንደሆነ ፡ በጐጃም ፡ ክፍል ፡ እነብሴ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ለሳይንትና ፡ ለቦረና ፡ ለወሎ ፡ ለመንዝ ፡ ጠረፍ ፡ ስለሆነ ፡ ለስብከት ፡ ይመቻል ። ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ አስፈላጊ ፡ የወንበራን ፡ በር ፡ ከፍተን ፡ ኃይላችን ፡ ካልበረታ ፡ እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተቆጠሩ ፡ አገሮች ፡ የሚሰበኩና ፡ የሚያምኑ ፡ አይደሉም ።

፲፪ ፡ ከወንበራ ፡ ወንበርማ ፡ ድረስ ፡ የጉዞ ፡ መንገድ ፤ የስድስት ፡ የሰባት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ነው ፤ ከወንበራ ፡ ሬሳሬስ ፡ ድረስ ፡ የስድስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ነው ። በድምሩ ፡ ከወንበርማ ፡ ሬሳሬስ ፡ ድረስ ፡ የአሥራ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ነው ።

## የደጃዝማች ፡ ነጋሽና ፡ የደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ የስምምነት ፡ ውል ።

በየትንንሹ ፡ ምክንያት ፡ ያለውን ፡ ጠባችንን ፡ ትተን ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ተባብሮ ፡ በመመካከር ፡ ጠላትን ፡ ማጥቃትና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃ ነቷን ፡ የምታገኝበትን ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ ከመካከላችን ፡ የሚገኙ በትን ፡ በስምምነት ፡ እንድንሠራ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መስሎ ፡ ስለታየን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ ስንል ፡ ጠባችን ፡ ቀርቷል ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ወደፊት ፡ ካንዳችን ፡ ወገን ፡ የጦር ፡ አርበኛ ፡ ሆኖ ፡ ሲሠራ ፡ የነበረውንና ፡ አገርም ፡ በአንደኛችን ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ ሲጠብቅ ፡ የቆየውን ፡ በማባበል ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ፈቅዶ ፡ ላንዳችን ፡ ልሁን ፡ ሲል ፡ ስምምነት ፡ የሚያጠፋ ፡ ስለሆነ ፡ እንዳንቀበለው ፡ ቃላችንን ፡ በፊርማችን ፡ እንመሰክራለን ። ይህንንም ፡ ቃል ፡ አፍርሶ ፡ አርበኞቹን ፡ በማባበል ፡ አገርም ፡ በማስከዳት ፡ በፈቃዱም ፡ የወጣውን ፡ የተቀበለና ፡ ይኸንን ፡ ሲሠራ ፡ የተገኘ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ ጠላት ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ያንድነትና ፡ የመተባበር ፡ ኮሚቴና ፡ ሙሴ ፡ ጳውሎስ ፡ ሲያስታርቁን ፡ በሦስት ፡ ቀለም ፡ ባንዲራ ችን ፡ ሥር ፡ ቆመንና ፡ ምለን ፡ ተራርቀን ፡ የፈረምንበት ፡ የስምምነት ፡ ውል ፡ ያፈረሰ ፡ በግርማዊ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ ይጠየቃል ።

## ከአርበኞች ፡ መሪዎች ፡ ጋራ ፡ በደብዳቤ ፡ ግኑኝነት ፡ እንዳደረግሁ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ ከአርበኞች ፡ መሪዎች ፡ ጋር ፡ የደ ብዳቤ ፡ ግንኙነት፡ በሰፊው ፡ አደረግሁ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለአርበኞች ፡ መሪ ዎች ፡ ከጻፍኳቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ ጥቂቶቹን ፡ በሚከተለው ፡ እገልጻለሁ ።

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስ ፤

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ። ከግርማዊ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በግፍ ፡ የወደቀባትን ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ከላይዋ ፡ ለማስወገድና ፡ ነፃነቷን ፡ ለመመለስ ፡ ተሰደው ፡ የነበረበት ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመላቸው ፡ የምሥ



ራቹን ፡ እንድነግራችሁ ፡ ወደ ፡ አርበኞቻቸው ፡ ተልኬ ፡ መጥቻለሁ ። ስለዚሁም ፡ የምንገናኝበትን ፡ አኳኋን ፡ ተነጋግር ፡ እንዲቆየን ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቆየ ፡ ስለሆነ ፡ አቶ ፡ ገብሬ ፡ መታፈሪያን ፡ ልከነዋል ። ማንኛውንም ፡ አኳኋን ፡ እርሱ ፡ ያስረዳችኋል ። እስትገናኛችሁ ፡ እቸኩ ላለሁ ።

ወደልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውና ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ለደጃዝ ማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ ደብዳቤ ፡ በብላታ ፡ ወንድም ፡ እጅ ፡ ልኬ ፡ ነበር ። መድረሱንና ፡ አለመድረሱን ፡ እስካሁን ፡ ስለአላወቅሁት ፡ ማንኛው ንም ፡ አኳኋን ፡ ማወቅ ፡ ስለቸገረኝ ፡ ሥራ ፡ ፈትቼ ፡ እጠብቃለሁና ፡ አስ ጠይቀህ ፡ በቶሎ ፡ እንድትልክልኝ ፡ አደራህን ።

ጥቅምት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፤
እጅጉን ፡ እንደምን ፡ ሰንብተዋል ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ።

ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ተልኬ ፡ ጐጃም ፡ መሬት ፡ እንደገባሁ ፡ የመ ገናኛ ፡ ደብዳቤ ፡ በብላታ ፡ ወንድም ፡ እጅ ፡ ልኬ ፡ ነበርና ፡ መልስ ፡ ባለ ማግኘቴ ፡ ምን ፡ ሆነው ፡ ይሆን ፡ በማለት ፡ እሰባለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ የምን ገናኝበትንም ፡ ሥፍራ ፡ ጠይቄ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ደብዳቤው ፡ እንደደረ ሰዎ ፡ ለኛም ፡ እንዳይርቀን ፡ ለናንተም ፡ እንዳይርቃችሁ ፡ አማካይ ፡ ሥፍራ ፡ ደጋ ፡ ዳሞት ፡ ነው ፡ ስለተባለ ፡ ፈቃድዎ ፡ ሆኖ ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ ተገናኝተን ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሣችን ፡ የተላክሁትን ፡ ዋናውን ፡ ጉዳያችንን ፡ እንድንነጋገርና ፡ ሥራችንን ፡ እንድንሠራ ። ማን ኛውንም ፡ አኳኋን ፡ የምንገናኝበትን ፡ ጊዜና ፡ የሚመጡበትን ፡ ቀን ፡ አስቀድመው ፡ መልሱን ፡ እስቲጽፉልኝ ፡ እጠባበቃለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ብለው ፡ እርስዎ ፡ ባወቁት ፡ ቢጽፉልኝም ፡ ይሆናል ፡ ስል ፡ በማክበር ፡ አስታውቅዎታለሁ ።

ጥቅምት ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ይድረስ ፡ ከክቡር ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፤

እንደምን ፡ ሰንብተዋል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ።

ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ተልኬ ፡ ጐጃም ፡ መሬት ፡ እንደገባሁ ፡ የመገ ናኛ ፡ ደብዳቤ ፡ በብላታ ፡ ወንድም ፡ እጅ ፡ ልኬ ፡ ነበርና ፡ እስካሁን ፡ ሳይ ደርስዎ ፡ አይቀርም ። ነገር ፡ ግን ፡ የምንገናኝበትን ፡ ሥፍራ ፡ ጠይቄ ፡

ስለነበረና ፡ መልስ ፡ ባለማግኘቴ ፡ ምን ፡ ሆነው ፡ ይሆን ፡ በማለት ፡ አስ ባለሁ ። አሁንም ፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ እንደደረሰዎ ፡ ለኛም ፡ እንዳይርቀን ፡ ለናንተም ፡ እንዳይርቃችሁ ፡ አማካይ ፡ ሥፍራ ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ ስለተባለ ፡ ፈቃድዎ ፡ ሆኖ ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ ተገናኝተን ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሣችን ፡ የተላክሁትን ፡ ዋናውን ፡ ጉዳያችንን ፡ እንድንነጋገርና ፡ ሥራ ችንን ፡ እንድንሠራ ። ማንኛውንም ፡ አኳኋንና ፡ የምንገናኝበትን ፡ ጊዜ ፡ የሚመጡበትን ፡ ቀን ፡ አስቀድመው ፡ መልስ ፡ እስቲጽፉልኝ ፡ እጠባበ ቃለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ እርስዎ ፡ በሚያውቁት ፡ እስከዚህ ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ ብለው ፡ቢጽፉልኝም ፡ ይሆናል ፡ ስል ፡ አስታውቃለሁ ።

ጥቅምት ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፤
እጅጉን ፡ እንደምን ፡ ሰንብተዋል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ።

ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ተልኬ ፡ ጐጃም ፡ መሬት ፡ ስደርስ ፡ እንደጎ ባሁ ፡ ረጅም ፡ ደብዳቤ ፡ በብላታ ፡ ወንድም ፡ እጅ ፡ ልኬ ነበርና ፡ እስካ ሁን ፡ ሳይደርስዎ ፡ አይቀርም ።

ነገር ፡ ግን ፡ የምንገናኝበትን ፡ ሥፍራ ፡ ጠይቂ ፡ ስለነበረና ፡ መልስ ፡ ባለማግኘቴ ፡ ምን ፡ ሆነው ፡ ይሆን ፡ በማለት ፡ ሰግቻለሁ ። አሁንም ፡ ደብዳቤው ፡ እንደደረሰዎ ፡ ፈቃድዎ ፡ ቢሆን ፡ የምንመካከረው ፡ የሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ስላለ ፡ ደጋ ፡ ዳሞት ፡ ፈታውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ድረስ ፡ብንገናኝ ፡ ለሥራችን ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ፡ ስል ፡ በማክበር፡ እስ ታውቃለሁ ።

ጥቅምት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ በቀለ ፡ አምባዬ ፤

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ።

ካሁን ፡ በፊት ፡ አቶ ፡ አስጋኸኝ ፡ አርአያን ፡ ልኬብህ ፡ እንደነበ ረው ፡ ከግርማዊ ፡ ዘንድ ፡ ተልኬ ፡ የመጣሁበትን ፡ አንዱ ፡ ዋና ፡ ሥራዬ ፡ ባርበኞቻቸው ፡ ሁሉ ፡ መሐከል ፡ አንድነት ፡ የሚገኝበትን ፡ ሥራ ፡ አጥ ብቄ ፡ እንድሠራ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ በደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጠብ ፡ አጥርቼ ፡ ብጠይቅ ፡ ጠቡ ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘሁት ፡ ይህንን ፡ ጠብ ፡ ለማብረድ ፡ ከፊታውራሪ ፡ አልማውና ፡ ከፊታውራሪ ፡ ዘለቀ ፡



ጋራ ፡ እመጣለሁና ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ እንደጻፍኩልህ ፡ ደብዳቤ ፡ ከጠብ ፡ ታግሠህ ፡ እንድትቆይና ፡ የምንገናኝበትን ፡ አቅራቢያ ፡ ቦታ ፡ በቶሎ ፡ እንድትጽፍልኝ ። የምንገናኝበትም ፡ ሥፍራ ፡ በአዛዥ ፡ ተሰማ ፡ በኩል ፡ እመጣለሁ ፡ ብለህ ፡ ልከህብኝ ፡ እንደነበረው ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ነው ። ሌላ ፡ ብርቱ ፡ ሥራ ፡ ስላለብኝ ፡ ጊዜ ፡ እንዳታሳልፍብኝ ፡ እኔም ፡ እየመ ላለስኩ ፡ የምጽፍልህ ፡ ምንም ፡ ባንተዋወቅ ፡ መልካም ፡ አገልግሎትህን ፡ ሰምቼ ፡ ነበርና ፡ የድካምህን ፡ ዋጋ ፡ በምታገኝበት ፡ ሰዓት ፡ እክል ፡ እን ዳያገኝህ ፡ ስል ፡ ነው ። ለራስህ ፡ ስል ፡ ነውና ፡ አስብበት ።

ጥቅምት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ቀኛዝማች ፡ ዘለቀ ፡ አስጌ ፤

ከልጅ ፡ ገሠሠ ፤ ከልጅ ፡ ደምለው ፤ ከልጅ ፡ አብርሃም ፡ እንደምን ፡ ሰን ብታችኋል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ።

ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በግፍ ፡ የወደቀባትን ፡ ቀንበር ፡ ከላይዋ ፡ አስወግዶ ፡ ነፃነ ቷን ፡ እንደነበረ ፡ ለመመለስ ፡ ተሰደው ፡ የነበረበት ፡ ጉዳይ ፡ ስለተፈጸ መላቸው ፡ የምሥራቹን ፡ እንድነግራችሁ ፡ ወደአርበኞቻቸው ፡ ተልኬ ፡ መጥቻለሁ ። ለዚሁም ፡ የምንገናኝበትን ፡ አማካይ ፡ ሥፍራ ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ስለተባለ ፡ በመጣን ፡ ጊዜ ፡ እዚያው ፡ ድረስ ፡ መጥታችሁ ፡ እንድንገናኝ ፡ አስታውቃችኋለሁ ። እስትንገናኝ ፡ እቸኩላለሁ ።

ጥቅምት ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፤

የማክበር ፡ ሰላምታዬን ፡ አቀርባለሁ ።

ጉታ ፡ ስደርስ ፡ ያገኘሁትን ፡ ወሬ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ መስ መር ፡ አስታውቃለሁ ።

፩ኛ/ ዳንግላ ፡ ያለው ፡ ኢጣልያ ፡ ኰሎኔል ፡ ቶሊሪ ፡ የሚባለው ፡ ስለወጣ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አስከብበው ፡ ይዋጋሉ ። የተጀመረውም ፡ ጥቅምት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ነው ።

፪ኛ/ ስለመጣው ፡ መሣሪያ ፡ ፊታውራሪ ፡ አደገ ፡ እንግዳና ፡ ፊታው ራሪ ፡ የኔ ፡ ታዘዋል ። መሣሪያው ፡ እስካሁን ፡ አልደረሰም ።

፫ኛ/ አሁን ፡ ለርስዎ ፡ የማሳስብዎ ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ዳንግላ ፡ እንዳያልፍ ፡ በርስዎም ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ አርበኞች ፡ እንደዚሁ ፡ እንዲሠሩ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ሁለተኛ ፡ ከቡሬ ፡ ጦር ፡ መጥቶ ፡ ያለፈ ፡ እንደሆነ ፡ ያለም ክንያት ፡ ስምዎ ፡ እንዳይነሳ ፡ አደራዎን ። እኔም ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ መንገሻ ፡ ልሄድ ፡ ነው ።

ጥቅምት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
አባቸ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፤
የማክበር ፡ ሰላምታዬን ፡ አቀርባለሁ ።

ኰሎኔል ፡ ቶሬሊ ፡ የሚባለው ፡ ዳንግላ ፡ ያለው ፡ የኢጣልያ ፡ ጦር ፡ መውጣቱንና ፡ እርስዎም ፡ አስከብበው ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ መጀመርዎን ፡ አቶ ፡ ጊላ ፡ ነገሩን ። እኛም ፡ ወደፊት ፡ ስለምንሠራው ፡ ሥራ ፡ ለመነጋገር ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጭምር ፡ ነገ ፡ ጥቅምት ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እር ስዎ ፡ እንመጣለንና ፡ ያሉበትን ፡ የሚመራን ፡ ሳንጌ ፡ እድንበሩ ፡ ድረስ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሰው ፡ እንዲልኩልን ፡ በማክበር ፡ አስታውቅዎታለሁ ።

ጥቅምት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
አባቸ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፤
የማክበር ፡ ሰላምታዬን ፡ አቀርባለሁ ።

፩ኛ/ መሣሪያ ፡ ሊአመጡ ፡ ከሄዱት ፡ ሹሞችዎ ፡ ግራዝማች ፡ በዛብህ ፡ ከ፴ ፡ ብረት ፡ ጋር ፡ መድረሱን ፡ ነግሮኛል ፡ ቀሪውም ፡ ብረት ፡ አቸፈር ፡ መሬት ፡ ሳይደርስ ፡ ያልቀረ ፡ መሆኑን ፡ ነገረኝ ። ስለዚህም ፡ ከደጃዝ ማች ፡ መንገሻ ፡ ተነጋግሬ ፡ የኛም ፡ የቀረ ፡ አለና ፡ ባንድነት ፡ እስከዚህ ፡ እንዲመጣ ፡ ለፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ እልካለሁ ፡ ብለዋል ።

፪ኛ/ አልፎንሶ ፡ ወደ ፡ ጃንሆይ ፡ እንዲሄድ ፡ ትእዛዝ ፡ መኖሩን ፡ ነግሬዎ ፡ እሺ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እንዲሰናዳ ፡ እናደርጋለን ፡ ብለውኝ ፡ ስለነበረ ፡ የሚወስደው ፡ አቶ ፡ አሰጋኸኝ ፡ አርአያ ፡ ስለሆነ ፡ ተነጋግሮ ፡ እንዲያመጣው ፡ ልኬዋለሁ ።

፫ኛ/ ስለቀረው ፡ ጓዛችን ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ፳ ፡ አጋሰስ ፡ ስለ ረዱን ፡ ከርስዎ ፡ ቢገኝ ፡ ይህንኑ ፡ ያህል ፤ ባይገኝ ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አም ስት ፡ አጋሰስ ፡ እንዲረዱንና ፡ ዕቃውን ፡ ካመጣ ፡ በኋላ ፡ እንመልሳለን ፡ አደራዎን ።



፬ኛ/ ምናልባት ፡ ስለቀረው ፡ መሣሪያ ፡ ተቀባይና ፡ አምጭ ፡ ይልኩ ፡ እንደሆነ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ከአቶ ፡ አሰጋኸኝ ፡ ጋር ፡ ሄዶ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ከእኛ ፡ ጓዝ ፡ ጋር ፡ ይመጣል ። ሁሉንም ፡ አቶ ፡ አሰጋኸኝ ፡ ይነግርዎ ።

ጥቅምት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
አባቸ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ይድረስ ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፤
የማክበር ፡ ሰላምታዬን ፡ አቀርባለሁ ።

በርስዎና ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ ተደርጎ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችሁ ፡ በመመካከርና ፡ በስምም ነት ፡ እንዲሠራ ፡ ተነጋግረን ፡ ስለነበረና ፡ የቀጠሮው ፡ ቀን ፡ በሥራ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ተላለፈ ፤ አሁን ፡ ሁለተኛ ፡ ቀጠሮ ፡ ያደረግነው ፡ ጥቅ ምት ፡ ፲፬ ፡ ሐሙስ ፡ ዕለት ፡ ሆኖዋልና ፡ ፈቃድዎ ፡ ሆኖ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ አሸፋ ፡ ጉንድል ፡ ድረስ ፡ እንዲመጡ ፡ በማክበር ፡ አስ ታውቃለሁ ።

ጥቅምት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
አባቸ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡


ፊታውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ፍላቴ ፡ (ደጃዝማች) ።

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ ኢየሱስ ፤

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ።
ጥቅምት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ በጥቅምት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ደረሰኝ ፤

አንድነት ፡ ጠቃሚ ፤ መለያየትና ፡ አለመስማማት ፡ ጉዳት ፡ መሆኑን ፡ አቶ ፡ ገብሬን ፡ በቃል ፡ ልኬው ፡ የነበረው ፡ ሐሳብ ፡ በቶሎ ፡ ገብቶህ ፡ እሺ ፡ ስላልከኝ ፡ ከልብ ፡ አመሰግናለሁ ። በውነትም ፡ የአገሩን ፡ ነጻነትና ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥቱን ፡ በቶሎ ፡ ለማየት ፡ የሚጓጓና ፡ የሚጣደፍ ፡ ሁሉ ፡ ያለፈ ፡ መልካም ፡ ታሪኩን ፡ ጠብቆ ፡ መቆየትና ፡ ያለምንም ፡ ቅሬታ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥቱን ፡ እንዲያገኝ ፡ እርግጥ ፡ ነውና ፡ በዚሁ ፡ ሥራህ ፡ እንድትገፋበት ፡ እያሳሰብኩ ፡ አደራ ፡ እልሃለሁ ።

ጥቅምት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
አባኙ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንዲሁ ፡ በጐጃምና ፡ በሌላም ፡ ስፍራ ፡ የሚገኙት ፡ አርበኞች ፡ ሁሉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በርትተው ፡ እንዲሠሩና ፡ ጠላትን ፡ በያለበት ፡ እንዲወጉት ፡ በማሳሰብ ፡ ለታወቁት ፡ አርበኞች ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፍሁላቸው ።

ከጻፍኩላቸውም ፡ ውስጥ ፡ ያንዳንዶቹ ፡ ስም ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

| | |
|---|---|
| ልጅ ፡ ደምሴ ፡ ዓለማየሁ ፡ | ፊታውራሪ ፡ አያሌው ፡ መኰንን ፡ |
| ልጅ ፡ ተፈራ ፡ | ቀኛዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ ፡ |
| አቶ ፡ ገብሬ ፡ መታፈሪያ ፡ | ፊታውራሪ ፡ ሞገስ ፡ |
| ቀኛዝማች ፡ የኋላው ፡ | አባኙ ፡ ቦጋለ ፡ ገብረወልድ ፡ |
| ቀኛዝማች፡ ሽፈራው፡ ረታ | ፊታውራሪ፡ መኰንን፡ ሽፈራው ፡ |
| ፊታውራሪ ፡ ዘለቀ፡ ደስታ ፡ | ባላምባራስ ፡ ገሠሠ ፡ ረታ ፡ |
| ልጅ ፡ አያሌው ፡ ደስታ ፡ | ግራዝማች ፡ ጉብና ፡ |
| ፊታውራሪ ፡ ኃይሉ፡ እምሩ ፡ | ልጅ ፡ ወርቁ ፡ አየለ ፡ |
| ልጅ ፡ ዓለማየሁ ፡ ተድላ ፡ | ፊታውራሪ ፡ በቀለ ፡ ካሣ ፡ |
| ባላምባራስ ፡ አያሌው፡አሰጌ ፡ | ባሻ ፡ ተገኘ ፡ ብሩ ፡ |
| ባላምባራስ፡አራጋው፡አሰጌ ፡ | ባሻ ፡ አይሸሹም ፡ |
| ቀኛዝማች ፡ መንገሻ፡አሰጌ ፡ | ቀኛዝማች ፡ ካሣ ፡ ጥቁሬ ፡ |
| ባላምባራስ፡ተክለአብ፡ቢሰጥ፡ | ቀኛዝማች ፡ አድማሱ ፡ |
| አቶ፡መኰንንና፡ልጅ፡እንግዳ፡ | ፊታውራሪ ፡ ታዬ ፡ |

ከአርበኞች ፡ ዘንድ ፡ ማንኛውንም ፡ የአገር ፡ ሁናቴ ፡ የሚገልጽ ፡ ደብዳቤ ፡ የቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ፖስተኛ ፡ እንደሚያመላልሰው ፡ በሰንጣቃ ፡ እንጨት ፡ እየተጣበቀ ፡ በግልጽ ፡ እንዲታወቅ ፡ እየሆነ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ድንኳን ፡ በየዕለቱ ፡ ይደርስ ፡ ጀመረ ። እኔም ፡ የግል ፡ ሥራዬ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽና ፡ በማስረዳት ፡ የሚመጡልኝን ፡ ደብዳቤዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡



አስቸኳይነታቸው ፡ እየተመለከትሁ ፡ በቅደም ፡ ተከተሉ ፡ ተራ ፡ እየሰጠሁ ፡ መልሱን ፡ እኔው ፡ እየጻፍሁ ፡ ለመጣው ፡ መላክተኛ ፡ ደብዳቤውን ፡ እየሰጠሁት ፡ ይመለስ ፡ ጀመረ ። ለእኔም ፡ የተጻፉ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ያላያቸውና ፡ መልስም ፡ በምሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ከማንም ፡ ሳላማክር ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አሠራር ፡ በቶሎ ፡ ከአርበኞች ፡ ጋራ ፡ በደብዳቤ ፡ መገናኘቴን ፡ ይመለከቱ ፡ የነበሩት ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ሥራችን ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ደብዳቤ ፡ መምጣቱንና ፡ ከዚህም ፡ መልስ ፡ ተሰጥቶት ፡ ይዞ ፡ መሄዱን ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ ምን ፡ እንደመጣ ፡ ከዚህም ፡ ምን ፡ መልስ ፡ እንደተሰጠ ፡ ባለማወቃቸው ፡ ሳይቸገሩ ፡ አልቀሩም ። ለጊዜው ፡ አንድና ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ቢታገሱም ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ የአርበኞቹ ፡ የደብዳቤ ፡ ግንኙነት ፡ ሥራው ፡ እየቀጠለ ፡ ስለሄደ ፡ በነገሩ ፡ አስበውበት ፡ ኖሮ ፡ የሦስት ፡ የአራት ፡ ቀን ፡ በቴሌግራም ፡ የተላለፈ ፡ ወሬ ፡ ይዘው ፡ ከአቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ወደኔ ፡ ድንኳን ፡ መጡና ፡ ወሬውን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ይነግሩኝ ፡ ጀመር ።

እኔም ፡ በነገሩ ፡ እየተገረምሁ ፡ በትዕግሥት ፡ ሳዳምጥ ፡ ወሬውን ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ እኛ ፡ የምንሠራውንና ፡ አንተ ፡ የምትሠራውን ፡ እየተመካከርን ፡ ተግባብተንና ፡ ተዋውቀን ፡ ብንሠራ ፡ ጠቃሚ ፡ ነውና ፡ እኛም ፡ ያገኘነውን ፡ እንነግርሃለን ፡ አንተም ፡ ያገኘኸውን ፡ እንድታሳየን ፡ ሲሉ ፡ በራሳቸው ፡ አሳቢነት ፡ ጠየቁኝ ፡ እኔም ፡ ቀድሞውንም ፡ አንተ ፡ ለብቻህ ፡ ሥራ ፡ እኛም ፡ ለብቻችን ፡ እንሠራለን ፡ ብትሉኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ካቀረባችሁኝና ፡ ካማከራችሁኝ ፡ አማክራችኋለሁ ፡ ብዬ ፡ መልስ ፡ ሰጠኋቸውና ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ መቀራረብ ፡ ደረሱ ። ይኸውም ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ የፖለቲካ ፡ መቀራረብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የልብ ፡ ግንኙነት ፡ እንደሆን ፡ የተቋረጠው ፡ በመጀመሪያ ፡ ንግግራቸው ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

## ዶጋ ፡ ዳሞት ፡ ካርበኞች ፡ መሪዎች ፡ ጋራ ፡ ስለመገናኘቴ ።

ካፒቴን ፡ ክርቺሌ ፡ የተባሉ ፡ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ የቅርብ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ የመጡት ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ ጠንካራና ፡ ብርቱ ፡ ሐሳብ ፡ ያላቸው ፡ ወጣት ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ፡ ብለን ፡ስንመለከታቸው ፡ እኛን ፡ ሳያውቁን ፡ እናውቃቸዋለን ፡ ከሚሉት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በመሆናቸው ፡ እንደአሰብናቸው ፡ ግምት ፡ አድርገው ፡ የሠሩ ፡ አይመስለኝም ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ ከዓይነተኛው ፡ መንገድ ፡ መሪያቸው ፡ ቢያሳስቷቸውና ፡ ባያስሩዋቸውም ፡ የተፈጥሮ ፡ ጥንካሬያቸውን ፡ ሳልናገረው ፡ አላልፍም ። እኚህ ፡ መኰንን ፡ ከገዳሪፍ ፡ ተነስተን ፡ ዳሞት ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ እስከንቀሳቀል ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ እበቅሎ ፡ ላይ ፡ ሳይወጡ ፡ በእግራቸው ፡ ረጅም ፡ ዘንግ ፡ ብቻ ፡ ጓደኛ ፡ አድርገው ፡ የዘለቁ ፡ ናቸው ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ከዳሞት ፡ በበላያ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ተመልሰው ፡ ያዩትንና ፡ የሰሙትን ፡ አስረድተው ፡ ወዲያው ፡ ተመልሰው ፡ በቀድሞው ፡ ሥራቸው ፡ ላይ ፡ ቆዩ ፤

ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድና ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ጐጃም ፡ ሄደን ፡ ከየአርበኞቹ ፡ ለመገናኘት ፡ ጉዞአችንን ፡ ቀጥለን ፡ በመጀመሪያ ፡ የዶጋ ፡ ዳሞት ፡ አርበኞች ፡ መሪ ፡ የሆኑትን ፡ ፊታውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ ኢየሱስ፡ ፍላቴን ፡ አገኘንና ፡ ረጅም ፡ የሥራ ፡ ንግግር ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፡ ወደፊት ፡ ጉዞዋችንን ፡ ቀጠልን ፤ ወዲያው ፡ ቢቡኝ ፡ በተባለው ፡ ቀበሌ ፡ የሚገኙ ፡ አርበኛ ፡ ልጅ ፡ ደምሴ ፡ ዓለማየሁ ፡ የተባለውን ፡ አገኘንና ፡ እንደዚሁ ፡ ለወደፊት ፡ ሥራችን ፡ የሚጠቅሙ ፡ ጉዳዮች ፡ ከተነጋገርን ፡ በኋላ ፡ ጉዞዋችንን ፡ ቀጠልንና ፡ አበያ ፡ የሚባለውን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግረን ፡ ለሞጣ ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነ ፡ ቀራንዮ ፡ ከተባለ ፡ ደብር ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ስንደርስ ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውን ፡ ካርበኞቻቸው ፡ ከነቀኛዝማች ፡ ሽፈራው ፡ ረታ ፡ ቀኛዝማች ፡ አበሻ ፡ ጀሌ ፤ ከልጅ ፡ ደበበ ፡ ወዳጄ ፡ ጋራ ፡ አገኘንናቸው ፡ እንደተለመደውም ፡ ያንኑ ፡ የሥራና ፡ የአሠራር ፡ ሁናቴ ፡ ተነጋግረን ፡ እንደገና ፡ ተመልሰን ፡ ለመነጋገር ፡ ቀጠሮ ፡ አደረግንና ፡ ወደፊት ፡ ጉዞአችንን ፡ ቀጠልን ። እነማይ ፡ መንግሥቶ ፡ ከተባለ ፡ ቀበሌ ፡ ስንደርስ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀን ፡ አገኘን ። እርሳቸውም ፡ ካዩናቸው ፡ አርበኞች ፡ ሁሉ ፡ በብዛት ፡ እጅግ ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የአርበኞች ፡ ሰልፍ ፡



ከጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አሳዩን ፤ ስለደስታም ፡ ስንገናኝ ፡ የመትረየስ ፡ ግባት ፡ ተኩስ ፡ ይተኰስ ፡ ነበር ።

በአቀባበላቸውም ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አሰኝተው ፡ ተቀበሉንና ፡ ለሥራ ፡ ጉዳይ ፡ በምንነጋገርበት ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ወደ ፡ ባላገርነቱ ፡ ስለሚአደሉ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መልስ ፡ ሊሰጡን ፡ አልቻሉም ፤ ይልቁንም ፡ ተኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ለመነጋገር ፡ ያንኑ ፡ ጣልያኑን ፡ ነው ፡ የሚመስሉት ፡ በማለት ፡ በማመን ፡ የማያነጋግሩዋቸው ፡ ሆኑ ። ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድም ፡ በንግግር ፡ ባለመጣጣማቸው ፡ ሊቆዩ ፡ አልፈለጉም ። ወደ ፡ ኋላ ፡ ትተነው ፡ ከመጣነው ፡ ስፈራችንም ፡ አስቸኳይ ፡ የሆነ ፡ ቴሌግራም ፡ ስለደረሳቸው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለሱ ፡ ሆነ ። እኔ ፡ ግን ፡ ባላገርና ፡ አውሬነት ፡ ያለውን ፡ አርበኛ ፡ አላምዶ ፡ ለማነጋገር ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ ጋር ፡ ሆነን ፡ ቀረን ። ነገሩንም ፡ በማለዘብ ፡ ባላገሩ ፡ አርበኛ ፡ ነገሩ ፡ ገብቷቸው ፡ ምክሩን ፡ እንዲቀበሉ ፡ አደረግን ።

## ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተላከ ፡ የሥራ ፡ መግለጫ ፡ ራፖር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የሥራ ፡ መግለጫ ፡ ራፖር ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ላክሁ ።

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፤

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ አስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኩ ባሪያዎ ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤ ጐጃም ፡ መሬት ፡ እንደደረስን ፡ የተሠራውንና ፡ ያየነውንም ፡ የመሰለንንም ፡ በዝርዝር ፡ ጽፌ ፡ መስከረም ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ የላክነው ፡ ፖስታ ፡ እስካሁን ፡ ከግርማዊነትዎ ፡ ዘንድ ፡ ይደርሳል ፡ ስል ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ የማመለክተው ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ያለውን ፡ ነው ፤

፩ኛ/ በደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህና ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ጠብ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አምላክ ፡ ረድቶኝ ፡ በስምምነት ፡ በመቅረቱ ፡ ሥራችንን ፡ በመመካከር ፡ እንሠራለን ፤ የኛን ፡ ጠብ ፡ ስለንጉሡ ፡ ነገሥታችንና ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ስንል ፡ ትተነዋል ፡ ብለው ፡ በሶስት ፡ ቀለም ፡ ባንዲራችን ፡ ሥር ፡ ቆመው ፡ በመሐላ ፡ ተራርቀዋል ፤ ሁለቱም ፡ ባንድነት ፡ የፈረሙበትን ፡ የእርቅ ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋራ ፡ ልኬዋለሁ ፤

፪ኛ/ ጥቅምት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ በሚጫ ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ በኩል ፤ ከቡሬ ፡ በደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በኩል ፤ ወጥቶ ፡ ግጭት ፡ አድርጎ ፡ አርበኞችዎ ፡ ተታኩሰው ፡ የሚጠብቁትና ፡ የሚያስቀሩት ፡ ቢሆን ፡ እንዳይከታተሏቸው ፤ ፫ ጊዜ ፡ አውሮፕላኖች ፡ መጥተው ፡ የኛን ፡ አርበኞች ፡ በቦምብ ፡ እያስፈራሩ ፡ የወጣውን ፡ ጦሩን ፡ ከቦ ፡ እምሽጉ ፡ አገባ ፤ እኔ ፡ እንደተመለከትኩትና ፡ እንደመሰለኝም ፡ የምናገኘው ፡ እር ዳታ ፡ ጠመንጃ ፡ ጥይት ፡ ብቻ ፡ እንደሆነና ፡ በሰማይ ፡ የሚአንጃብብ ፡ እርዳታ ፡ እናገኝ ፡ እንደሆን ፡ እንዲሁ ፡ እንደተፋጠጥን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከመጨረስ ፡ በስተቀር ፡ የምናተርፈው ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ፤ መድፍና ፡ መትረየስ ፡ ጠመንጃና ፡ ጥይት ፡ በፊትም ፡ ነበረን ። ድል ፡ ለመሆን ፡ የደረስንበት ፡ አውሮፕላን ፡ በማጣት ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ አሁንም ፡ በዚያው ፡ ዓይነት ፡ እንዳይሆን ፡ ይታሰብበት ፤

፫/ በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ የሞተና ፡ የቆሰለውን ፡ ዝርዝር ፡ የሚያ መለክት ፡ ከሁለቱም ፡ ደጃዝማቾች ፡ ያገኘሁትን ፡ ማስታወቂያ ፡ ከዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋራ ፡ ልኬዋለሁ ።

፬ኛ/ ከግርማዊነትዎ ፡ እንደተቀበልኩት ፡ ማስታወሻ ፡ ለብዙ ፡ ሰው ፡ ስንቅ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እንዲቆይ ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ቸገረ ፡ ምንም ፡ መሥራት ፡ አልቻልኩም ፤ ስለዚህ ፡ ገንዘብ ፡ በቶሎ ፡ የሚገባበትን ፡ መንገድ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ አጥብቀው ፡ እንዲያስቡበት ፡ አስታውሳለሁ ፤

፭ኛ/ ከበጌምድር ፡ የመጣ ፡ መላክተኛ ፡ ስላገኘሁ ፡ የግርማዊነት ዎን ፡ አዋጅ ፡ የኔን ፡ ደብዳቤ ፡ እየጨመርኩ ፡ ልኬዋለሁ ፤ አጋፋሪ ፡ ያረ ጋልን ፡ ግን ፡ ወደኛው ፡ እንዲመጡ ፡ ጽፌላቸውአለሁ ።

፮ኛ/ እስካሁን ፡ በደጃዝማች ፡ ነጋሽና ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ስናስተካክል ፡ ነው ፡ የቆየነው ። አሁን ፡ ግን ፡ የሁለቱ ፡ ጉዳይ ፡ በሰላም ፡ ስላለቀልኝ ፡ ሁለቱ ፡ እየተመካከሩ ፡ ይሠ ራሉ ፤ በማለት ፡ ተስፋ ፡ ስላደረግሁ ፡ ከዚሁ ፡ ሰሞን ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውና ፡ ወደልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ መሄዴ ፡ ነው ። በዚያውም ፡ በኩል ፡ መልክተኛ ፡ ባገኝ ፡ ወደሸዋ ፡ ክፍል ፡ ለመላላክ ፡ አስባለሁ ፤

፯ኛ/ ወለጋ ፡ ጉድሩ ፡ ያሉ ፡ ባላባቶች ፡ የኛና ፡ የመሳሪያውን ፡ ጉዳም ፡ መግባት ፡ ስለሰሙ ፡ ሽፍተው ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ይዋጋሉ ፤ ስንገባም ፡ ከዚያው ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ይሠራ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ ስለ ፡ ነገረኝ ፤ ወዲያው ፡ አከታትዬ ፡ የግርማዊነትዎን ፡ አዋጅና ፡ አስፈላጊ ፡ እንደመ ሰለኝ ፡ የኔንም ፡ ደብዳቤ ፡ እየጨመርኩ ፡ ጽፌአለሁ ፤



፰ኛ/ ከዚሁ ፡ አስከትዬ ፡ ስለወለጋ ፡ ልሠራ ፡ ያሰብኩት ፡ ደጃዝ ማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ ፡ የኖሩበት ፡ አገር ፡ ስለሆነ ፡ ላንድ ፡ ጊዜ ፡ እስኪ ገቡ ፡ ከጐጃም ፡ አርበኞች ፡ የኃይል ፡ እርዳታ ፡ ጠይቄ ፡ እንዲያስገቧቸ ውና ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ላላው ፡ አገር ፡ ከሳቸው ፡ ጋራ ፡ ለመሥራት ፡ ነው ፤ ለጊዜው ፡ ለመግባት ፡ ቢሰጉ ፡ እንኳ ፡ ባቅራቢያ ፡ ያሉት ፡ ባላባቶች ፡ እንዲያኖሩዋቸውና ፡ እዚያው ፡ በቅርብ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠሩም ፡ አስቤአለሁ ፤ በሁለተኛው ፡ ፖስታ ፡ ስለወለጋ ፡ የሚሆ ነውን ፡ ሁሉ ፤ አጥርቼ ፡ እጽፋለሁ ።

፱ኛ/ አሁን ፡ የምንሠራው ፡ ለጊዜው ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የታየንን የጠላት ፡ ጦር ፡ ካንዱ ፡ ምሽግ ፡ እየለቀቀ ፡ ወዳንድ ፡ ምሽግ ፡ እየተደረበ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ኃይሉን ፡ ለማበርታት ፡ ስለሆነ ፡ ሐሳቡ ፡ ይኸን ፡ እንዳያ ደርግ ፡ ለማድረግ ፡ ምሽግ ፡ ባለበት ፡ አቅራቢያ ፡ የሆኑትን ፡ አርበኞች ፡ ተኩሎኤል ፡ ሳንድፎርድ ፡ የተገኘውን ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ እያስተላለፍኩ ላቸው ፡ እንደዚሁ ፡ ሊሠራ ፡ ነው ፤

፲ኛ/ ባንዳ ፡ የሆነው ፡ ሕዝብ ፡ በየአቅራቢያ ፡ ዘመዱ ፡ ተቀበሉኝ ፡ እመንገድ ፡ ሽፍታ ፡ እንዳይገለኝ ፡ እያለ ፡ መላላክ ፡ ጀምሯል ።

፲፩ኛ/ መልካም ፡ ለሠራ ፡ የሚሰጥ ፡ ሽልማት ፡ ባመለመኖሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጠመንጃም ፡ ሌላም ፡ ለሽልማት ፡ የሚሆን ፡ ዕቃ ፡ ይዘን ፡ ቢሆን ፡ ለሥራችን ፡ መልካም ፡ ረዳት ፡ ይሆነን ፡ ነበር ፤ እኔም ፡ ከግርማ ዊነትዎ ፡ ስለይ ፡ በተቀበልኩት ፡ ማስታወሻ ፡ ላይ ፡ አንብቤ ፡ ስለነበረ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ የተዘጋጀ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ። ከተነሳሁ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ብመለከተው ፡ እንኳን ፡ ለሰው ፡ ልንተርፍ ፡ ለራሳችንም ፡ መጠበቂያ ፡ ጐድሎ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ለወደፊቱ ፡ የሽልማት ፡ ነገር ፡ አጥ ብቆ ፡ ይታሰብበት ፡ ስል ፡ አመለክታለሁ ።

ጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
ያለሐኪት ፡ ባሪያዎ
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

በልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውና ፡ በልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ መሐከል ፡ ጠብ ፡ ተነስቶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተዋግተው ፡ ሁለተኛ ፡ ለመዋጋት ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ይፈላለጉ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እንዲታረቁና ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ለመዋጋት ፡ መፈላለጋቸው ፡ ቀርቶ ፡ በመተባበር ፡ ጠላት ፡ እንዲያጠቁ ፡ የስምምነት ፡ ውል ፡ ሁለቱ ፡ ተፈላላጊዎች ፡ ተገናኝተው ፡ እንዲፈራረሙና ፡ እርቁ ፡ በመሐላ ፡ ሐሳብ ፡ ቀርቦ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሐሳቡን ፡ ተቀበሉት ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ ግን ፡ ኬጂ ፡ ጠብ ፡ ፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አልወጋውም ፡ ከጠላት ፡ በሚከራከርበት ፡ ጊዜ ፡ እረዳዋለሁ ፡

እንጂ ፡ ተደራቢ ፡ ሆኜ ፡ እንዲጠቃ ፡ አላደርግም ፤ ስለአገሩ ፡ ክፍያ ፡ ግን ፡ አንተ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መላክተ ኛና ፡ ሠራተኛ ፡ በመሆንህ ፡ በትእዛዝ ፡ ከምታደርገው ፡ በስተቀር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አገር ፡ ተካፍዬ ፡ አልታረቅም ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ስለሰጡኝ ፡ ተገና ኝተው ፡ መነጋገርና ፡ የአገሩ ፡ ክልል ፡ በስምምነት ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በትእዛዝ ፡ ሲፈጸም ፡ በሌላው ፡ ነገር ፡ ተባብሮ ፡ ጠላት ፡ ለማጥቃት ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ የጦር ፡ አደጋ ፡ የወደቀበት ፡ እንደሆነ ፡ ሊረዳዱ ፡ ቃል ፡ መግባታቸውን ፡ የሁለቱ ፡ ተስማሚዎች ፡ የሐሳብ ፡ ስጭውም ፡ ፊርማ ፡ ተፈርሞ ፡ ለሁለቱም ፡ ተሰጥቶ ፡ አንድ ፡ ኮፒ ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ እንዲቀር ፡ ተደረገና ፡ ከምሥራቅ ፡ ጐጃም ፡ ቢሮ ፡ ወደ ፡ አቆምንበት ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ጐጃም ፡ ዳሞት ፡ መመለስ ፡ ሆነ ፤ ለልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለ



ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ (ራስ) ።

ውና ፡ ለልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ የተሰጠው ፡ የስምም ነትና ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ ቃሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ተጽፎአል ።

እኔ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተልከው ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ እንዳ ንጣላና ፡ ለሀገር ፡ ጉዳት ፡ እንዳናመጣ ፡ ለጠላትም ፡ ምቹ ፡ እንዳንሆን ፡ በአንድነት ፡ ተባብረን ፡ እንድናጠቃ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምክር ፡ ስለመ ከሩኝ ፡ እንደዚሁም ፡ በልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውና ፡ በእኔ ፡ መሐከል ፡ ስላ ለው ፡ ጠብ ፡ እንድንታረቅ ፡ ስለጠየቁኝ ፡ የርስ ፡ በርሳችን ፡ ጠብ ፡ ጉዳት ፡



እንጂ ፡ ጥቅም ፡ እንደሌለው ፡ ስለተረዳሁት ፡ እሺ ፡ እታረቃለሁ ፡ ስል ፡ ሐሳቤን ፡ አጸናለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በመሐከላችን ፡ ጠብ ፡ የሚያስነሳው ፡ የሌባ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ ከርሳቸው ፡ አገር ፡ ክፍል ፡ መጥቶ ፡ ከእኔ ፡ ክፍል ፡ አገር ፡ ከብት ፡ እንዳይነዳ ፡ ከእኔም ፡ አገር ፡ ከብት ፡ ሰርቆ ፡ ወደ ፡ እሳ ቸው ፡ አገር ፡ ቢገባ ፡ ሳይቀበሉ ፡ አሳልፈው ፡ ሊሰጡ ፤ እኔም ፡ ከምገ ባበት ፡ ክፍለ ፡ አገር ፡ ወደሳቸው ፡ አገር ፡ ክፍል ፡ ሌባ ፡ ሂዶ ፡ ከብት ፡ እንዳይነዳ ፤ ከእርሳቸውም ፡ አገር ፡ ክፍል ፡ ከብት ፡ ተሠርቆ ፡ ቢመጣ ፡ ሳልቀበል ፡ አሳልፌ ፡ ልሰጥ ።

ሁለተኛ ፡ ባንዳም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የኢጣልያን ፡ ጦር ፡ ቢመጣ ፡ በርሳቸው ፡ ላይ ፡ መጥቶ ፡ ለእርዳታ ፡ ቢጠሩኝ ፡ ሂጄ ፡ ልረዳና ፡ በእኔም ፡ ላይ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ቢመጣ ፡ በላኩባቸው ፡ ጊዜ ፡ መጥተው ፡ ሊረዱኝ ፤

ሶስተኛ ፡ በጠቅላላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃነቷን ፡ የምታገኝበትንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚ ገቡበትን ፡ ሁለታችንም ፡ እየተመካከርን ፡ በመሥራት ፡ የዕለት ፡ ጠባ ችንን ፡ ልንተው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ልንታረቅና ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ለወደ ፊት ፡ ሥራዬን ፡ ልሠራ ፡ ጊዮርጊስን ፡ በማለት ፡ መሐላዬን ፡ ከኢት ዮጵያ ፡ ባንዲራ ፡ ሥር ፡ ቆሜ ፡ ምያለሁ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ ስምምነቱን ፡ አልቀበልም ፡ ቢሉ ፡ እርሳቸው ፡ ይታዘዙና ፡ በሀገራቸው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ (ካምቦ) ፡ ይውጉ ፡ እኔም ፡ በክፍል ፡ ሀገሬ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የጠላት ፡ ምሽግና ፡ (ካምቦ) ፡ በመንገድ ፡ የሚመ ጣውን ፡ እየጠበቅሁ ፡ አደጋ ፡ ልጥል ፤ ይህንንም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻ ፈው ፡ ቃል ፡ ለመፈጸም ፡ ተስማምቻለሁ ፡ ኅዳር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ዓ ፡ ም ፡ የሚል ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ አገሩ ፡ ክፍያ ፡ ብቻ ፡ አልስማማም ፡ ሲሉ ፡ በቀረው ፡ ሐሳብ ፡ በሙሉ ተስማምተው ፡ ተቀብለዋል ። ከስምምነቱም ፡ በኋላ ፡ ስለሥራ ፡ አፈጻ ጸም ፡ ለልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውና ፡ ለልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኘው ፡ ቃል ፡ ምክርና ፡ ትእዛዝ ፡ ሆኖ ፡ ተሰጠ ።

## ማስታወሻ ።

፩ኛ/ ወደ ፡ ጠላት ፡ ምሽግ ፡ የንግድ ፡ ጉዳዮች ፡ የሆኑ ፡ እህል ፤ ቅቤ ፤ ማር ፤ የሥጋ ፡ ከብትና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉት ፡ ሁሉ ፡ ለጠላት ፡ እንዳይሸጡና ፡ በጠላት ፡ ይዞታ ፡ ገበያ ፡ ላይ ፡ እንዳይገቡ ፡ አዋጅ ፡ መንገርና ፡ ማስከልከል ።

፲፫ኛ/ የሞጣንና ፡ የቄሮን ፡ ምሽጎች ፡ መክበብና ፡ በጭራሽ ፡ አሁን ፡ ካሉበት ፡ እንዳይወጡ ፡ ማድረግና ፡ ማስጨነቅ ።

፲፬/ በጠላት ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ባንዳዎች ፡ እየከዱ ፡ እንዲወጡ ፡ መጻጻፍ ፤

፲፭ኛ/ ሶስት ፡ ፈረሰኛ ፡ መልክተኞች ፡ በተቀባይ ፡ ማቆምና ፡ ጠቅላላውን ፡ የአገር ፡ አኳኋን ፡ በየሳምንቱ ፡ ጽፎ ፡ ከዚህ ፡ ካላችሁበት ፡ ደጋ ፡ ዳሞት ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ መላክ ። መላክተኛውም ፡ ሰው ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ሲነሳ ፡ በእንቦሎጮ ፡ ላይ ፡ የተነሳበትን ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ እንዲጻፍበት ፤

፲፮ኛ/ ሁለት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አጋሰስ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ማስቀመጥና ፡ መጫሪያ ፡ ለማንሳት ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ቶሎ ፡ መላክ ፡ እንዲቻል ።

፲፯ኛ/ ከኢጣልያ ፡ እየከዳ ፡ የሚመጣውን ፡ የአገር ፡ ተወላጅ ፡ ባንዳም ፡ ሆነ ፡ ነጭ ፡ ለባሽ ፡ ቢሆን ፡ ሕይወቱ ፡ እንዳይነካ ፡ እጠብቃለሁ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የቀረበልኝን ፡ ምክርና ፡ ትእዛዝ ፡ እፈጽማለሁ ፡ ስል ፡ ቃሌን ፡ መስጠቴን ፡ በፊርማዬ ፡ አስታውቃለሁ ።

ጥቅምት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም
ፊርማ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፤

## በምዕራብ ፡ ጐጃም ፡ በአገውና ፡ በዳሞት ፡ ስለሚገኘው ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ።

በጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ገብቼ ፡ ጐጃምን ፡ ከምዕራብ ፡ እስከ ፡ ምሥራቅ ፡ በመዘዋወር ፡ ከተመለከትሁና ፡ ካጠናሁት ፡ በኋላ ፡ የጠላት ፡ ኃይል ፡ በመጀመሪያ ፡ የያዘውንና ፡ በኋላም ፡ አርበኞች ፡ ዕረፍት ፡ እየነሱ ፡ ስለአስጨነቁት ፡ የለቀቀውንና ፡ ያለበትን ፡ ምሽጎችና ፡ ኃይሉንም ፡ የሚያመለክት ፤ እንደዚሁም ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ አገርና ፡ የሕዝቡንም ፡ ስሜት ፡ በመግለጽ ፡ ወደ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተላለፈ ፡ የሥራ ፡ መግለጫ ፡ ራፖር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

## በምዕራብ ፡ ጐጃም ፡ በአገውና ፡ በዳሞት ፡ የሚገኝ ፡ ምሽግ ፡

| የወረዳ ፡ | ግዛቱ ፡ ቀበሌው ፡ | |
|---|---|---|
| አቸፈር ፡ | ይስማላ ፡ ጊዮርጊስ ፡ | ተለቋል ፡ |
| | ቋንዝላ | |
| አገው ፡ ምድር ፡ | ዳንግላ ፡ | |




| | | |
|---|---|---|
| | ፋግታ ፡ | ተለቋል ፡ |
| | እንጅባራ ፡ | |
| | ወንበራ ፡ | |
| ሜጫ ፡ | ባኅር ፡ ዳር ፡ | |
| | ደብረ ፡ ፀሐይ ፡ | |
| | ቀርቃኛ ፡ | |
| | መሸንቲ ፡ | ተለቋል ፡ |
| ቆላ ፡ ዳሞት ፡ | ቡሬ ፡ | |
| | ማንኩሳ ፡ | |
| | ቀረር ፡ | |
| | ጅጋ ፡ | |
| | ግሼ ፡ ዓባይ ፡ | ተለቋል ፡ |
| | ይድቢ ፡ | » |
| | ወበታ ፡ | » |
| | ወንደገዝ ፡ | » |
| ይልማና ፡ ዴንሳ ፡ | ዘጌ ፡ አዴት ፡ | |
| | ደብረ ፡ መዊዕ ፡ | |
| ደጋ ፡ ዳሞት ፡ | ፈረስ ፡ ቤት ፡ | ተለቋል ፡ |
| | ደምበጫ ፡ | |

የጠላት ፡ ምሽግ ፡ የነበረው ፡ በነዚህ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ከ፳፰ ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ ነበር ፤ነገር ፡ ግን ፡ በየጊዜው ፡ አርበኞች ፡ እየጎተጎቱ ፡ ጤና ፡ ስለነሱት ፡ ከ፰ቱ ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ ለቆ ፡ የሄደ ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡ የሚገኘው ፡ በ፲፫ ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ ነው ። ከነዚህም ፡ አገርና ፡ ቦታዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኃይል ፡ ያለበት ፡ ፩ኛ ፡ ቡሬ ፡ ዳሞት ፡ ፪ኛ ፡ ከአገው ፡ ዳንግላ ፤ ፫ኛ ፡ ባኅር ፡ ዳር ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ቀጥዬ ፡ የማሳስበው ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ አሁን ፡ እንደምንመለከተው ፡ ከያለበት ፡ ጦሩን ፡ እየሰበሰበ ፡ ኃይሉንና ፡ ስንቁን ፡ በተወሰኑ ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ አደራጅቶ ፡ ለመከላከል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አለፈው ፡ ጊዜ ፡ የማጥቃት ፡ ክጅሎት ፡ ያለው ፡ መስሎ ፡ አልተገመተምና ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ ኃይሉን ፡ ለማደራጀት ፡ ያሰበው ፡ በእነዚህ ፡ በሶስት ፡ ምሽጎች ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ አሁኑኑ ፡ በማደራጀት ፡ ላይ ፡ ሳለ ፤ በምሽጎቹ ፡ ላይ ፡ የአይሮፕላን ፡ አደጋ ፡ ሰዓት ፡ እያዘዋወረ ፡ እንዲደርስበት ፡ ማድረግ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የጦርነቱን ፡ ጊዜ ፡ የሚያሳጥረው ፡ መሆኑን ፡ እያሳሰብኩ ፤ ደግሞ ፡ የምሥራቁን ፡ ጐጃም ፡ ሁኔታ ፡ ለማስረዳት ፡ እቀጥላለሁ ፤ ለነዚህም ፡ ምሽጎች ፡ ይገኙባቸዋል ፡ በማለት ፡ ከቆጠርኳቸው ፡ አገሮች ፤

ለአገው ፡ ምድር ፤ ለአቸፈር ፤ ለሜጫ ፤ ለዴንሳ ፤ ከዳሞት ፡ ክፍል ፡ ለጉታ ፤ ሐገረ ፡ ገገር ፡ ሆነው ፡ አርበኞችን ፡ በመምራት ፡ የሚያስተዳድሩ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬና ፡ በልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ መሐከል ፡ የሁለቱም ፡ የትውልድ ፡ ሀገር ፡ ስለሆነና ፡ በትውልድም ፡ የታላቅና ፡ የታናሽ ፡ ልጆች ፡ ሲሆኑ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፤ ይህን ፡



ልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ።

አገር ፡ ጠላት ፡ ከመውረሩ ፡ በፊት ፡ የተሰጠኝ ፡ የሹመት ፡ ሀገሬ ፡ ነውና ፡ በእኔ ፡ ውስጥ ፡ መታዘዝና ፡ መተዳደር ፡ አለብህ ፡ በማለት ፡ ሲሆን ፡ በልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ በኩል ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ ለጠላት ፡ እምነው ፡ የአንድ ፡ አገር ፡ ምስለኔ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ አገሩ ፡ በጠላት ፡ ላይ ፡ በተነሳበት ፡ ጊዜ ፡ አውራ ፡ ሆነው ፡ ይምሩን ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡



እምቢ ፡ ብለውን ፡ እኔና ፡ ፊታውራሪ ፡ ተገኜን ፡ አገር ፡ ጠይቆ ፡ እኛም ፡ ጥያቄውን ፡ ተቀብለን ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ላይ ፡ ጠላትን ፡ በመረኑታችን ፡ ስናጠቃ ፡ ፊታውራሪ ፡ ተገኜ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ስለሞቱ ፡ የሜጫ ፡ አርበኛ ፡ በሙሉ ፡ መረኑቱንና ፡ አስተዳዳሪነቱን ፡ ሰጥቶኝ ፡ እብዙ ፡ ቦታ ፡ የተዋጋሁበት ፡ ስለሆነ ፡ ለእርስዎ ፡ ታዛዥ ፡ ልሆን ፡ አይገባም ፡ በማለት ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ ክርክራቸው ፡ እስከ ፡ መዋጋት ፡ አድርሷቸው ፡ ነበር ፤ ስለሁለቱ ፡ የተደረገውን ፡ ውሳኔ ፡ እቦታው ፡ ላይ ፡ ስደርስ ፡ እገልጠዋለሁ ፡ በማለት ፡ አልፌ ፡ አሁን ፡ በምሥራቅ ፡ ጎጃም ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ ያለበትን ፡ አገር ፡ እጽፋለሁ ።

| ወረዳና ፡ ቀበሌው ፡ | ምሽግ ፡ ያለበት ፡ ደብርና ፡ አገር ፡ | |
|---|---|---|
| እነሴ ፡ | ሞጣ ፡ | |
| ሥልጣን ፡ ዓይኔ ፡ | ቄሮ ፡ | |
| ማቻከል ፡ | አማኑኤል ፡ | |
| ጀቢ ፡ | ኤልያስ ፡ | ተለቋል ፡ |
| ይናሞ ፡ | ወፊት ፡ | ተለቋል ፡ |
| ጎዛምን ፡ | ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ | |
| እነብሴ ፡ | መርጡለ ፡ ማርያም ፡ | ተለቋል ፡ |
| እናርጅ ፡ እናውጋ ፡ | ደብረ ፡ ወርቅ ፡ | ተለቋል ፡ |
| እነማይ ፡ | ብቸና ፡ | |
| ደጀን ፡ | ውሻ ፡ ጥርስ ፡ | |

በጠቅላላው ፡ በምሥራቅ ፡ ጎጃም ፡ የጠላት ፡ ምሽግ ፡ የነበረበት ፡ ፲ ሲሆን ፡ ከዚሁ ፡ አራቱ ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ እንደገለጽሁት ፤ አርበኞች ፡ እየጎተጎቱ ፡ ፋታ ፡ ስለነሱት ፡ አራቱን ፡ ለቆ ፡ አሁን ፡ የሚገኘው ፡ በስድስት ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ከነዚህም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኃይል ፡ የሚገኝበትና ፡ ለጎጃምም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ስለሆነ ፡ በደብረማርቆስ ፡ የአይሮፕላን ፡ ኃይል ፡ በዚህ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ እንዲያርፍበት ፡ ቢሆን ፡ በጎጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ያለው ፡ ጦር ፡ በቀላሉ ፡ ድል ፡ እንዲሆን ፡ የማያጠራጥር ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ አስተያየቴንና ፡ ስሜቱን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ከገለጽኩ ፡ በኋላ ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ አካባቢ ፡ ያለውን ፡ ያገር ፡ ሁኔታ ፡ እቀጥላለሁ ።

በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ አካባቢ ፡ ያሉ ፡ አገሮች ፡ ሊበንና ፡ ባሶ ፡ የተባሉትን ፡ ከዳባት ፡ የጎጃምን ፡ ጦር ፡ አስከድቶ ፡ የተመለሰው ፡ የደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡ በለው ፡ ልጅ ፡ አያሌው ፡ ገሠሠ ፡ የተባለው ፡ የጠላት ፡ ረዳት ፡ ሆኖ ፡ ይዟታል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ነፃነታቸው ፡ ቆርጠው ፡ የሚከራከሩት ፡ አርበኞች ፡ በየጊዜው ፡ እየሄዱ ፡ አገሬውን ፡ ይዘርፉታል ፡

ሊበንና ፡ ባሶን ፡ መጥቀሴ ፡ በጠላት ፡ ሹም ፡ እጅ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የበረታ ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ ያለውና ፡ አስጊ ፡ ነው ፡ ማለቴ ፡ አይደለም ። እንደዚሁ ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉት ፡ አገሮች ፡ ጐዛምን ፤ ሰናን ፡ ቂሮ ፤ አነደድ ፤ እርባብ ፡ ደማሞ ፡ በረበር ፡ ጥላትማን ፡ ፳ ፡ ቀበሌ ፡ ወረዳ ፡ ማዛቶች ፡ ለጠላት ፡ ተሰብከው ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ተቀማጭ ፡ የሆኑ ፡ ባንዳዎች ፡ ተሾመው ፡ አገሩ ፡ ላይ ፡ መቀመጥ ፡ ስላልቻሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየመጡ ፡ አገሩን ፡ እየዘረፉ ፡ ይመለሳሉ ፡ ምክንያቱም ፡ በውጭ ፡ ለመቆየት ፡ የአርበኞችን ፡ አደጋ ፡ በመፍራትና ፡ በመስጋት ፡ ነው ።

አርበኞቹም ፡ እስከ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከተማ ፡ እጥጉ ፡ ድረስ ፡ እየሄዱ ፡ አካባቢውን ፡ ሀገር ፡ ጤና ፡ ነስተውት ፡ ነው ፡ የሚታየው ። ባላገሩ ፡ ግን ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ከጉዳት ፡ ያልዳነ ፡ በመሆኑ ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ አካባቢ ፡ የሚገኘው ፡ ሕዝብ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ መስሎ ፡ ቢታይና ፡ ባንዳዎ ችም ፡ የጠላት ፡ ሹምነታቸው ፡ ቢነገር ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አድረው በት ፡ በሥልጣናቸው ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩበት ፡ አይችሉም ፤ ይኸውም ፡ የአገሩን ፡ ሕዝብ ፡ ባለማመንና ፡ አርበኞችንም ፡ በመፍራት ፡ ነው ።

## ለኢትዮጵያ ፡ መኳንንቶችና ፡ ለአርበኞች ፡ መሪዎች ፡ ደብ ዳቤ ፡ እንደጻፍኩላቸው ።

እኛም ፡ መጥተን ፡ በዚሁ ፡ ሀገር ፡ አካባቢ ፡ ሥራ ፡ ከጀመርን ፡ በኋላ ፡ ባሉት ፡ ጊዜያቶች ፡ ውስጥ ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ላሉት ፡ የኢትዮ ጵያ ፡ መኳንንቶች ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይን ፡ ምክርና ፡ የመሪነት ፡ ትእዛዝ ፡ ጽፌንላቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሙሉ ፡ ሐሳባቸው ፡ በግር ማዊነትዎ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ስለተመሰጠ ፤ በልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ በኩል ፡ ሊመጡ ፡ ተዘጋጅተዋል ፡ ስለተባለ ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውም ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ያለው ፡ ባንዳና ፡ መኳንንት ፡ በአንተ ፡ በኩል ፡ እንምጣ ፡ ተቀ በለን ፡ ብለወኛልና ፡ ይፍቀዱልኝ ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁኝ ። ከጠላት ፡ በኩል ፡ ሆኖ ፡ ያጠቃን ፡ የነበረው ፡ ወገናችን ፡ ጠላትን ፡ ከድቶ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ቃል ፡ አክብሮ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ሲመለስና ፡ ከጠላት ፡ ሲለይ ፡ የጠላታችን ፡ ኃይል ፡ እየቀነሰ ፡ በመሄዱ ፡ ለሥራችን ፡ ቀና ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ እኔም ፡ በበኩሌ ፡ የሥራውን ፡ ጠቅላላ ፡ ሁናቴ ፡ በቅርብ ፡ ሆኜ ፡ እንዳጠናሁት ፡ ጠላታችን ፡ የሚጠቃበትን ፡ ነፃነታችን ፡ የሚቋቋምበትን ፡ ዘዴ ፡ እያሰቡ ፡ ይህን ፡ በመሰለው ፡ አኳኋን ፡ ቢሠሩ ፡ በበለጠ ፡ የሚያስመሰግንዎ ፡ ነውና ፡ በማርቆስ ፡ ከተማ ፡ ባካባቢው ፡ ያሉትን ፡ መኳንንቶችና ፡ የጠላት ፡ ባንዳዎች ፡ ቢያስከዱና ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡





ደጃዝማች ፡ ለጥይበሉ ፡ ገብሬ ።

እንዲተባበሩ ፡ ቢያደርጉ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ተፈቅዷል ፡ ስል ፡ ለልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ የምክርና ፡ ያደራ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፌላቸዋለሁ ።

ከዚህም ፡ ቀጥለው ፡ አሁን ፡ በአርበኝነት ፡ የማስተዳድረውና ፡ የም መራው ፡ አገር ፡ ጐንቻና ፡ ጣር ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ዓባይ ፡ ድንበር ፡ ድረስ ፡ ወርዶ ፡ ይዋሰናል ፡ ማዶው ፡ አማራ ፡ ሳይንት ፡ ከሀገሩ ፡ ወሰነተኛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ያለውን ፡ ባንዳ ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ የሚመለሰውን ፡ በም ክር ፤ ምክር ፡ አልሰማም ፡ ብሎ ፡ የሚያምጠውን ፡ በኃይል ፡ ተዋግቼ ፡ ላስገብረውና ፡ ላቅናው ፡ ብለው ፡ በጽሑፍ ፡ ስለጠየቁኝ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኘውን ፡ ቃል ፡ ጻፍኩላቸው ።

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ የማክበር ፡ ሰላምታ ዬን ፡ አቀርባለሁ ። ስለ ፡ አማራ ፡ ሳይንት ፡ ጉዳይ ፡ ተሻግሬ ፡ ባንዳውን ፡ እንዳስገባው ፡ የጠላትም ፡ ጦር ፡ ቢመጣብኝ ፡ እንድዋጋ ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ሲሉ ፡ የጻፉልኝ ፡ ደብዳቤዎ ፡ ደረሰኝ ፤ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ በቃል ፡ ነግረውኝ ፡ ስለነበረ ፤ እኔም ፡ በበኩሌ ፡ አስተያየቴን ፡ የሚሆ



ሜ/ጀኔራል ፡ ተድላ ፡ መኰንን ።



ደጃዝማች ፡ ፀሐዩ ፡ ዕንቁ ፡ ሥላሴ ።

ንልዎትና ፡ የሚችሉ ፡ ከሆነ ፡ ጠላታችን ፡ ቢጠቃና ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ያለውንም ፡ ባንዳ ፡ የነፃነት ፡ ዓላማውንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ከመው ጋት ፡ ቢያድኑት ፡ የሚጠቅም ፡ ነውና ፡ ቢሠሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብዬ ፃት ፡ ነበር ፤ አሁንም ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እስኪመጡ ፡ ድረስ ፡ በምክርና ፡ በሰላም ፡ የሚገባውን ፡ በሰላም ፤ ምክር ፡ አልሰማም ፡ ብሎ ፡ የሚያምጸውን ፡ በኃይል ፡ እያሳመኑ ፡ እየ ሠሩ ፡ ቢቆዩ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መሆኑን ፡ በማክበር ፡ አስታው ቅዎታለሁ ።

ኅዳር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አባኘር ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡



በልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ መሪነት ፡ የሚተዳደረው ፡ አገርና ፡ አር በኛ ፡ የሚገኝበት ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

፩ኛ/ ሥልጣን ፡ ዓይኔ ፡

፪ኛ/ እነሴ ፡

፫ኛ/ ጉንቻ ፡

፬ኛ/ ማር ፡ ምድር ፡ እነዚህ ፡ አራቱ ፡ ቀበሌዎች ፡ ናቸው ።

ከነዚሁም ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ጉንቻና ፡ ማር ፡ ምድር ፡ እነሴ ፡ የተባሉት ፡ በቆራጥነት ፡ መንፈስ ፡ ከጠላት ፡ የተለዩና ፡ የሚያጠቁም ፡ ሲሆኑ ፤ እነብሴና ፡ ሥልጣን ፡ ዓይኔ ፡ የተባሉት ፡ ቀበሌዎች ፡ በሞጣ ፡ አካባቢ ፡ የሚገኙና ፡ ለምሽግም ፡ ቅርብ ፡ በመሆናቸው ፡ ሐሳባቸው ፡ እሁለት ፡ የተከፈለ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ከጠላትም ፡ ከአርበኝነትም ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ ናቸው ። አሁን ፡ ግን ፡ እኛ ፡ ከደረስንበት ፡ ጊዜ ፡ እንስቶ ፡ በም ሽግ ፡ ውስጥ ፡ በሞጣ ፡ ከተማ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ካሉ ፡ መኳንንትና ፡ ባላ ባቶች ፡ የግርማዊነትዎን ፡ አዋጅና ፡ የምክር ፡ የሰላምታ ፡ እንደዚሁም ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደብዳቤ ፡ እየጻፍንላቸው ፡ ስለ ፡ ደረሳቸው ፡ ከጠላት ፡ ለመለየት ፡ ሐሳብ ፡ ያላቸው ፡ መሆኑን ፡ እየገለጡ ፡ መጻፍ ፡ ጀምረዋልና ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ ከጠላት ፡ ተለይተው ፡ ከአርበኞች ፡ ጋራ ፡ ኅብረት ፡ አድ ርገው ፡ ጠላትን ፡ ለማጥቃት ፡ ይስማራሉ ፡ በማለት ፡ በተስፋ ፡ የሚጠ ብቁ ፡ ናቸው ።

በልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ የሚተዳደረው ፡ ሀገር ፡ ያሙት ፡ ግብሩን ፡ (ድጎው) ፡ ባላገሩ ፡ በፈቃዱ ፡ አስቦ ፡ ካልሰጣቸው ፡ በቀር ፡ በግድ ፡ አዘው፡ አይቀበሉም ። እንደዚሁም ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬና ፡ በደጃ ዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ የሚተዳደረው ፡ አገር ፡ በጣም ፡ አያስጨንቁ ትም ፡ እንጂ ፡ እንደደንብ ፡ የተወሰነውን ፡ ግብር ፡ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ እያሳሰቡ ፡ መቀበላቸው ፡ አልቀረም ። እንደ ፡ ደንብ ፡ ሆኖ ፡ አገሬው ፡ በፈቃዱ ፡ የሚሰጣቸውም ፡ አንድ ፡ ብርና ፡ አንድ ፡ ማድጋ ፡ እህል ፡ ነው ፤ በጐጃም ፡ ማድጋ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ መስፈሪያ ፡ በሸዋ ፡ ፳ ፡ ቁና ፡ የሚይዝ ፡ እንሥራ ፡ ነው ፤ ይህንኑም ፡ የማድጋ ፡ እህል ፡ የሚሰ ጣቸው ፡ አዝመራ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው ።

## በምሥራቅ ፡ ጐጃም ፡ ስለሥራችን ፡ እርምጃ ።

በምሥራቅ ፡ ጐጃም ፡ በልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ በተለይ ፡ የሚተዳደ ረው ፡ አገር ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

፩ኛ/ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ሸበል ፡
፪ኛ/ ደባይ ፡ ጥላትግን ፡
፫ኛ/ አዋባል ፡
፬ኛ/ አራራ ፡
፭ኛ/ በረንታ ፡
፮ኛ/ ጉባያ ፡
፯ኛ/ ናዝሬት ፡
፰ኛ/ ይናጭ ፡
፱ኛ/ እነማይ ፡
፲ኛ/ ውድማጊት ፡
፲፩ኛ/ እናርጅ ፡ እናውጋ ፡
፲፪ኛ/ ቅንቧት ፡

እነዚህ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ቀበሌ ፡ አገሮች ፡ ናቸው ፡፡ እነብሴ ፡ ከተባለ ውም ፡ አገር ፡ በግማሽ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ነው ፡፡ ከልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለውም ፡ ተጣልተው ፡ እመዋጋት ፡ የደረሱት ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ በሚገ ኙት ፡ አርበኞች ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡፡ ጉባያ ፡ የሚባለውም ፡ አገር ፡ ጫኔ ፡ ተረፈ ፡ የሚባለው ፡ በአርበኝነት ፡ የነበረው ፡ ከድቶ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ገብቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሕዝቡን ፡ እየሰበከ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ስቦት ፡ ነበር ፡፡ አሁን ፡ ግን ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥለውበት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እንደራሴውን ፡ ገድለው ፡ እርሱንም ፡ ለሞት ፡ የሚያሰጋ ፡ ቁስል ፡ ቆስሎ ፡ ድል ፡ አድርገውት ፡ ጠላት ፡ ከወደ ቀበት ፡ አንስቶ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከወሰደው ፡ ወዲህ ፡ አገሩ ፡ ለልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ መገበር ፡ ጀምሮዋል ፡፡ ሁለተኛም ፡ ከዓባይም ፡ ወንዝ ፡ ማዶ ፡ ቦረናና ፡ ጫቀታን ፡ ደራን ፡ ፫ቱንም ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ አስተዳደር ፡ ሙሉ ፡ ግብሩን ፡ ያስገብሩታል ፡፡

ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ግን ፡ ሥራቸው ፡ ከአርበኞች ፡ ሁሉ ፡ የተለየ ፡ በመሆኑ ፡ ጐበዙንና ፡ ጊዜው ፡ በሚፈቅደው ፡ ዓይነት ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚችለውን ፡ እያበረታቱ ፡ በመሥራታቸው ፡ ከእርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ አርበኛ ፡ በቁጥር ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ መሆኑን ፡ ተመልክቼ ፡ ገምቻለሁ ፡፡ ጀግናውም ፡ አርበኛ ፡ ከግራዝማች ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ቢትወ ደድ ፡ ድረስ ፡ ስም ፡ እየሰጡ ፡ ይሾማሉ ፤ ተሿሚውም ፡ እየተቀበለ ፡ ሲጠራበት ፡ ቅርም ፡ አይለው ፤ የደጃዝማችና ፡ የፊታውራሪ ፡ ብዛት ፡ በየደብሩና ፡ በየጐጡ ፡ ስለሆነ ፡ ክልክ ፡ ያለፈ ፡ ነው ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንደዚሁ ፡ ብዙ ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ በሚሰጡበት ፡ ቀን ፡ ታናሽ ፡ ወንድማቸውን ፡ ደጃዝማች ፡ ብለው ፡ ቢሾሙት ፡ «ጋሼ ፡ ሁሉን ፡ ራስ ፡



ደጃዝማች ፡ ብለህ ፡ ሾምህ ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ልትባል ፡ ነው» ? ቢላቸው ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ ምን ፡ ያስፈልገኛል ፡ እናቴ ፡ በላይ ፡ ብላኝ ፡ የለምወይ ፡ አሉት ፡ ይባላል ፡፡

በሚያስተዳድሩት ፡ አገር ፡ ደስ ፡ ሲያሰኝ ፡ በመሾምና ፡ በመሸለም ፡ ሲያጠፋም ፡ በጠበቀ ፡ ቅጣት ፡ ያለምሕረት ፡ የሚቀጡት ፡ ስለሆነ ፡ አርበኛውም ፡ ሆነ ፡ ባላገሩ ፡ የሚተላለፍለትን ፡ ትእዛዝ ፡ በፍርሐት ፡ ተቀብሎ ፡ ሲፈጽም ፡ ይታያል ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ፈቅ ደውም ፡ ይሁን ፡ ሳይፈቅዱ ፡ ወይም ፡ ሕዝቡ ፡ ለማቆላመጥና ፡ ለማሞካ ሸት ፡ ይሁን ፡ አይታወቅም ፤ በው ስጣቸው ፡ ያለው ፡ አርበኛና ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ ልዑል ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ እያለ ፡ ይጠራቸዋል ፤ እሳቸውም ፡ አልተቃወሙትም ፡፡

ስላገሩና ፡ ስላርበኞቹ ፡ ሁናቴ ፡ ከገለጽኩ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀን ፡ ስለሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ምክር ፡ ሰጥቼ ፡ እሠራለሁ ፡ ብለው ፡ ቃል ፡ ገብተው ፡ የፈረሙበት ፡ ቃል ፡ ግልባጭ ፡ እዚህ ፡ ተገልጿል ፡ ቃሉም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፡፡

፩ኛ/ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ በርም ፡ ለመክፈት ፡ ጐጃ ምና ፡ ሸዋን ፡ ለማገናኘት ፡ ቦረናና ፡ ጫቀታን ፡ ደራን ፡ ማሳመን ፡ ጀምሬ አለሁና ፡ አሁንም ፡ ለመሥራት ፡ የሚቀና ፡ ስለመሰለኝ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ እስከ ፡ መርሐ ፡ ቤቴና ፡ ሰላሌ ፡ ድረስ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ መግቢያ ፡ በሩን ፡ ለመክፈት ፡ እስከሚቻለኝ ፡ እሠራለሁ ፡፡

፪ኛ/ በጐጃም ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ አግጄ ፡ አቆማለሁ ፡ ለማለት ፡ ድንገት ፡ በኃይል ፡ ገፍቶ ፡ ቢያልፍ ፡ ውሸታም ፡ ያሰኘኛል ፡ በማለት ፡ እሰጋለሁ ፡ እንጂ ፡ በተረፈ ፡ በቢቸናም ፡ ሆነ ፡ በደብረ ፡ ማርቆስ ፡ በደጀ ንም ፡ ባለው ፡ ባንዳ ፡ ላይ ፡ ከጠላት ፡ እንዲለይ ፡ የተነገረውን ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ ከጠላት ፡ አልለይም ፡ ያለውን ፡ አደጋ ፡ በመጣልና ፡ ጤና ፡ በማሳጣት ፡ እረፍት ፡ ነስቶ ፡ ጠላትን ፡ ለማስለቀቅ ፡ በትጋት ፡ እሠራለሁ ፡፡

፫ኛ/ በየጊዜው ፡ የምንሠራውን ፡ ሥራ ፡ በ፫ ፡ በ፫ ፡ ቀን ፡ ዕለት ፡ ፈረሰኛ ፡ መላክተኛ ፡ አቁሜ ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ እልካለሁ ፡፡

፬ኛ/ ለመሣሪያና ፡ ለገንዘብ ፡ ማስነሻ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ አጋሰስ ፡ ላክ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ሲደርሰኝ ፡ ደብዳቤው ፡ በደረሰኝ ፡ በስምንተ ኛው ፡ ቀን ፡ አጋሰሱን ፡ አሰናድቼ ፡ ይላክ ፡ እተባለበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ ለመላክ ፡ እዘጋጃለሁ ፡፡

፭ኛ/ ወደ ፡ ጠላት ፡ ከተማና ፡ ምሽግ ፡ የሚገባውን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ እንዳይሄድ ፡ የጠበቀ ፡ አዋጅ ፡ አስነግሬ ፡ እስከለክላለሁ ፡፡

፳፯ኛ/ በእግዚአብሔር ፡ ኢጋዥነት ፡ እስከሚቻለኝ ፡ ጠላት ፡ የሚጠቃበትን ፡ የእኛ ፡ ኃይል ፡ በርትቶ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ የነፃነት ፡ ባንዲራችንን ፡ ይዘው ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ የሚገቡበትን ፡ በመተባበር ፡ እሠራለሁ ፡ ስል ፡ በፊርማዬ ፡ አረጋግጣለሁ ፡ ኅዳር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡፡

ፊርማ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡

እንደዚሁ ፡ የአርበኞች ፡ መሪዎች ፡ ባለመግባባት ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ይፈላለጉ ፡ የነበረው ፡ ጠብ ፡ ቀርቶ ፡ በስምምነት ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማድረግ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬና ፡ ቢትወደድ ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ በሐሳብ ፡ በጣም ፡ የተራራቁ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ እንዲገናኙ ፡ አድርገን ፡ የርስ ፡ በርሳቸው ፡ ጠብ ፡ ቀርቶ ፡ ጠላትን ፡ በመተባበር ፡ እያጠቁ ፡ እንዲሆኑ ፡ ስላደረግን ፡ ከተገናኙ ፡ በኋላ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባንዲራ ፡ መትረየሱን ፡ በመሐከላቸው ፡ አድርገው ፡ ወደፊት ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ ለመጠቃቃት ፡ መፈላለጋችን ፡ ቀርቶ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ የሚገቡበትን ፡ በር ፡ ለመክፈት ፡ በመተባበር ፡ ጠላትን ፡ እናጠቃለን ፡ በማለት ፡ ባንዲራውን ፡ በየእጃቸው ፡ ይዘው ፡ በንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስም ፡ በመሐላ ፡ ስምምነታቸውን ፡ አጸኑ ፡፡

በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬና ፡ በልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ መሐከል ፡ ስላለው ፡ ነገር ፡ እላይ ፡ ባለፍኩት ፡ መስመር ፡ እንደጻፍኩት ፡ ጠብ ፡ ተነስቶ ፡ ተዋግተው ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ሁለተኛም ፡ ለመዋጋት ፡ ይፈላለጉ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ይህ ፡ ጠብ ፡ ቀርቶ ፡ በኅብረት ፡ ጠላትን ፡ እንዲያጠቁ ፡ አገናኝቶ ፡ ለማስማማት ፡ እስቤ ፡ ሁለቱንም ፡ ለየብቻቸው ፡ አነጋግሬያቸው ፡ ልጅ ፡ አበረ ፡ ይማምም ፡ የስምምነቱን ፡ ሐሳብ ፡ ሲቀበል ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ ስላልፈቀዱ ፡ ነገሩ ፡ በስምምነት ፡ ሊያልቅ ፡ አልተቻለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻን ፡ በመሸሽ ፡ ከጠላት ፡ ተጠግቷል ፡ ስለተባለ ፡ ለመነጠል ፡ አስቤ ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻና ፡ በልጅ ፡ አበረ ፡ መሐከል ፡ ጠብ ፡ እንዳይነሳ ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ሰጥቻቸዋለሁ ፡፡ ቃሉም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፡፡

፳፰ኛ/ ልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ ማረፊያ ፡ በማጣት ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ገብቶ ፡ የጠላት ፡ መሣሪያ ፡ እንዳይሆን ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ እስኪመጡ ፡ ለእርሱና ፡ ለጓዙ ፡ ማረፊያ ፡ የሚሆን ፡ አሁን ፡ በአለበት ፡ አገር ፡ አቅራቢያ ፡ ከሆነው ፡ ዙሪያ ፡ አሥር ፡ ደብር ፡ አገር ፡ ከሜጫ ፡ ውስጥ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ ለልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ ሊሰጡ ፤

፳፱ኛ/ ስለዚሁ ፡ አገር ፡ አስተዳደር ፡ ልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ ባወቀ ፡ ሊያስተዳድር ፡ እንጂ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ በማናቸውም ፡ ሰበር ፡ ላይገቡበት ፡፡



፴ኛ/ በልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ባላገር ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ባላገር ፡ በድሎ ፡ ቢገኝና ፡ የሚከሰስበት ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ዳኝነት ፡ የሚፈጸመው ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ላይ ፡ ነው ፡፡

፴፩ኛ/ እንደዚሁ ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ባላገር ፡ በልጅ ፡ አበረ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ባላገር ፡ ቢበድለውና ፡ የሚከሰስበት ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ የዳኝነቱን ፡ ሥራ ፡ የሚመለከተውና ፡ የሚፈጸመው ፡ በልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ በኩል ፡ ነው ፡፡

፴፪ኛ/ ልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ ከወረዳው ፡ አርበኛ ፡ መሪዎች ፡ ጋራ ፡ ቢጣላ ፡ ወይም ፡ የወረዳ ፡ አርበኛ ፡ መሪዎች ፡ ከልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ ጋራ ፡ ቢጣሉ ፡ የእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ዳኝነት ፡ የሚታየው ፡ በንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ስም ፡ በቆመው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነው ፡፡

፴፫ኛ/ ምናልባት ፡ ልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገጥሞ ፡ ማጥቃት ፡ አቅቶት ፡ የሚጠቃ ፡ ሆኖ ፡ የመሸሽ ፡ ግዴታ ፡ ሲደርስበት ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነው ፡ በማንኛውም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ሸሽቶ ፡ ቢጠጋ ፡ ላይከለከል ፡ ነው ፡፡

፴፬ኛ/ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ አገር ፡ ነፍስ ፡ ገድሎና ፡ ከብት ፡ ዘርፎ ፡ በጠቅላላው ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ በደሉኝ ፡ ብሎ ፡ ከድቶ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ አበረ ፡ ቢመጣ ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሰላምን ፡ የሚያጠፋ ፡ ስለሆነ ፡ ሳይቀበል ፡ አሳልፎ ፡ ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ እንዲሰጥ ፡፡

እንደዚሁ ፡ በልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ በኩል ፡ በድሎ ፡ ወደ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ ክፍለ ፡ አገር ፡ ቢገባ ፡ ላይቀበሉና ፡ ለልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡ ሊሰጡ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጦር ፡ ተነስቶ ፡ ለመረዳዳት ፡ የማንኛቸውም ፡ ወገን ፡ አርበኛ ፡ የአንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ሄዶ ፡ በፈቃዱ ፡ ቢረዳ ፡ አይከለከልም ፡ በማለት ፡ ውሳኔ ፡ አድርጌ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ እንዲፈርሙበትና ፡ በመሥሪያ ፡ ቤታችን ፡ እንዲቀመጥ ፡ ጠይቄ ፡ ልጅ ፡ አበረ ፡ እሺ ፡ ሲል ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አልፈቀዱም ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስም ፡ የቆመው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በትእዛዝ ፡ ለሁለቱም ፡ ይህን ፡ ስምምነት ፡ እንዲያከብሩት ፡ ኮፒውን ፡ አስቀርቶ ፡ አስተላለፈና ፡ ልጅ ፡ አበረ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲደርሰው ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ የነበረውን ፡ ግንኙነት ፡ አቋረጠና ፡ ጠላትን ፡ ማጥቃት ፡ ጀመረ ፡፡ እንደዚሁም ፡ በደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በፊታውራሪ ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስና ፡ በፊታውራሪ ፡ በቀለ ፡ አምባዬ ፡ መካከል ፡

አለመግባባት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ባይገናኙም ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ በመረዳዳት ፡ ማጥቃት ፡ እንጂ ፡ የእርስ ፡ በርሳቸው ፡ መጋጨትና ፡ መፈላለግ ፡ ለጠላት ፡ መመቸትና ፡ ማጥቂያ ፡ ጉዳይ ፡ መስጠት ፡ ስለሆነ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ መጥፎ ፡ ሐሳብ ፡ እንዲተው ፡ ያቀረብኩላቸውን ፡ ምክር ፡ ሁሉም ፡ ተቀብለው ፡ ጠላትን ፡ በማጥቃት ፡ ላይ ፡ መሰማራት ፡ ጀምረዋል ።

## በሸዋ ፡ በቤጌምድር ፡ በላስታ ፡ በአገውና ፡ በሰቆጣ ፡ ካሉ ፡ አርበኞች ፡ ጋራ ፡ በደብዳቤ ፡ ግንኙነት ፡ ስለመደረጉ ።

እንደዚሁም ፡ በሸዋ ፡ በቤጌምድር ፡ በላስታ ፡ በአገው ፡ ሰቆጣ ፡ ላሉ ፡ አርበኞች ፡ ለጊዜው ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለመገናኘት ፡ ስላልተቻለ ፡ በደብዳቤ ፡ ግንኙነት ፡ አድርገናል ፡ ደብዳቤ ፡ የጻፍንላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ስምና ፡ የጽሑፍ ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

ለጊዜው ፡ ስማቸው ፡ ለታወቁት ፡ በስማቸው ፡ ሲጻፍ ፡ ለቀረው ፡ ግን ፡ በአገሩ ፡ ስም ፡ ነው ፡ የተጻፈው ፡ ቃሉ ፡ ግን ፡ የሁሉም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ስለሆነ ፡ የጽሑፉ ፡ ቃል ፡ ይቀጥላል ።

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡..............................

፩/ ለአጋፋሪ ፡ ያረጋል ፡

፪/ ለልጅ ፡ ነገደ ፡ ዘገዬ ፡

፫/ ለልጅ ፡ ዮሐንስ ፡ ኢያሱ ፡

፬/ ለፊታውራሪ ፡ ታፈረ ፡

፭/ ለፊታውራሪ ፡ አዬ ፡ ታደሰ ፡

፮/ ለፊታውራሪ ፡ በላይ ፡ ተሰማ ፡

፯/ ለቀኛዝማች ፡ ታደሰ ፡ ይማም ፡

፰/ ለደጃዝማች ፡ ዳኘው ፡ ተሰማ ፡

በቤጌምድር ፡ አውራጃና ፡ በየሀገሩ ፡ ላላችሁ ፡ አርበኞችና ፡ ለባላገሩም ፡ ለጤናችሁ ፡ እንደምን ፡ ሰንብታችኋል ፡ ቸር ፡ አምላካችን ፡ ይመስገን ፡ ለጤናችን ፡ እኛ ፡ ደህና ፡ ነን ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አጥቂው ፡ ጠላታችን ፡ በግፍ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረ ፡ ጊዜ ፡ ከአቅማችን ፡ በላይ ፡ በሆነው ፡ መሣሪያ ፡ በአይሮፕላን ፡ ቦንብና ፡ በጭስ ፡ መርዝ ፡ እየጣለ ፡ ሕዝቡን ፡ ከነቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እያቃጠለ ፡ የሚፈጀው ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ ለመበቀል ፡ ሲሉ ፡ ተሰደው ፡



ሲደክሙበት ፡ የነበረው ፡ ጉዳይ ፡ ስለ ፡ ተፈጸመላቸውና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመመለስና ፡ ለመግባት ፡ ወደ ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ በተቃረቡበት ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አርበኞችና ፡ ሕዝቧም ፡ ለሆናችሁ ፡ ሁሉ ፡ የምሥራቹን ፡ ለመንገር ፡ ተልኬ ፡ ጐጃም ፡ መሬት ፡ ገብቻለሁ ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ደክመው ፡ ያገኙትን ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚገባበትን ፡ የአርበኛውንም ፡ ብርታትና ፡ ትጋት ፡ መርምረው ፡ ለመንግሥታቸው ፡ የሚያስታውቁ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ አብረውኝ ፡ አሉ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ መሣሪያ ፡ እስቲቀድምና ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚጠብቁ ፡ በቶሎ ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሊገቡ ፡ ተወስኗል ፤ ስለዚህ ፡ ሁላችሁም ፡ በየበኩላችሁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ የሚገቡበትን ፡ ሐሳብ ፡ በመተባበር ፡ እየመከራችሁ ፡ በብርታት ፡ የምትሠሩትን ፡ ሥራ ፡ በደብዳቤ ፡ በየዕለቱ ፡ ግንኙነት ፡ እንድናደርግና ፡ የሚቸግራችሁንና ፡ የሚጐድላችሁ ፡ እርዳታ ፡ እንዲላክላችሁ ፡ ይሆናል ፤ ለአርበኛው ፡ ሕዝባቸው ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤና ፡ የአዋጁን ፡ ቃል ፡ ይዞ ፡ ከዛሬ ፡ በፊት ፡ ሰው ፡ ተልኮ ፡ ነበርና ፡ ሳይደርሳችሁ ፡ አልቀረም ፡ ለዚህም ፡ ሥራ ፡ በአርማጭሆም ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ መላክተኞች ፡ ከረዳቶቻቸው ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ መላክተኞች ፡ ጋራ ፡ ገብተው ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ናቸውና ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ብትላላኩ ፡ ትችላላችሁ ። የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችንን ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ በየዓይነቱ ፡ ልከናል ፤ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ለእርዳታ ፡ የተላኩት ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ የሆኑት ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ የጻፉላችሁን ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ልኬዋለሁ ።

የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ነፃነት ፡ ረዳቶች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ጠላት ፡ እንደሚያወራው ፡ የግዛት ፡ ተካፋይ ፡ አለመሆናቸውን ፡ በማረጋገጥ ፡ እውነተኛውን ፡ እነግራችኋለሁ ፤ በእኔም ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ልብ ፡ አድርጋችሁ ፡ አንብቡት ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ፡ ነገሥታችን ፡ አዋጅም ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ማስረጃ ፡ ታገኙታላችሁ ። ሁላችንም ፡ የምንጠብቀውን ፡ ነፃነታችንን ፡ አግኝተን ፡ በሕይወት ፡ ለመገናኘት ፡ ያብቃን ፡ ጥቅምት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ የተላከላቸው ፡ አገሮች ፡ የሚቀጥሉት ፡ ናቸው ።

## በቤጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ።

፩ኛ/ ጋይንት ፡
፪ኛ/ ውዶ ፡
፫ኛ/ ቆማ ፡
፬ኛ/ አፈረዋናት ፡
፭ኛ/ መና ፡ መቀጣዋ ፡
፮ኛ/ ላስታ ፡
፯ኛ/ እስቴ ፡
፰ኛ/ ፋርጣ ፡
፱ኛ/ ከምከም ፡ ቃሮዳ ፡
፲ኛ/ ነገላ ፡
፲፩ኛ/ እንዳቤት ፡
፲፪ኛ/ ዋግ ፡

በሸዋ ፡ ላሉ ፡ አርበኞችና ፡ በየክፍሉ ፡ ላሉ ፡ መኳንንቶች ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ዓይነት ፡ ተጽፎአል ። የተጻፈላቸው ም ፡ መኳንንቶችና ፡ የአርበኞች ፡ የስም ፡ ዝርዝር ፡ ከነአድራሻቸው ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ነው ።

መርሐ ፡ ቤቴና ፡ ሰላሌ ፡

፩ኛ/ ልጅ ፡ ተሾመ ፡ ሽንቁጥ ፡
፪ኛ/ ልጅ ፡ አበበ ፡ ሽንቁጥ ፡
፫ኛ/ ልጅ ፡ ዘገዬ ፡ ሽንቁጥ ፡
፬ኛ/ ልጅ ፡ መሸሻ ፡ በርቅሶ ፡
፭ኛ/ ባሻ ፡ ገለታ ፡ ቆርቾ ፡
፮ኛ/ ልጅ ፡ ፀሐዩ ፡ ዕንቈ ፡ ሥላሴ ፡
፯ኛ/ ልጅ ፡ ይልማ ፡ በሺ ፡
፰ኛ/ ባላምባራስ ፡ ተድላ ፡ መኰንን ፡
፱ኛ/ ልጅ ፡ ዘውዴ ፡ በለጠ ፡

በመሐል ፡ ሸዋ ፡

፩ኛ/ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡
፪ኛ/ ደጃዝማች ፡ አውራሪስ ፡
፫ኛ/ ፊታውራሪ ፡ ዘውዱ ፡ አባ ፡ ኰራን ፡



፬ኛ/ ፊታውራሪ ፡ አየለ ፡ ኃይሌ ፡
፭ኛ/ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ወሰኔ ፡
፮ኛ/ ብጅሮንድ ፡ ለጥይበሉ ፡ ገብሬ ፡
፯ኛ/ ከንቲባ ፡ ከበረ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
፰ኛ/ ፊታውራሪ ፡ ተሰማ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
፱ኛ/ ልጅ ፡ ደገፋ ፡ አየለ ፡
፲ኛ/ ልጅ ፡ ሉል ፡ ሰገድ ፡ በየነ ፡
፲፩ኛ/ ልጅ ፡ መኩብብ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡
፲፪ኛ/ ልጅ ፡ ገነነ ፡ በዳኔ ፡


ፊታውራሪ ፡ አየለ ፡ ኃይሌ ፡


ልጅ ፡ መኩብብ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡

በመንዝና ፡ ይፋት ፡

፩ኛ/ ልጅ ፡ ከፈለው ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡
፪ኛ/ ባሻ ፡ ተሰማ ፡ እርገጤ ፡

በግሼና ፡ በኤፍራታ ፤
፩ኛ/ ፊታውራሪ ፡ ዳምጠው ፡ መሸሻ ፡



ፊታውራሪ ፡ ገረሱ ፡ ዱኪ ፡ (ደጃዝማች) ፡

በጋላው ፡ ሀገር ፡ ያሉ ፡

፩ኛ/ ፊታውራሪ ፡ ገረሱ ፡ ዱኪ ፡
፪ኛ/ ቀኛዝማች ፡ በዛብህ ፡ ስለሺ ፡
፫ኛ/ ልጅ ፡ ከበደ ፡ ብዙነሽ ፡
፬ኛ/ ግራዝማች ፡ እንደሻው ፡ ቂንጤ ፡

በግንደበረት ፡ ላሉ ፡ ስማቸው ፡ ላልታወቀው ፡ በሀገር ፡ ስም ፡ ተጽፎላቸዋል ፡፡

ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ በቡልጋ ፡ በኩል ፡ ዞሮዋል ፡ ስለተባለ ፡ በተለይ ፡ ለርሱ ፡ የጻፍሁለት ፡ ደብዳቤ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ፡፡





ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡



አባኙ ፡ ከበደ ፡ ተሰማና ፡ ቀኛዝማች ፡ በዛብህ ፡ ስለሺ ፡ (ደጃዝማች) ፡

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፤

ለጤናህ ፡ እጅጉን ፡ እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፤ ቸር ፡ ፈጣሪያችን ፡ ይመስገን ፡ እኔ ፡ ደኅና ፡ ነኝ ፤ እንደምታውቀው ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ጋራ ፡ ተሰድጄ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሳለሁ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፌልህ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ የምጽፍልህ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ተሰደው ፡ ሲደ ክሙበት ፡ የነበረው ፡ ጉዳይ ፡ ስለተፈጸመላቸውና ፡ አገራቸው ፡ ድንበር ፡ ስለደረሱ ፤ ለኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ሁሉ ፡ የምሥራች ፡ ለመናገርና ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ ለማናገር ፡ ተልኬ ፡ ስለመጣሁ ፡ ጐጃም ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሆኘ ፡ ነው ። በጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ካሉ ፡ አርበኞች ፡ ጋራ ፡ እየተገናኘን ፡ የሚጐድለውን ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ እንዲረዱ ፡ ተችሏል ። ይህንንም ፡ እርዳታ ፡ የሚያደርጉ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ መጥተው ፡ ጐጃም ፡ መሬት ፡ ገብተዋል ፤ ወደ ፡ እናንተም ፡ ለመዝለቅ ፡ አስበን ፡ የመንገዱን ፡ አኳኋን ፡ ለመመርመር ፡ ስንል ፡ ነውና ፡ የቆየነው ፡ ማንኛውንም ፡ አኳኋን ፡ አጥር ተህ ፡ ጻፍልኝ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥታችንም ፡ በድንገተኛ ፡ ጊዜ ፡ በአርበኞቻ ቸው ፡ መሐከል ፡ ሊገኙ ፡ ተወስኗል ። ለጊዜውም ፡ አሁን ፡ ያልመጡበት ፡ ምክንያት ፡ መሣሪያውንና ፡ ገንዘቡን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለማስገባት ፡ ብቻ ፡ ሲሉ ፡ ነው ። ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ መድረሱንና ፡ በቶሎ ፡ መገናኛ ፡ መኖ ሩን ፡ ባውቅ ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ማኅተም ፡ እንዲደርስህ ፡ ስለማምን ፡ እልክልሀለሁ ።

አሁን ፡ ግን ፡ ያላኩልህ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሁናቴ ፡ አጥ ርቼ ፡ ባለማወቄ ፡ ነው ። በሸዋ ፡ ክፍል ፡ ያሉትን ፡ አርበኞች ፡ ለጊዜው ፡ በብዙ ፡ አጥርቼ ፡ ስለማላውቃቸው ፡ ቃሉን ፡ ጽፌ ፡ የስም ፡ ማግቢያ ፡ ቦታ ፡ ትቼ ፡ እየፈረምኩ ፡ ልኬልሀለሁና ፡ ለምታውቀው ፡ አርበኛ ፡ ሁሉ ፡ ስሙን ፡ እየሞላህ ፡ እንድትልክልኝ ፡ እለምንሀለሁ ። በሸዋ ፡ ክፍል ፡ ያለውን ፡ የጠላት ፡ ኃይልና ፡ ምሽግ ፡ ያለበትን ፡ አገር ፡ በዝርዝር ፡ ብት ጽፍልኝ ፡ የአይሮፕላን ፡ አደጋ ፡ እንዲያገኛቸው ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ። እንደዚሁም ፡ የኛ ፡ አርበኞች ፡ ያሉበትን ፡ አገርና ፡ ብርታታቸውንም ፡ በጠቅላላው ፡ የሕዝቡንም ፡ ሐሳብ ፡ እንድትጽፍልኝ ፤ የመሣሪያና ፡ የገን ዘብ ፡ እርዳታ ፡ ለማግኘት ፡ እንዲቻል ፡ ከጐጃም ፡ የምትገናኝበትን ፡ በር ፡ ለመክፈት ፡ እጥብቀህ ፡ አስብበት ። የመንገዱን ፡ ደኅንነት ፡ በላክናቸው ፡ መላክተኞች ፡ አጥርቼ ፡ ሳውቀው ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሠራተኛ ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ በመሐከላችሁ ፡ ይገኛል ። በባኅርዩ ፡ ሞት ፡ በመንግሥቱ ፡ ኅልፈት ፡ የሌለበት ፡ አምላክ ፡ በሕይወት ፡ ለመገናኘት ፡ ያብቃን ።

ኅዳር ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡




ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉት ፡ ደብዳቤዎች ፡ ግልባጭና ፡ የሥራውም ፡ ራፖሮች ፡ ጐጃም ፡ ከደረስሁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ተልከዋል ።

በአርበኝነት ፡ ዘመን ፡ በሸዋ ፡ ክፍል ፡ ሀገር ፡ በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መዐየጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጀግኖች ፡ ማኅበር ፡ » በሚል ፡ ስም ፡ የተ ጠራ ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ቆሞ ፡ የአርበኞችን ፡ ልብ ፡ በማበረታታትና ፡ በየሃገሩ ፤ ካሉ ፡ አርበኞች ፡ ጋር ፡ በመላላክ ፡ የሚገኘውን ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ወደ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ እየላከ ፤ ከግርማዊነታቸውም ፡ ለአርበ ኞች ፡ የሚላከውን ፡ የተስፋ ፡ ቃልና ፡ ማበረታቻ ፡ እያስተላለፈ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ማኅበር ፡ መሥራች ፡ ማኅበረተኞችና ፡ ከኮሚቴው ፡ አባ ሎች ፡ ውስጥ ፡ ከአንዳንዶቹ ፡ ጋር ፡ እንላላክ ፡ ስለነበረ ፡ ስማቸውን ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ሙስመር ፡ ገልጬዋለሁ ። በጊዜው ፡ ላይ ፡ የነበሩበትን ፡ ሁናቴ ፡ የሚያሳይ ፡ ፎቶግራፋቸው ፡ የተገኘውንም ፡ የአርበኞች ፡ ዓይ ነት ፡ ለማሳየት ፡ ያህል ፡ በዚህ ፡ ማስታወሻ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገኝ ፡ አድርጌአለሁ ።

የመሥራች ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ስም ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ። የማዕ ርግ ፡ ስማቸው ም በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ ዓይነት ፡ ተጽፎአል ።



ራስ ፡ አበበና ፡ ባላምባራስ ፡ ተድላ ፡ መኰንን ፡ (ሜ/ጄኔራል) ።




ባሻ ፡ ወልደ ፡ ኪሮስ ፡ ትብረ ፡ መስቀል ፡ (ደጃዝማች) ።



የጀግኖች ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ።

ከግራ ፡ ወደቀኝ ፡ ልጅ ፡ ተስፋዬ ፡ ዕንቊ ፡ ሥላሴ ፡ (ደጃዝማች) ፡ አቶ ፡ ደጣለኝ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ልጅ ፡ ፀሐዩ ፡ ዕንቊ ፡ ሥላሴ ፡ (ደጃዝማች) ፡ አቶ ፡ ልሣኑ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፡ ልጅ ፡ አሉላ ፡ በቀለ ፡ (ደጃዝማች) ።





ደጃዝማች ፡ ደምሴ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ።

ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፤
ባሻ ፡ ወልደ ፡ ኪሮስ ፡ (አሁን ፡ ደጃዝማች) ፡
ልጅ ፡ ደምሴ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ (አሁን ፡ ደጃዝማች) ፡
ልጅ ፡ ደጣለኝ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፤
አቶ ፡ ልሳኑ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ፤
ባላምባራስ ፡ ተድላ ፡ መኰንን ፤ (ሜ/ጀኔራል) ፡
ልጅ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ መኰንን ፤ (ፊታውራሪ) ፡
ልጅ ፡ ፀሐዩ ፡ ዕንቊ ፡ ሥላሴ ፡ (አሁን ፡ ደጃዝማች) ፡

አቶ ፡ ፈለቀ ፡ ዳኜ ፡ (ደጃዝማች) ፡
አቶ ፡ ጽጌ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤
አቶ ፡ ተስፋዬ ፡ ዕንቁ ፡ ሥላሴ ፡ (ደጃዝማች) ፡



ፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ መኰንን ።

ልጅ ፡ አሉላ ፡ በቀለ ፤
አቶ ፡ እምአእላፍ ፡ ኅሩይ ፤
አቶ ፡ ዘውዴ ፡ ሃብተ ፡ ወልድ ፤
አቶ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ የምሩ ፤
አቶ ፡ ተፈሪ ፡ ማንደፍሮ ፤
አቶ ፡ ለማ ፡ ደገፌ ፤





ፊታውራሪ ፡ ይልማ ፡ በሺ ፡ ከወታደሮቹ ፡ ጋር ።



አቶ ፡ እምአእላፍ ፡ ኅሩይ ።



ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወልዴ ፡
በገጽ ፡ ፻፶፫ ፡ ተመልከት ፡



ደጃዝማች ፡ ታከለ ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡
በገጽ ፡ ፻፶፰፰ ፡ ተመልከት ፡



ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ይልማ ፡
በገጽ ፡ ፻፶፫ ፡ ተመልከት ፡





ፊታውራሪ ፡ በቀለ ፡ ካሣ ፡ (ደጃዝማች) ፡
በገጽ ፡ ፻፺፷፯ ፡ ተመልከት ፡




ፊታውራሪ፡አልማው፡ወርቅነህ፡ (ደጃዝማች)፡
በገጽ ፡ ፻፺፷፱ ፡ ተመልከት ፡



ዶክተር ፡ አምባዬ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡
በገጽ ፡ ፻፶፬ ፡ ተመልከት ፡

ግራዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ሥላሴ ፡ በላይነህ ፡ (በኋላ ፡ ቀኛዝማች) ፡
አቶ ፡ ይስሐቅ ፡ ወልዴ ፤
አቶ ፡ ታደሰ ፡ ዘለቀ ፤
አቶ ፡ አበበ ፡ ጠጋዬ ፤
አቶ ፡ አድማሱ ፡ ገብሬ ፤

በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ የመሥራቾቹ ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ማኅበረተኞች ፡ እየተጨመሩ ፡ የአባሎቹ ፡ ቁጥር ፡ ከሶስት ፡ መቶ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ።



አቶ ፡ ልዑል ፡ ሰገድ ፡ በየነ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

## ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተላኩ ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደብዳቤ ዎችና ፡ ማስታወሻዎች ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የምጽፈው ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተላኩልኝን ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደብዳቤዎችና ፡ ማስታወሻዎችን ፡ ነው ። እነርሱም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

### የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፤ አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ በሕዝባችን ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ የሚሠሩትን ፡ ፕሮፓጋንዳ ፤ የአውሮፓን ፡ አኳኋን ፡ የሚያውቀው ፡ ስለሆነ ፡ ተቀዋሚ ፡ የሚሆነውን ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ እንዲሠራ ፡ አዘነው ፡ መጥቷልና ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አብራችሁ ፡ ሆናችሁ ፡ እንዲሠራ ፡ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድም ፡ እንድታገናኘው ፡ ይሁን ፤ ስለርሱም ፡ ስለሥራው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ገንዘብ ፡ ከዚያ ፡ እንዲቀበል ፡ አስታውቀንዋል ።ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ።

### ፩ኛ/ ማስታወሻ ፡ ለአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

፩/ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬና ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ እስከ፡ ተገናኛችሁበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ስለመንገዳችሁ ፡ አኳኋን ፡ በዝርዝር ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ አየነው ፤ ይልቁንም ፡ ዝብስት ፡ ላይ ፡ ስትደርሱ ፡ ጠላት ፡ ካዘጋጀው ፡ ወጥመድ ፡ ለማምለጥ ፡ መቻላችሁን ፡ ስንመለከት ፡ ደስ ፡ አለን ፤ የዝብስት ፡ አርበኞች ፡ ባነስ ፡ ቁጥራቸው ፡ የሠሩት ፡ ጀግንነት ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ፤ ስላደረጉላችሁም ፡ አቀባበል ፡ ምስጋናቸው ፡ አይጠፋም ።

፪/ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በነሐሴ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ለጻፍክለው ፡ ማመልከቻ ፡ ወደ ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ በመጡት ፡ በሻለቃ ፡ መሥ

ፍን ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ምላሹ ፡ በ፳፰ ፡ መስከረም ፡ በተጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ስለተላከልህ ፡ እስካሁን ፡ ሳይደርስህ ፡ አይቀርም ፡፡

፫/ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጆምበሬና ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ ጋራ ፡ ተነጋግራችሁ ፡ የወሰናችሁት ፡ ከአንድ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ቁጥር ፡ የተመለከቱ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጉዳዮች ፡ የሥራ ፡ መጀመሪያ ፡ የሚ ሆኑ ፡ ናቸውና ፡ በመልካም ፡ ተደልድለዋል ፤

የእኛንም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በቶሎ ፡ መግባት ፡ የሚያፋጥን ፡ የነ ዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ፍጻሜ ፡ ማግኘት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መላክተኞችሁ ፡ የተነሳው ፡ ስምምነቱ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ገና ፡ ሥራው ፡ ሳይጀመር ፡ ስለሆነ ፡ ስለፍጻሜው ፡ ያልጻፋችሁልን ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑ ፡ ገብቶናል ፤ አሁንም ፡ በሚመለሰው ፡ አውሮፕላን ፡ የሆነውን ፡ እስከታ ስታውቁን ፡ እንጠብቃለን ፡፡ የእኛ ፡ እዚህ ፡ አለፈታዳችን ፡ መቆየት ፡ ለሕዝባችን ፡ እንደተሰማው ፡ ጉዳቱ ፡ ይሰማናል ፤ ደግሞ ፡ በአንድ ፡ወገን ፡ ከወዳጆቻችን ፡ የምንቀበለውን ፡ እርዳታ ፡ በሚበቃ ፡ አኳኋን ፡ ለማጠቃ ለል ፡ በእናንተም ፡ ወገን ፡ ስለወታደር ፡ ምልመላና ፡ ስለመግቢያው ፡ መንገድ ፡ ሥራችሁ ፡ ተፈጽሞ ፡ እስከታስታውቁን ፡ ለመጠባበቅ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ብንቸኩል ፡ ለዛሬ ፡ ሳይደርስ ፡ ቀረ ፤

ከዚህም ፡ በቀር ፡ አውሮፕላን ፡ በዚያ ፡ ለማረፍ ፡ የሚችል ፡ ከሆነ ፤ አሁን ፡ የተሞከረው ፡ ወደፊት ፡ ለማድረግ ፡ ለሚቻለው ፡ ምሳሌ ፡ ይሆ ናልና ፡ ይህም ፡ የሚመራረጥ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እርዳታውና ፡ ጓዙ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊላክና ፡ በቦታው ፡ እንዲጠብቅ ፡ ማድረግ ፡ ሊያስ ፈልግ ፡ ነው ፤ ይህንም ፡ የመሰለውን ፡ በሚመቸው ፡ ቀን ፡ እንዲመራ ፡ አሁን ፡ በአውሮፕላን ፡ከመጣው ፡ መላክተኛ ፡ ከማገር ፡ ዊንጌት ፡ ጋራ ፡ ሁላችሁም ፡ አብራችሁ ፡ ሆናችሁ ፡ ተማከሩበት ፤ ስለዚህ ፡ መላክተኛ ፡ በሚቀጥለው ፡ ቁጥር ፡ ተጽፎአል ፡፡

፬/ ማገር ፡ ዊንጌት ፡ ሚስተር ፡ ኤደን ፡ መጥተው ፡ ከተነጋገርን ፡ በኋላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚደረገውን ፡ ጦርነት ፡ ለማጣደፍ ፡ እዚህም ፡እኛ ፡ አጠገብ ፡ ሆነው ፡ ሥራችን ፡ እንዲከናወን ፡ ረዳት ፡ እንዲሆኑ ፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ፡ ሥራውንና ፡ እርዳታውን ፡ ለማጣደፍ ፡ ቁርጥ ፡ ነገር ፡ ተደርጐ ፡ ለዚሁ ፡ የሚበጀውን ፡ እዚያ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ካሉት ፡ ለመመካከር ፡በተ ለየ ፡ ተልከው ፡ መጥተዋል ፤ ስለዚህ ፡ በሚደረገው ፡ ጉባኤ ፡ አንተ ፡ ጊላ ጊዮርጊስ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ ሳትለዩ ፡ ተመካከሩ ፤ በቅርባችሁም ፡ እን ዳሉ ፡ ጊዜው ፡ ይፈቅድ ፡ እንደሆን ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻና ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በምክሩ ፡ እንዲገኙ ፡ አድርጉ ፡፡



፭/ አሁን ፡ ከጀመራችሁት ፡ ሥራ ፡ ባላገሩ ፡ ለጠላት ፡ ምግብ ፡ እንዳይሸጥ ፡ የተደረገው ፡ ክልከላ ፡ በብርቱ ፡ ኢጣልያኖችን ፡ እንደጎዳ ፡ ሰምተናል ፤ ምግብ ፡ በብርቱ ፡ መቸገራቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ዋና ፡ የጠላትን ፡ ልብ ፡ የሚሰብር ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ በሄዳችሁ ፡ ጊዜ ፡ መግባታ ችን ፡ በድንገት ፡ እንዲሆን ፡ ስለታሰበ ፡ ያለንበት ፡ ቦታ ፡ እንዳይታወቅ ፡ ምስጢር ፡ እንዲሆን ፡ ተቆርጦ ፡ አስታውቀናችሁ ፡ ነበር ፤ መቆየታችን ፡ ስለበዛ ፡ ዛሬ ፡ ያልሰማውና ፡ የማያውቀው ፡ የለም ፤ ምናልባት ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ምስጢር ፡ ሆኖ ፡ ሕዝባችንን ፡ የማጠራጠር ፡ አሳብ ፡ አብቅሎበት ፡ እንደሆነ ፡ በወሰን ፡ ላይ ፡ መድረሳችንን ፡ ገልጦ ፡ መንገር ፡ ይቻላል ፤ስለ ዚህ ፡ ለሥራው ፡ በሚጠቅመው ፡ መንገድ ፡ እንድታውሉት ፡ እንዳት ሰጉ ፡ ማስታወቃችን ፡ ነው ፤



ወይዘሮ ፡ ላቀች ፡ ደምሰው ፡፡

፮/ የበላይ ፡ ዘለቀ ፡ ደብዳቤ ፡ አዋጁ ፡ ከደረሰው ፡ በኋላ ፡ ያልተላ ከበት ፡ ጠላት ፡ አደጋ ፡ አብዝቶበት ፡ ሥራ ፡ ስለበዛበት ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ለላከው ፡ አዋጅ ፡ ምላሹ ፡ እስኪመጣለት ፡ ይሆን ፤ አሁንም ፡

የደረሰን ፡ የርሱ ፡ ደብዳቤ ፡ ቀን ፡ የሌለበት ፡ ስለሆነ ፡ የቆየ ፡ ደብዳቤ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ፤ ኢጣልያኖችም ፡ ለማባበል ፡ የላኩለትን ፡ ደብዳቤ ፡ አይተነዋል ፤ አሁንም ፡ እንደገና ፡ የተጻፈለት ፡ ደብዳቤ ፡ ተልኳልና ፡ በቶሎ ፡ እንዲደርሰው ፡ አድርጉ ።

፯/ ስለ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ ያመለከትከውን ፡ አየ ነው ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ መምጣቱን ፡ ስምተን ፡ መግሪያ ፡ ለመቀበል ፡ ከጎጃም ፡ መጥተው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ በጳጕሜ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ለርሱም ፡ ለወይዘሮ ፡ ላቀችም ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ ተልኮ ፡ ነበር ፤ በደብዳቤውም ፡ እንደተጻፈለት ፡ አሳባችን ፡ አዋጁን ፡ ይዞ ፡ አገሩ ፡ በሆነው ፡ ክፍል ፡ በወሎ ፡ ቃላችንን ፡ እንዲያሰማና ፡ ሥራ ፡ ጀምሮ ፡ እን ዲቆየን ፡ ነበር ፤ አንተም ፡ ስትሄድ ፡ ለወሎ ፡ መኳንንቶች ፡ ብዙ ፡ ስለተ ጻፈና ፡ ስለተሰጠ ፡ ይህንኑ ፡ አስተማማኝ ፡ በመሆን ፡ ይረዳል ፡ ብለን ፡ አስበን ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ የጻፈልን ፡ ደብዳቤ ፡ ደርሶናል ፤ የጻፈልንም ፡ የእኛ ፡ ሳይደርሰው ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ይልቅ ፡ ለዚህ ፡ ለተመ ረጠበት ፡ ሥራ ፡ እንዳሰብከው ፡ የሚበስ ፡ መስሎ ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ በዓንተ ፡ ወገን ፡ የሚሆነውን ፡ ድርጅት ፡ የሚያጣድፍ ፡ በመሆኑ ፡ መል ካም ፡ ነው ፡ አሳቡን ፡ ተቀብለነዋል ፤ ለርሱም ፡ ጽፈንለታልና ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ታገኘዋለህ ።

፰/ ስለ ፡ ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ ፡ ያሰብከው ፡ አሳብ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ እኛም ፡ በዚያ ፡ መኖሩን ፡ ስምተን ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈን ለት ፡ ነበርና ፡ በጥቅምት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ የጻፈልን ፡ ምላሽ ፡ ደረሰን ፤ አሁንም ፡ እንደመለከትከው ፡ ደብዳቤውን ፡ ጽፈንለታል ፤ ስለርሱ ፡ ወደፊት ፡ ስለ ሚሠራው ፡ በወሊጋ ፡ አውራጃ ፡ ለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ከዚህ ፡ ብላታ ፡ ዴሬሳንና ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በጋዴ ፡ ጦር ፡ ሲዋጋ ፡ ቆይቶ ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ገብቶ ፡ ያገኘነውን ፡ ቀኛዝማች ፡ ወልደአማኑኤል ፡ ደበላ ፡ የሚባለውን ፡ ለመላክ ፡ አስበን ፡ መዘጋጀት ፡ ተጀምሯዋል ። ቀኛዝማች ፡ ወልደ ፡ አማኑኤልንም ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ ሳያውቀው ፡ አይቀርም ፤ ወደ ፡ ወሊጋ ፡ በሮዛይሬስ ፡ በኩል ፡ ልከናቸው ፡ የነበረው ፡ የወሊጋ ፡ ልጆች ፡ መንገዱ ፡ በጠላት ፡ ስለታጠረባቸው ፡ አደጋ ፡ ደርሶባቸው ፡ ዋናው ፡ መላ ክተኛ ፡ ሞተ ፤ የተረፉት ፡ ሰባት ፡ የሚያህሉት ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ገዳሪፍ ፡ መጥ ተው ፡ ይጠባበቃሉ ፤ ስለዚህ ፡ በጎጃም ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ቢገቡና ፡ ሥራቸውንም ፡ ከደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ቢጀምሩ ፡ የሚሻል ፡ መስሎ ፡ ስለታየን ፡ አሳባችሁን ፡ አስታውቁን ።

፱/ ስለ ፡ እቶ ፡ ጊላ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስለ ፡ አሥጋኽኝ ፡ አርአያ ፡ የጻፍ ከውን ፡ ክፍል ፡ አየነው ፤ ስለዚሁ ፡ ነገር ፡ ያሳለፋችሁልን ፡ ቴሌግራም ፡ ደርሶን ፡ እንደጠየቃችሁት ፡ በዚያው ፡ እንዲቆዩ ፡ በቴሌግራም ፡ አሳልፈ



ናልና ፡ ደርሷችኋል ፤ ምርኮኞቹም ፡ በዚያው ፡ እንዲቆዩ ፡ አሳልፈንላች ኋል ፤ በደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ እጅ ፡ ስላለው ፡ ምርኮኛ ፡ ኢጣልያኖች ፡ ሲያታልሉ ፡ ዘመድ ፡ መስለው ፡ ነውና ፡ በጕን ፡ እየተላላኩ ፡ ጉዳት ፡ እንዳያመጡ ፡ በብርቱ ፡ ማስጠንቀቅ ፡ ነው ።

፲/ በየመንገዱ ፡ ፖስተኛ ፡ ለማቆም ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ከተ ረዳኸው ፡ እነዚህ ፡ የተጠየቁት ፡ ሰዎች ፡ በቶሎ ፡ እንዲመጡልህ ፡ ይደ ረጋል ፤ ምናልባት ፡ ዛሬ ፡ በአውሮፕላን ፡ ለላክንላችሁ ፡ ምላሹን ፡ ለመ ጻፍና ፡ ሌላም ፡ አዲስ ፡ ጉዳይ ፡ የምትልኩልንን ፡ ለማዘጋጀት ፡ የሚበቃ ፡ ጊዜ ፡ ብታገኙ ፡ ምላሹን ፡ እነዚሁ ፡ መላክተኞች ፡ እንዲያመጡላችሁ ፡ ይደረጋል ፤ ስንልካቸውም ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ስለመንገዳቸው ፡ አደጋ ፡ የሌለበትን ፡ ወይም ፡ አቋራጭ ፡ የሆነውን ፡ ያረጋገጣችሁት ፡ እንዳለ ፡ መሪ ፡ እንዲሆናቸው ፡ በማስታወሻ ፡ ይላክልን ፤ ዛሬ ፡ መላክተኛ ፡ ለመ ላክ ፡ በሮዛይሬስ ፡ ወይም ፡ በመተማ ፡ በኩል ፡ ይሻል ፡ እንደሆነ ፡ የሚ መረጠውን ።

፲፩/ ፍቱዊ ፡ ሐጎስ ፡ የተቀበለውን ፡ ፖስታ ፡ እርሱ ፡ ሊያደርስልን ፡ አልቻለም ። ታሞ ፡ በማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ ቆይቶ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ደህና ፡ ገብቷል ። ፖስታውን ፡ ግን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ልኮት ፡ ነው ፡ የደረሰን ፤ እርሱም ፡ ከሌሎቹ ፡ መላክተኞች ፡ ጋራ ፡ እንዲመጣ ፡ ይደረ ጋል ።

፲፪/ ስለ ፡ አውሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ የጻፋችሁት ፡ ማመልከቻ ፡ ትክ ክለኛ ፡ ነው ፤ ደብዳቤውን ፡ በጻፋችሁ ፡ ጊዜ ፡ በአየርና ፡ በውስጥ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ለመፈጸም ፡ አልተቻለም ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ እንደሰማች ሁት ፡ ቀን ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ በጠላታችን ፡ ላይ ፡ በዚያው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ ከሚያደርገው ፡ ጉዳት ፡ በቀር ፡ ሌሊት ፡ እናንተ ፡ ባላችሁበትና ፡ በዙሪያው ፡ ባለው ፡ አገር ፡ እየመጣ ፡ ስለሥራ ፡ ይህም ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ የሰጠውን ፡ አሳብና ፡ ሌላም ፡ ሕዝባችን ፡ የሚመኘው ፡ እንዳለ ፡ ጻፉልን ። እኛ ፡ ባለንበት ፡ ሥፍራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የጠላት ፡ አውሮፕላን ፡ የመጣው ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ያወም ፡ ነጠላ ፡ እየሆነ ፡ ነው ፡ ምንም ፡ ጉዳት ፡ አላደረገም ፡ ከሶስት ፡ ልጆች ፡ ሞት ፡ በቀር ፤ ያላዘወተረ በት ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኘነው ፡ ማስረጃ ፡ ቤንዚን ፡ እጅግ ፡ አንሶታል ። ከሌላም ፡ ዘንድ ፡ ለማስመጣት ፡ አየሩና ፡ ባሕሩ ፡ በእንግሊዝ ፡ መርከ ብና ፡ አውሮፕላን ፡ ስለተዘጋበት ፡ የማይቻለው ፡ ሆኑዋል ፤ ከምግብ ፡ በቀር ፡ በመግሪያም ፡ ችግር ፡ እንዳለበት ፡ እርግጥ ፡ ሆኖ ፡ ታውቋል ። ከገለባትና ፡ ከመተማ ፡ ጦርነት ፡ የተማረኩትም ፡ ኢጣልያኖች ፡ የነበ ሩበት ፡ ሥቃይ ፡ ከሚናገሩት ፡ ቃል ፡ በቀር ፡ በልብሳቸውና ፡ በሰውነታ ቸው ፡ ይታያል ። አሁንም ፡ ወደፊት ፡ የአውሮፕላን ፡ እርዳታ ፡ እየጨ መረ ፡ እንዲሄድ ፡ ተነጋግረን ፡ የሚፈጸም ፡ ሆኑዋል ።

፲፫/ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ስምምነት ፡ የሚያገኙበትን ፡ መን ገድ ፡ ማበጀት ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ ነውና ፡ እንዳሳሰብከው ፡ በትጋት ፡ ድክ ሙበት ፤ በጊዜውም ፡ ሲታሰብ ፡ ይህን ፡ የሚቀንስ ፡ የእኛ ፡ መግባትና ፡ አዝማቹን ፡ በየቦታው ፡ ማደላደል ፡ ነው ፤ ይህ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ በእኛ ፡ ቃል ፡ ከተለመደው ፡ አዝማች ፡ ቃል ፡ እንዳይወጣ ፡ እያስታወቃችሁና ፡ እየመከራችሁት ፡ እኛ ፡ ስንገባ ፡ ለሚደረገው ፡ ድልድል ፡ አገልግሎቱ ፡ እንዳይጠፋበት ፡ የሠራውን ፡ ሞያ ፡ በማስታወሻ ፡ እያገባችሁለት ፡ ማቆ የት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የተሻለ ፡ ለጊዜው ፡ አይታየንም ፤ ምኞት ፡ የሚ ፈጸመው ፡ አገርና ፡ ነፃነት ፡ ሲገኝ ፡ መሆኑን ፡ ለዚህም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ የሚመኘውን ፡ እንዲያገኝ ፡ አስቀድሞ ፡ ጠላትን ፡ ከአገር ፡ማስ ወጣት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፤ አንድነት ፡ ከመሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ኃይል ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ በልቡ ፡ እንዲያሳድር ፡ በብርቱ ፡ መስበክና ፡ የእኛ ፡ መላክተኛ ፡ በመሆንህ ፡ ባለህ ፡ ሥልጣን ፡ በማስማማትም ፡ በዳኝ ነትም ፡ መሥራት ፡ ነው ፤ የዚህም ፡ አገባቡ ፡ የጊዜውን ፡ አስፈላጊነት ፡ በመመልከት ፡ በዘዴ ፡ የሚደረግ ፡ መሆኑን ፡ አትስቱትም ፡ ምክንያቱም ፡ ባለማወቅ ፡ ለጠላት ፡ መሣሪያ ፡ እንዳይሆን ፡ ነው ፤ ይህንም ፡ አስባችሁ በት ፡ ራሳችሁ ፡ አስታውሳችሁናል ፤

፲፬/ ደጃዝማች ፡ መንገሻና ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ የሚስማሙበት ፡ ማስታወሻ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ እንኳንስ ፡ የነሱ ፡ የሌላም ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ጉዳይ ፡ የሥራው ፡ መሣሪያ ፡ ስለሆነ ፡ በተቻላችሁ ፡ ድከሙ በት ፤

፲፭/ የስሜንና ፡ የበጌምድር ፡ ወሬ ፡ እስካሁን ፡ በትክክል ፡ የደረ ሰን ፡ የለም ። አማኑኤል ፡ መንገሻ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ የበጌ ምድር ፡ አኳኋን ፡ ስለተለወጠ ፡ ሌላ ፡ ፕሮግራም ፡ ያስፈልጋል ፡ ብሎ ፡ እስካሁን ፡ ሳይገባ ፡ ቆይቶዋል ፤ እኛም ፡ ያለው ፡ በበለሳ ፡ አጠገብ ፡ መሆ ኑን ፡ ስለሰማን ፡ ከጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፡ ጋራ ፡ እንዲማከሩ ፡ ጽፈን ለታል ።

፲፮/ ወደ ፡ ሸዋ ፡ በአበበ ፡ አረጋይ ፡ በኩል ፡ የሚላላክ ፡ ሰው ፡ መላ ክተኛ ፡ የሚሆን ፡ ከዚህ ፡ እንዲላክ ፡ ተብሎ ፡ ከእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ አለ ቆች ፡ ጋራ ፡ ስለተስማማንበት ፡ መላክተኞቹ ፡ ከዚህ ፡ የሚላኩት ፡ ወደ ፡ እናንተና ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ዘንድ ፡ ደርሰው ፡ ስለመገናኛው ፡ ዝርዝር ፡ ተቀብለው ፡ የሚሄዱት ፡ እንዲመረጡ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

፲፯/ አሁን ፡ ከዚያ ፡ ከደረሳችሁ ፡ በኋላ ፡ እንዳጠናችሁት ፡ ባይና ችሁ ፡ ለማየት ፡ ወሬውን ፡ ለመስማት ፡ በቻላችሁት ፡ በኢትዮጵያ ፡ክፍል፡



ያሉ ፡ የታመኑ ፡ አርበኞች ፡ ሹማምንቶች ፡ ስም ፡ የጎጃም ፡ ጭምር ፡ ያሉ በት ፡ ሥፍራ ፤ በግምት ፡ ያላቸው ፡ ብረት ፡ ዓይነቱ ፡ ስማቸው ፡ ከአባታ ቸው ፡ ስም ፡ ጋራ ፡ ከመዝገባችሁ ፡ ተገልብጦ ፡ በቶሎ ፡ ላክልን ።

ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡



አቶ ፡ አማኑኤል ፡ መንገሻ ።

## ፪ኛ ፤ ማስታወሻ ፡ ለአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

፩/ ስለ ፡ ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ ፡ ነገር ፡ በ፩ኛ ፡ ማስታወሻ ፡ በ፳ ፡ ቁጥር ፡ ስለተጻፈው ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ ሆሮን ፡ አስለቅቀው ፡ ጠባቂ ፡ ዋና ፡ ሹም ፡ ይላኩልን ፡ ብለው ፡ ስለጠ የቁ ፡ ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ እሸቴ ፡ እንዲሄዱ ፡ በቴሌግራም ፡ ማሳለፋች ንን ፡ የምታውቀው ፡ ስለሆነ ፡ እርሱ ፡ በዚሁ ፡ ተጨርሷል፡ ማለት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ አሳብህን ፡ (ምታስታውቀን ፡ ስለብላታ ፡ ዴሬሳና ፡ ቀኛዝ ማች ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ማለፍ ፡ ነው ።

፪/ እንደሰማነው ፡ ከጎጃም ፡ መሣሪያ ፡ ለማንሳት ፡ መጥተው ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ መትረየስና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ዋና ፡ መሣሪያ ፡ ገንዘ

ብም ፡ በብዙ ፡ ታዞልን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አስቀረብን ፡ ይኸውም ፡ የሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ወሬ ፡ ይነዛሉ ፡ ማለትን ፡ ሰማን ፡ ይህ ፡ በፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ። የጐጃም ፡ መላክተኞች ፡ መጀመሪያ ፡ ሲመጡ ፡ ጠላት ፡ ሰምቶ ፡ አደጋ ፡ ስለጣለባቸው ፡ ሁለተኛ ፡ ይዘውት ፡ የነበረው ፡ ከብት ፡ ስላለቀባቸው ፤ ሶስተኛ ፡ በአደጋው ፡ ምክንያት ፡ ሰው ፡ ተመልሶ ፡ የቀሩት ፡ ጥቂት ፡ ስለሆኑ ፤ አራተኛ ፡ ሲመለሱ ፡ ጠላት ፡ በብርቱ ፡ ጉልበት ፡ አድፍጦ ፡ ጠብቆ ፡ አደጋ ፡ ይጥልባቸዋል ፡ ተብሎ ፡ ተሠግቶ ፡ እንደል ባቸው ፡ በቀላል ፡ ጭነት ፡ ለመከላከልና ፡ ለመዘዋወር ፡ እንዲችሉ ፡ ታስቦ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ዋና ፡ ጉዳይ ፡ አድርጎ ፡ ማንሳት ፡ አያስፈልግም ፤ ጊዜ ፡ ሲያ ጋጥም ፡ ግን ፡ የሐሰተኛው ፡ ወሬ ፡ እንዲቀር ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሆነው ፡ የነበረው ፡ አኳሆን ፡ እንዲገለጥልህ ፡ ነው ።

ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## የሚነገር ፡ ማስታወሻ ፡ ለአዛዥ ፡ ከበደ ።

፩/ እዚህ ፡ ከመጣን ፡ የሚቻለውንና ፡ የማይቻለውን ፡ መርምራችሁ ፡ እስክታስታውቁን ፡ በመጠበቅ ፤ የሚበቃ ፡ መሣሪያ ፡ እንግሊዞች ፡ እንዲያሰናዱልን ፡ ከመጠየቅ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ማድረግ ፡ አልተቻለም ።

፪/ በአበበ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ የላካችሁት ፡ ወረቀት ፡ ለሮዛይሬስ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሹም ፡ እንዲያስረክብ ፡ ስላዘዛችሁት ፡ አስረክቦ ፡ እርሱ ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ ገብቶ ፡ ሳለ ፡ ወረቀቱ ፡ በጣም ፡ ዘግይቶ ፡ ደረሰን ፤ ለወደፊቱ ፡ የሚመጡ ፡ መላክተኞች ፡ ለእኛ ፡ በቀጥታ ፡ እንዲያስረክቡ ፤ ቢጠይቁዋቸው ፡ እነርሱን ፡ ብቻ ፡ በፍጥነት ፡ እንዲያደርሱዋቸው ፡ እንዲጠይቁ ፡ ማስጠንቀቅ ፡ ነው ።

፫/ በአውሮፓ ፡ ጦርነት ፡ እንግሊዝ ፡ በየቀኑ ፡ እየበረታ ፡ ይሄዳል ።

፬/ ኢጣልያ ፡ ከግሪክ ፡ ጋራ ፡ ጦር ፡ ገጥማለች ፡ በየቀኑ ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ይማረኩባታል ፤ በአልባኒያ ፡ በኩል ፡ የግሪክ ፡ ወታደሮች ፡ ገብተው ፡ አገር ፡ ይዘዋል ፤ ኢጣልያ ፡ ያለውድ ፡ በግድ ፡ ከጀርመን ፡ ጋራ ፡ ሆና ፡ ጦርነት ፡ ስለገባች ፡ መውጫ ፡ ጠፍቶባት ፡ ተጨንቃለች ።

፭/ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትር ፡ ወትሮም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወዳጅ የነበሩ ፡ ሚስተር ፡ ኤደን ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ ጉዳይና ፡ በተለይም ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ለሚደረገው ፡ እርዳታ ፡ ለመመርመር ፡ ከመንግሥታቸው ፡ ታዘው ፡ መጥተው ፡ በካርቱም ፡ ተገናኙን ፤ ለኢትዮጵያ ፡ የሚሰጠው ፡ እርዳታ ፡ እንዲበረክት ፡ ነግረናቸው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሊያጣድፉ ፡ ተመልሰው ፡ ሄደዋል ።



፮/ የገለባትን ፡ ጦርነት ፡ የመተማን ፡ ማስለቀቅ ፡ የሰማችሁት ፡ ነው ፤ የእንግሊዝ ፡ አውሮፕላን ፡ በብርቱ ፡ ሥራ ፡ ኢጣልያኖችም ፡ ይህን ፡ ሲለቁ ፡ ብርቱ ፡ ጉዳት ፡ በጦርነቱ ፡ አግኝቷቸዋል ። አንድ ፡ አንዱ ፡ ባታዮን ፡ ለምሳሌ ፡ ፳፯ኛው ፡ ባታዮ ፡ የተባለው ፡ ለወሬ ፡ ነጋሪ ፡ ሳይቀር ፡ ጠፋ ።

ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## የሚጠየቅ ፡ ለአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ማስታወሻ ።

(ጥያቄ) ፡

፩/ በመስከረም ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ከጸፍክልን ፡ ደብዳቤ ፡ ወዲህ ፡ ማን ፡ ተገናኘህ ፡

፪/ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ ሆናችሁ ፡ ሥራችሁን ፡ ከጀመራችሁ ፡ በኋላ ፡ መኳንንቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ምን ፡ ይሰማዋል፤ የዛሬውስ ፡ አሳቡ ፡ ምንድር ፡ ነው ።

፫/ ደብዳቤህ ፡ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ተደረገ ።

፬/ ሕዝቡና ፡ ሹማምንት ፡ አስተዳደራቸው ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ አንተ ፡ ሥራ ፡ ከጀመርክ ፡ ወዲህ ፡ የሹም ፡ ቃል ፡ ይከበራልን ፡ ወይስ ፡ ይለግማል ።

፭/ ያወቅሃቸውና ፡ ወሬአቸው ፡ የደረሰህ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ስንት ፡ ስንት ፡ ጦር ፡ አላቸው ፡ ያሉበትስ ፡ በየት ፡ በየት ፡ ነው ።

፮/ የጎጃም ፡ የበጌምድር ፡ በአቅራቢያውም ፡ ያሉ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ስም ፡ በሙሉ ፡ ያሉበት ፡ ሥፍራና ፡ በግምት ፡ የጦራቸው ፡ ልክ ።

፯/ ከኢጣልያ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሹማምንቶች ፡ ስም ።

፰/ የእኛ ፡ መምጣት ፡ ከተሰማ ፡ ወዲህ ፡ እየከዳ ፡ መጣ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ቁጥር ፡ መሣሪያውን ፡ ይዞ ፡ የመጣ ፡ ከነመሣሪያው ፡ ቁጥር ።

፱/ ኢጣልያኖች ፡ ያሉበት ፡ ሥፍራ ፡ ከነቁጥራቸው ።

፲/ አገሩ ፡ በምግብ ፡ የተራበ ፡ ወይም ፡ የጠገበ ፡ መሆኑን ።

፲፩/ በያይነቱ ፡ ስንት ፡ መሣሪያ ፡ የሚሆን ፡ ይገኛል ፡ ጥይት ፡ ጭምር ፤

፲፪/ የበላይ ፡ ዘለቀ ፡ ወሬ ፤

፲፫/ የአበበ ፡ አረጋይ ፡ ወሬ ፤



አባኘር ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

፲፬/ አንተ ፡ ከሄድህ ፡ የተደረገውን ፡ ጦርነት ፡ በአጭሩ ፡ ላክብን ፤ ኢጣልያኖችስ ፡ በጦርነቱ ፡ በአውሮፕላን ፡ ጉድተዋችሁ ፡ እንደሆን ፤ ጋዝ ፡ እንደቀድሞው ፡ ያደርጉ ፡ እንደሆን ።

ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## የተላከ ፡ የደብዳቤ ፡ ዝርዝር ፡ ማስታወሻ ።

| | | |
|---|---|---|
| ለደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ | ፩ | ደብዳቤ ፡ |
| ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ ፡ | ፩ | » |
| ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ | ፩ | » |
| ለወይዘሮ ፡ ላቀች ፡ | ፩ | በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡አቦዬ፡ አንቦልፕ ፡ ውስጥ ፡ |
| ለልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ | ፩ | ደብዳቤ ፡ |
| ለልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ | ፩ | » |



የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ፡

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

ይድረስ ፡ ከአባኘር ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፤ በመስከረም ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ አብሮ ፡ ከተላኩት ፡ ማስታወሻዎች ፡ ጋራ ፡ በአበበ ፡ ተክለ ፡ማርያም ፡ እጅ ፡ የተላኩት ፡ በኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ደረሱን ፤ ወደዚያ ፡ የሚመጣ ፡ አውሮፕላን ፡ በአጋጣሚ ፡ ስለ ተገኘ ፡ ምላሹን ፡ በአጭሩ ፡ በማስታወሻ ፡ ጽፈን ፡ ልከንልሃል ፤ እናን ተም ፡ በአደጋው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠብቋችሁ ፡ ወደታዘዛችሁ በት ፡ ሥፍራ ፡ በደህና ፡ ደርሳችሁ ፡ ሥራ ፡ መጀመሩን ፡ በመስማታችን ፡ የተሰማን ፡ ደስታ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነው ። ሁሉ ፡ የማይሳነው ፡ አምላክ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ እንድንገናኝ ፡ እንዲፈቅድልን ፡ እንተማመና ለን ።

ኅዳር ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

ይድረስ ፡ ከአባኘር ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፤ ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ የተጻፈ ፡ ለአንተም ፡ ለመኳንንቶችም ፡ የተላኩ ። ደብዳቤዎች ፡ በመኰንን ፡ ደስታ ፡ እጅ ፡ ልከንልህ ፡ የነበረው ፤ እስካሁን ፡ ሳይደርስ ፡ አልቀረም ፤ መላክተኞቹም ፡ በመጡበት ፡ ቀን ፡ አንተ ፡ በዚያው ፡ አለመኖርህን ፡ ሰማን ። የሰዎቹ ፡ መምጣት ፡ ሁላችሁም ፡ አስቀድሞ ፡ አውቃችሁት ፡ አብራችሁ ፡ የምትጠባበቁ ፡ መስሎን ፡ ምላሹ ፡ በቶሎ ፡ እንዲደርሰን ፡ ጠብቀን ፡ ነበር ፤ አቶ ፡ መኰንን ፡ ደስታ ፡ ከያዘው ፡ ደብዳቤ ፡ በቀር ፡ በማገርር ፡ ዊንጌት ፡ እጅ ፡ በተለየ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ ልከንልህ ፡ ነበር ፡ ደርሶሀልን?

ኅዳር ፡ ፳፫ ፡ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ለአሣኸ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ።

## ማስታወሻ ።

፩/ አሁን ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የመጨረሻው ፡ አኳኋን ፡ ዝርዝሩ ፡ ገና ፡ ስላልደረሰን ፡ ማናቸውንም ፡ ልንጽፍልህ ፡ አልቻልንም ፤ ተሰብስባችሁ ፡ የወሰናችሁትን ፡ የሥራ ፡ አቅድ ፡ መልካም ፡ ሆኖ ፡ አግኝተነዋል ።



ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፡ ወልደ ፡ ሩፌ ።

ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይሌ ፡ ከግራዝማች ፡ ውብነህና ፡ ከሌሎቹም ፡ ሹማምንቶች ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራ ፡ በአርማጭሆ ፡ ልከነዋል ፤ በዚያም ፡ በደህና ፡ መድረሱን ፡ ሰምተናል ።



፪/ ስለ ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ አስቀድሞ ፡ በላክኸው ፡ ማመልከቻ ፡ እኛን ፡ የሚቀበል ፡ ዘበኛ ፡ ተመልምሎ ፡ እርሱን ፡ ዋና ፡ ለማድረግ ፡ ስለነበረ ፡ በኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ በጻፍንልህ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አሳቡን ፡ ተቀብለነው ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ በወሎ ፡ በኩል ፡ የሚሠራው ፡ የሚያመዝን ፡ በመሆኑ ፡ ደብዳቤዎቹ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ከዚህ ፡ ማስታወሻ ፡ ጋራ ፡ ተልከዋልና ፡ የተገኘውን ፡ ያህል ፡ መሣሪያ ፡ ተቀብሎ ፡ በቶሎ ፡ እንዲሄድ ፡ ብታደርግ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ለርሱም ፡ ለራሱ ፡ የተጻፈው ፡ አብሮ ፡ ይገኛል ።

፫/ ዮሐንስ ፡ ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጽሮለታል ፡ ለተባለው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለንደን ፡ በነበርን ፡ ጊዜ ፡ ስለሥራውና ፡ ስላገርም ፡ ጥቅም ፡ የሚሆን ፡ ደህና ፡ ደህና ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎልናል ፤ ወደዚህ ፡ ከመጣን ፡ ግን ፡ መላክተኛውን ፡ ይልካል ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ይመጣል ፡ ብለን ፡ ስናስብ ፡ እስካሁን ፡ ገና ፡ አልመጣም ፤ ምክንያቱንም ፡ ለማወቅ ፡ አልቻልንም ፤ ስለዚህ ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ለመሄድ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ መጥቶ ፡ እንዲነጋገር ፡ ያስፈልጋልና ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ እንዲጽፍለት ፡ እናንተም ፡ እንድትልኩለት ፡ ይሁን ፤ የደጃዝማች ፡ መንገሻን ፡ መሄድ ፡ ግን ፡ የሚያግድ ፡ ነገር ፡ የለበትም ።

፬/ የበላይ ፡ ዘለቀና ፡ የአበበ ፡ አረጋይ ፡ ወረቀት ፡ እንደተቻለ ፡ በቶሎ ፡ እንዲደርሰን ፡ ማድረግ ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ወደዚያ ፡ የሚላኩ ፡ መላክተኞች ፡ አዘጋጅተናልና ፡ እነርሱ ፡ እስኪደርሱ ፡ አትጠብቁ ፤ በበኩላችሁ ፡ ሰው ፡ ልካችሁ ፡ በቶሎ ፡ የነርሱን ፡ ሁናቴ ፡ ለማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኑዋልና ፡ የተቻላችሁን ፡ ድከሙበት ፤ ደጃዝማች ፡ መንገሻም ፡ ይረዳል ።

፭/ ለጎጃም ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ከገዳሪፍ ፡ የተነሱት ፡ ሰዎች ፡ የእደጋውን ፡ ክፍል ፡ አልፈው ፡ በደህና ፡ መድረሳቸውን ፡ ሰምተናል ፤ ሰዎቹ ፡ ጥቂት ፡ በዚያ ፡ እንዲያርፉ ፡ ማድረግ ፡ ነው ፤ ወደዚህ ፡ የሚመለሱበትን ፡ በቴሌግራም ፡ እናስታውቅሀለን ፤

፮/ ቀኛዝማች ፡ ወርቁ ፡ የቋራው ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የመጣው ፡ ጓዝ ፡ ሸኝቶ ፡ ሲመለስ ፡ አደጋ ፡ ወድቆበት ፡ መሞቱን ፡ ሰምተን ፡ አዘንን ፤ በዚያ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ጦር ፡ እንዳይፈርስ ፡ በፍጥነት ፡ አጽናኝ ፡ ቃል ፡ ልካችሁ ፡ ከአዲስ ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ አድርጉ ፤

፯/ አውሮፕላን ፡ ሳይመጣ ፡ የዘገየ ፡ እንደሆነ ፡ ዝርዝር ፡ ራፖር ፡ ጽፈህ ፡ በሁነኛ ፡ ሰው ፡ እገሥግሰህ ፡ ላክ ፤ በጠላት ፡ እጅ ፡ እንዳይወድቅ ፡ ብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ኅዳር ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## የተላከ ፡ የደብዳቤ ፡ ዝርዝር ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ስማቸው ፡ በዝርዝር ፡ ለተመለከተው ፡ መኳንንትና ፡ አገሮች ፡ ደብዳቤ ፤ ማስታወሻ ፤ ወይም ፡ አዋጅ ፡ ተልኰላቸዋል ።

| | | |
|---|---|---|
| ለአዛዥ ፡ ከበደ ፡ | ፩ | ደብዳቤ ፡ |
| ለአዛዥ ፡ ከበደ ፡ | ፩ | ማስታወሻ ፡ |
| ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ጀምበሬ | ፩ | ደብዳቤ ፡ |
| ለደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብህ ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ ገረሱ ፡ ዱኪ ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ አየለ ፡ ኃይሌ ፡ | ፩ | » |
| ለልጅ ፡ አስፋው ፡ መሸሻ ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ በላይ ፡ ንጋቱ ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ቃሲሞ ፡ | ፩ | » |
| ለቀኛዝማች ፡ ጓንጉል ፡ | ፩ | » |
| ለልጅ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ በላይ ፡ | ፩ | » |
| ለደጃዝማች ፡ አመዴ ፡ ሊበን ፡ | ፩ | » |
| ለልጅ ፡ አሊ ፡ አመዴ ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ ደጀኔ ፡ | ፩ | » |
| ለቀኛዝማች ፡ ከበደ ፡ አሊ ፡ ወሌ ፡ | ፩ | » |
| ለልጅ ፡ ሙሉጌታ ፡ ገብረ ሕይወት ፡ | ፩ | » |
| ለደጃዝማች ፡ ዮሴፍ ፡ | ፩ | » |
| ለቀኛዝማች ፡ ናደው ፡ አምዴ ፡ | ፩ | » |
| ለቀኛዝማች ፡ ይማም ፡ መሸሻ ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ መላኩ ፡ | ፩ | » |
| ለቀኛዝማች ፡ አስፋው ፡ ያዘው ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ ዘውዴ ፡ መሸሻ ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ ሣህለ ፡ ድንግል ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ ተሰማ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ | ፩ | » |
| ለፊታውራሪ ፡ ዳምጠው ፡ መሸሻ ፡ | ፩ | » |
| ለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ | ፩ | » |
| ለወሎ ፡ | ፩ | አዋጅ ፡ |
| ለራያና ፡ አዘቦ ፡ ጨርጨር ፡ | ፩ | » |



የወሎና ፡ የሸዋው ፡ በደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ አቦዬ ፡ በኩል ፡ የሚላክ ፡ ነው ። ሌላም ፡ የታመነ ፡ አቋራጭ ፡ መንገድ ፡ ቢገኝ ፡ ይታሰብበት ።

ኅዳር ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማኅተም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ደህና ፡ ነን ፤

ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ለስብከት ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ አቅራቢያ ፡ መምጣታቸውንና ፡ ወደዚህም ፡ ለመግባት ፡ ይመኛሉ ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ተገኝተዋል ፡ ብለው ፡ ኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ቃል ፡ ስለላኩብን ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ለመላላክና ፡ ለማስገባት ፡ ይፈቀድ ፡ እንደሆነ ፡ ብለው ፡ ስለጠየቁን ፤ ለኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ መላካችንና ፡ ለመነጋገርም ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ ጽፈንላቸዋል ፤ ደብዳቤውን ፡ ተመልክተው ፡ ከኰሎኔል ፡ ሳንድፎርድ ፡ ጋራ ፡ ተመካክራችሁ ፡ እንድትላላኩ ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ልከንልሀል ፤ ስለሆነ ፡ ሁለት ፡ ዋና ፡ ነገሮች ፡ አጥብቃችሁ ፡ የምትመካከሩበትና ፡ የምታስቡበት ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ መጀመሪያ ፡ ወረቀቱን ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ የሚያደርሰው ፡ ሰው ፡ በፍጹም ፡ ታማኝነቱ ፡ የተረጋገጠ ፡ ለማድረስ ፡ የሚችል ፡ እንዲሆን ፤ ሁለተኛ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ሲገቡ ፡ በዚያ ፡ ያሉት ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽና ፡ ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ቅር ፡ እንዳይላቸውና ፡ በሥራ ፡ እንዳይሰንፉ ፡ ለማስረጃ ፡ ማስጠንቀቅ ፤

ታኅሣሥ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ።

## ከጠላት ፡ ጋር ፡ ለሚገኙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሹማምንት ፡ ደብዳቤ ፡ ስለ ፡ መጻፉ ።

በጎጃም ፡ ውስጥ ፡ በደብረ ፡ ማርቆስና ፡ በሞጣ ፡ በሌላም ፡ ከተማ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ የሚገኙት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሹማምንትና ፡ መኳንንቶች ፡ ከጠላት ፡ እየተለዩ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ እንዲዞሩ ፡ በመምከርና ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይን ፡ መምጣት ፡ የምሥራች ፡ በመንገር ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፍሁላቸው ፡ ከደብዳቤዎችም ፡ ጥቂቶቹ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ልጅ ፡ እያሴው ፡ ገሠሠ ፡

እጅጉን ፡ እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ እኔ ፡ ደህና ፡ ነኝ ፤

የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ያለውድ ፡ በግድ ፡ ከመገዛት ፡ ለማዳን ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተሰደው ፡ ሲደክሙበት ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ስለደረሰ ፡ የምስራቹን ፡ ለመንገርና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ለቆየው ፡ ሕዝባቸው ፡ ምሕረት ፡ ማድረጋቸውን ፡ ለሁላችሁም ፡ ለማስረዳት ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ታዝዤ ፡ ስለመጣሁ ፡ ጐጃም ፡ መሬት ፡ ገብቻለሁና ፡ ሲሆን ፡ ሥራ ፡ ሠርተህ ፡ ሳይሆንም ፡ ራስህንና ፡ ወገኖችህን ፡ መክረህ ፡ ሰዓቱ ፡ ሳያልፍ ፡ ከጠላት ፡ ተለዩ ፡ ማንኛውንም ፡ አኳኋን ፡ አጥርቼ ፡ እንድጽፍልህ ፡ ሐሳብህ ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ በደብዳቤ ፡ ላክብኝ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ መግባት ፡ ሩቅ ፡ መስሎህ ፡ እንዳትዘነጋና ፡ በኋላ ፡ ጸጸት ፡ እንዳይሆንብህ ፡ አጥብቀህ ፡ አስብበት ፡ እውነቱን ፡ እንጂ ፡ ሐሰቱን ፡ አይደለም ፡ የጻፍኩልህ ፡ ከዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋር ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይን ፡ የአዋጅ ፡ ቃል ፡ በየዓይነቱ ፡ ልከናል ።

ጥቅምት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ለክቡር ፡ ልጅ ፡ አበረ ፡ ይማም ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሀል ፡ እኔ ፡ ቸር ፡ አምላካችን ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ፤

ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትህ ፡ ፍቅር ፡ ከጠላት ፡ ስትከራከር ፡ መቆየትህንና ፡ የነጻነት ፡ ባንዲራህን ፡ መውደድህን ፡ ብዙዎች ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ መልክተኞች ፡ መስክረውልህ ፡ እኔም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነጻነቷን ፡ ልታገኝ ፡ መቻሏንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ በቅርብ ፡ ሰዓት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ መሆናቸውን ፡ ለሕዝቡ ፡ ለመግለጽና ፡ የምሥራቹን ፡ ለመንገር ፡ ታዝዤ ፡ ስለመጣሁ ፡ ያለፈውን ፡ መልካም ፡ ሥራህን ፡ በማስታወሻ ፡ ተቀብዬው ፡ ነበርና ፡ ልገናኝህ ፡ ሳስብ ፡ ያንተ ፡ ወረቀት ፡ ደረሰኝ ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ከሚመስሉህ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ስንነጋገር ፡ አንተ ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ ነህ ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ደረሰኝ ፡ ስለዚህ ፡ እውነቱን ፡ ከአፍህ ፡ እንዳገኘው ፡ ፈልጌአለሁና ፡ የጻፍክልኝ ፡ ወረቀት ፡ እውነት ፡ ከሆነና ፡ የፊተኛው ፡ ያገር ፡ ፍቅርህ ፡ ያልጠፋ ፡ መሆኑን ፡ እንድረዳው ፡ የምንገናኝበትን ፡ ቦታ ፡ ጻፍልኝና ፡ እንነጋገር ፡ ሰዓቱ ፡ አጭር ፡ ነውና ፡ አይለፍብህ ።

ጥቅምት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡



ይድረስ ፡ ለክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ያዘው ።

እጅጉን ፡ እንደምን ፡ ሰንብተዋል ፡ ቸር ፡ ፈጣሪያችን ፡ ይመስገን ፡ እኔ ፡ ደህና ፡ ነኝ ።

የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ያለውድ ፡ በግድ ፡ ከመገዛት ፡ ለማዳን ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተሰደው ፡ ሲደክሙበት ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ስለተፈጸመላቸው ፡ የምስራቹን ፡ ለመንገርና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ ለቆየው ፡ ሕዝባቸው ፡ ምህረት ፡ ማድረጋቸውን ፡ ለሁላችሁም ፡ ለማስረዳት ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ታዝዤ ፡ ስለመጣሁ ፡ ጐጃም ፡ መሬት ፡ ገብቻለሁና ፡ ሲሆን ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ሳይሆንም ፡ ራስዎንና ፡ ወገኖችዎን ፡ መክረው ፡ ሰዓቱ ፡ ሳያልፍ ፡ ከጠላት ፡ ይለዩ ። ማንኛውንም ፡ አኳኋን ፡ አጥርቼ ፡ እንድጽፍልዎ ፡ ሃሳብዎ ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ እንዳውቀው ፡ በደብዳቤ ፡ ይላኩብኝ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ መግባት ፡ ሩቅ ፡ መስሎዎ ፡ እንዳይዘነጉና ፡ በኋላ ፡ ጸጸት ፡ እንዳይሆንብዎ ፡ አጥብቄ ፡ አሳስብዎታለሁ ። እውነቱን ፡ እንጂ ፡ ሐሰቱን ፡ አይደለም ፡ የጻፍኩልዎ ። ከዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ጋር ፡ የግርማዊ ፡ ጃንሆይን ፡ ያዋጅ ፡ ቃል ፡ በያይነቱ ፡ ልከናል ።

ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ለሌሎችም ፡ በጐጃም ፡ ለሚገኙ ፡ መኳንንቶች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ ዓይነትና ፡ እርሱንም ፡ በሚመስል ፡ አኳኋን ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፌላቸዋለሁ ። የመኳንንቶቹም ፡ ስም ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ለቀኛዝማች ፡ አድገህ ፡ ቢሰውር ፡
ቀኛዝማች ፡ እንተነህ ፡ ንጉሤ ፡
ፊታውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ እምሩ ፡
ፊታውራሪ ፡ ፍላቴ ፡
ደጃዝማች ፡ ማዘንጊያ ፡
ቀኛዝማች ፡ ገሠሠ ፡ ይልማ ፡
ፊታውራሪ ፡ ደስታ ፡ ጌታሁን ፡
ቀኛዝማች ፡ ምናሉ ፡
ቀኛዝማች ፡ ሰውነቴ ፡
ፊታውራሪ ፡ ታደሰ ፡ ረታ ፡
ቀኛዝማች ፡ እያሌው ፡ ንጉሤ ፡
ሻለቃ ፡ ምን ፡ ውዬለት ፡ ካሣ ፡
ልጅ ፡ መርሶ ፡
ቀኛዝማች ፡ ደስታ ፡ ወንዴ ፡

ልጅ ፡ አያሌው ፡ ገሠሠ ፡
ፊታውራሪ ፡ ደምሰው ፡ ይመር ፡
ፊታውራሪ ፡ በየነ ፡ ይመር ፡
ቀኛዝማች ፡ ወርቄ ፡
ፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ወልዴ ፡ ማርያም ፡
ቀኛዝማች ፡ በላይ ፡ መሸሻ ፡
ነጋድራስ ፡ አወቀ ፡ በለው ፡
ግራዝማች ፡ እንግዳ ፡ ጎሹ ፡
አዛዥ ፡ ጸጋ ፡
ልጅ ፡ ሽፈራው ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ደጃዝማች ፡ ያዘው ፡
ፊታውራሪ ፡ አየለ ፡ ያዘው ፡
ልጅ ፡ ሊበን ፡ አመዴ ፡
ልጅ ፡ ኃይሌ ፡ ሮባ ፡
ፊታውራሪ ፡ ዘውዴ ፡ መሸሻ ፡

ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ የምጽፈው ፡ ለልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የጻፍሁላቸውንና ፡ ከእርሳቸውም ፡ የተላከልኝን ፡ መልስ ፡ ነው ።

ለልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፤

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኩ ፡ ለክቡርነትዎ ፡ የሚገባ ፡ ሰላምታዬን ፡ አቅርቤ ፡ እጅ ፡ እነሳለሁ ፤ ልዑል ፡ ለጤናዎ ፡ እንደምን ፡ ሰንብተዋል ፡ ብርቱ ፡ አይደሉምን ፤ እኔ ፡ ቸር ፡ ፈጣሪያችን ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ።

በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ በኢትዮጵያውያኖች ፡ ሀብት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ተሰደው ፡ ሲደክሙበት ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ስለተፈጸመ ፡ የመጀመሪያው ፡ አዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ሆኜ ፡ ከተገኘው ፡ እርዳታ ፡ ከነረዳቶቼ ፡ ጋር ፡ ጎጃም ፡ ሀገርዎ ፡ ገብቻለሁና ፡ ቢፈቅዱ ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ካለው ፡ ምልክት ፡ እኔና ፡ እርስዎ ፡ ከምናውቀው ፡ ከታመነ ፡ ሰውዎ ፡ ጋር ፡ ቢልኩብኝ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ መነጋገር ፡ ይቻላል ። ለማንኛውም ፡ ቀኛዝማች ፡ መኰንን ፡ አበበን ፡ ቢልኩት ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል ፤ ደግሞም ፡ የሚሻለውን ፡ እርስዎ ፡ ያውቃሉ ።

ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡



ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ይድረስ ፡ ከአዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ለጤናህ ፡ እንደምን ፡ ሰንብተሃል ፤ እኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነን ፤

የላክህልንም ፡ የሰላምታ ፡ ደብዳቤህ ፡ ደረሰን ። እኛም ፡ በሥላሴ ፡ ቸርነት ፡ በኃያሉ ፡ የኢጣልያን ፡ መንግሥት ፡ ኃይልና ፡ ጉልበት ፡ በተሰደድን ፡ በ፲፮ ፡ ዘመናችን ፡ ከሞት ፡ ተርፈን ፡ ሀገራችንን ፡ ተቀብለን ፡ ሀገር ፡ ለማደላደል ፡ ሕዝብ ፡ ለማስማማት ፡ መጥተን ፡ በደህና ፡ ከከተማችን ፡ ገባን ። ስለላክህብንም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ድሬደዋ ፡ ስንወርድ ፡ ተቆራኝተኸኝ ፡ የኸድህ ፡ አንተ ፡ ነበርክ ። ሁኔታችንን ፡ ሁሉ ፡ አይተኸዋል ። ከዚያ ፡ መከራ ፡ አውጥቶ ፡ ከሞት ፡ አትርፎ ፡ ሀገሬን ፡ ሰጥቶ ፡ ለዚህ ፡ ላበቃኝ ፡ ለኃያሉ ፡ የኢጣልያን ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ውለታ ፡ ልመልስለት ። ከንግዲህ ፡ ወዲአስ ፡ ለየትኛው ፡ ዕድሜ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ የምሠራው ፤ አንተስ ፡ ፍረድ ፡ ቢሉህ ፡ ምን ፡ ትፈርዳለህ ፡ አትታዘበኝም ። ሃይማኖት ፡ ለውጡ ፡ ማተብ ፡ ፍቱ ፡ አላለ ። ሁሉንም ፡ በሃይማኖቱ ፡ አስማምቶና ፡ አጽንቶ ፡ ይገዛል ።

ጥር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ፊርማ ፡ ጸሐፊ ፡ ቀኛ ፡ ተገኝ ፡

ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በጻፉት ፡ ደብዳቤ ፡ ወደ ፡ ድሬደዋ ፡ ስንወርድ ፡ «ተቆራኝተኸኝ ፡ የሄድህ ፡ አንተ ፡ ነበርክ» ፡ ሲሉ ፡ በጠቀሱት ፡ ቃል ፡ ለእኔ ፡ ምልክት ፡ ለመስጠት ፡ እንደፈለጉ ፡ ተሰምቶኛል ፤ ምክንያቱም ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ወደ ፡ ድሬደዋ ፡ እንዲወርዱ ፡ ታዘው ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የተቆራኘኋቸው ፡ እኔ ፡ ነበርሁና ፡ የምልክቱ ፡ ቃል ፡ ትክክለኛ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ለኢጣልያ ፡ ታማኝ ፡ መሆናቸውንም ፡ በማጋነን ፡ የጻፉት ፡ ምናልባት ፡ ደብዳቤው ፡ ከኢጣልያኖች ፡ እጅ ፡ ቢወድቅ ፡ ለመከላከያ ፡ ያሉት ፡ ዘዴ ፡ ይመስላል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ምልክቱ ፡ ይላኩብኝ ፡ ብዬ ፡ ለጠየቅሁዋቸው ፡ ጥያቄ ፡ በሚገባ ፡ ስለመለሱልኝ ፡ ምናልባት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ሲያገኙ ፡ ከጠላት ፡ ተለይተው ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ለመዞርና ፡ ይቅርታ ፡ ለመለመን ፡ አስበው ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ግምት ፡ ለመውሰድ ፡ ችያለሁ ። ይኸውም ፡ ነገር ፡ ወደፊት ፡ በምዕራፍ ፡ ፳ ፡ ላይ ፡ እንደሚነበበው ፡ ሆኖ ፡ ተፈጽሟል ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የምጽፈው ፡ በኅዳርና ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜያቶች ፡ የተፈጸሙትን ፡ የሥራዎች ፡ ሁኔታ ፡ በመግለጽ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የጻፍሁትን ፡ ራፖርና ፡ ማስታወሻዎች ፡ ነው ።

ለግርማዊ ፡ ጌታዬ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዕድሜ ፡ ከጤና ፡ አስተባብሮ ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኩ ፤ ባሪያዎ ፡ የረገጡትን ፡ መሬት ፡ እስማለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤

፩ኛ/ የቤጌምድር ፡ አርበኞች ፡ መልክተኞቻቸው ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ግንኙነታቸው ፡ የማያቋርጥ ፡ ሆኖአል ፤ የእስቴና ፡ የእንዳቤት ፡ የፋርጣ ፡ የሐሙስ ፡ ወንዝ ፡ የውዶ ፡ አርበኞች ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ከላስታና ፡ ከወሎ ፡ ወደመተማ ፡ ለማለፍ ፡ ሲመጣ ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ አርበኞችዎ ፡ መልካም ፡ አድርገው ፡ ተጋደሉ ፡ ድልም ፡ አግኝተዋል ። በድሉም ፡ ላይ ፡ የሞተ ፡ ፴፮ ፡ ነጭ ፡ የተማረከ ፡ ፰ ፡ ነጭ ፡ የሃማሴኑ ፡ ወታደር ፡ ለቁጥር ፡ የበዛ ፡ ነው ፡ የሞተው ፡ ይላሉ ፤ የተማረከው ፡ ካሚዎን ፡ ሁለት ፡ ነበር ፡ የተጫነውን ፡ ዕቃ ፡ ካነሡ ፡ በኋላ ፡ አቃጠሉት ፡ ይባላል ፤ ልኩ ፡ ተጣርቶ ፡ አልታወቀም ፡ እንጂ ፡ መትረየስና ፡ ጠመንጃ ፡ ብዙ ፡ ማርከዋል ፤ ከነዚህም ፡ አርበኞች ፡ ዘንድ ፡ በጦሩ ፡ ላይ ፡ የነበረ ፡ መልክተኛ ፡ አግኝቼ ፡ ነው ፡ ይኸን ፡ ወሬ ፡ ያገኘሁት ። ወደፊት ፡ ግን ፡ አጣርተው ፡ እንዲጽፉልኝና ፡ ምርኮኞቹንም ፡ ወደኛ ፡ እንዲልኩልን ፡ ጽፌአለሁና ፡ መልሱ ፡ እንደደረሰኝ ፡ አከታትዬ ፡ እጽፋለሁ ።

፪ኛ/ ከአጋፋሪ ፡ ያረጋል ፡ ጋር ፡ ተጻጽፌ ፡ ወዶት ፡ ድረስ ፡ ልምጣ ፡ ብለው ፡ ስለጠየቁኝ ፡ እኛ ፡ አለንበት ፡ ድረስ ፡ እንዲመጡ ፡ ጽፌላቸዋለሁ ፡ በሚመጡበትም ፡ ጊዜ ፡ ከቤጌምድር ፡ አርበኞች ፡ እየተገናኙ ፡ የማያቋርጥ ፡ መገናኛ ፡ እንዲአበጁ ፡ አጠንክሬ ፡ ጽፌላቸዋለሁ ፤ ይኸንንም ፡ ያደርጋሉ ፡ ስል ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።

፫ኛ/ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ እንደጻፉልኝ ፡ ጎጃምና ፡ ሸዋን ፡ ለማገናኘት ፡ መዘጋጀታቸውን ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ የራስ ፡ ኃይሉ ፡ መምጣትና ፡ ስለደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ከጠላት ፡ የተጻፈው ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ አቀዝቅዟቸው ፡ ነበር ።

ነገሩ ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ ካረጋገጥንላቸው ፡ በኋላ ፡ ወደፊተኛው ፡ ፕላናቸው ፡ መመለሳቸውን ፡ ጽፈውልኝ ፡ መልካም ፡ ሥራቸውን ፡ አያቋርጡም ፡ ስል ፡ ተስፋ ፡ አድርጌአለሁ ።



፬ኛ/ የጎጃም ፡ ሕዝብና ፡ የሹማምንቱም ፡ ሃሳብ ፡ ባላገሩ ፡ መማሪያ ፡ እንዲይዝ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በሃሳብ ፡ ስሉተለያየን ፡ ነው ፡ የሚመጣውን ፡ ዕቃ ፡ ማንሳት ፡ ችግር ፡ የሆነበት ፤ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ እኛ ፡ በቀጥታ ፡ ለመሥራት ፡ አስበን ፡ ወታደር ፡ መቅጠር ፡ አጋሰስም ፡ መግዛት ፡ ጀምረን ፡ መሥራት ፡ ይዘናል ፤ ለጊዜው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ቴሌግራም ፡ እንደደረሰን ፡ ከደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ያለዋጋ ፡ ፲፯ ፡ አጋሰስ ፡ አገኘን ፡ ከደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ በዋጋችን ፡ ፫ ፡ አጋሰስ ፡ አገኘን ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ በኪራይም ፡ ከሌላም ፡ ቦታ ፡ ፈልገን ፡ ፴፮ ፡ ያህል ፡ አጋሰስ ፡ ጭምር ፡ ፪፻፴፪ ፡ አጋሰስ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጓዝ ፡ ለማስነሳት ፡ ሰደናል ፡ ይኸንንም ጓዝ ፡ ሊአመጣ ፡ የሄደ ፡ ልጅ ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ ነው ፤

፭ኛ/ በጥር ፡ ፳ ቀን ፡ ልጅ ፡ ማሞ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡ ፲፪ ፡ ሺህ ፡ ጦር ፡ በደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ ሌሊት ፡ ሲገሠግስ ፡ አድሮ ፡ ሲነጋ ፡ ዘብ ፡ ከሚጠብቁ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ጋር ፡ ተታኰሰ ። ወዲያው ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትተው ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ገጥመው ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ እያባረሩ ፡ እቡሬ ፡ ምሽግ ፡ ገብቶ ፡ አመለጣቸው ። ከጠላት ፡ ወገን ፡ የተደረገውን ፡ ጉዳት ፡ ለማወቅ ፡ መርማሪ ፡ ልከናል ፤ ሲጣራ ፡ እጽፋለሁ ። ከእኛም ፡ ወገን ፡ የሆነው ፡ እንደዚሁ ፤

፮ኛ/ የራስ ኃይሉም ፡ ስብከት ፡ እንደመጡ ፡ በጣም ፡ ገና ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ እየቀዘቀዘ ፡ ስለሄደ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ልጅ ፡ ኃይሉ ፡ በለው ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ሊወጓቸው ፡ አዘጋጅተው ፡ ይጠብቋቸዋል ። እራስ ፡ ኃይሉም ፡ ሊወጓቸው ፡ መዘጋጀታቸውን ፡ ስለሰሙ ፡ ያደርጉትን ፡ አጥተው ፡ ማርቆስ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ በሃሳብ ፡ ይናውዛሉ ፤ በመጨረሻ ፡ ምን ፡ እንደሚያደርጉ ፡ እንጠባበቃለን ። ጠላት ፡ በሚአደርገው ፡ ፖለቲካ ፡ ሁሉ ፡ አገሬው ፡ በሙሉ ፡ ማታለል ፡ መሆኑ ፡ ገብቶት ፡ አይቀበለውም ፤ በየሀገሩም ፡ ላይ ፡ የሚጥለውን ፡ የስብከት ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ልኬአለሁ ፤

፯ኛ/ ይኸንን ፡ ደብዳቤ ፡ ስጽፍ ፡ ከበጌምድሮች ፡ የደረሰኝን ፡ ደብዳቤ ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ልኬአለሁ ፤

፰ኛ/ ወደፊት ፡ አጣራለሁ ፡ ብዬ ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ የጻፍኩት ፡ የቡሬ ፡ ወሬ ፡ ስለደረሰኝ ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ ልኬአለሁ ፤

፱ኛ/ ግርማዊነትዎ ፡ በሚመጡበት ፡ ጊዜ ፡ ከወር ፡ በፊት ፡ እንዳውቀውና ፡ ማንኛውንም ፡ ሃሳብ ፡ አቋሚ ፡ እንድጠባበቅ ፡ በድንገት ፡ እንዳይሆንብን ፤ ይኸንንም ፡ ማለቴ ፡ ለመዘጋጀት ፡ ቦታ ፡ ስለአላገኘንና ፡ ስለ አልወሰን ፡ ነው ፤

፲ኛ/ ወደሸዋ ፡ አርበኞች ፡ የሚላከው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲላክልኝ ፡ ብዬ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አስታውሼ ፡ እስካሁን ፡ ሳይደርሰኝ ፡ በመቅረቱ ፡ ምቹ ፡ ጊዜአችንን ፡ አስተላለፍነው ። አሁንም ፡ መልክተኛ ፡ አዘጋጅቼ ፡ እጠባበቃለሁና ፡ ጊዜው ፡ ሳያልፍ ፡ በአየር ፡ መንገድ እንዲ ላክልን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አመለክታለሁ ።

ጥር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ያለሐኬት ፡ ባሪያዎ ፡
ከበደ ፡ ተሰማ ፡

ማመልከቻ ፡

፩ ፡ ለግርማዊ ፡ ከኔ ፡ የተጻፈ ፡ ፫ ፡ ገጽ ፡ ከ፴፩ ፡ እስከ ፡ ፴፪ ፡ ቁጥር ፡
፩ ፡ የቡሬን ፡ ጦር ፡ አወጣጥና ፡ ድል ፡ የሚአመለክት ፡ ከሰው ፡ የደረሰኝ ፡
፩ ፡ የጃንሆይ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ጠላት ፡ ለፕሮፓጋንዳ ፡ የጣለው ፡
፩ ፡ ከቤጌምድር ፡ አርበኛ ፡ ለግርማዊ ፡ የተላከ ፡ በ፫ ፡ ገጽ ፡ የተጻፈ ፡
፩ ፡ ከሸዋ ፡ አርበኞች ፡ ለግርማዊ ፡ የተላከ ፡
፩ ፡ ከጠላት ፡ በጃንሆይ ፡ ማኅተም ፡ አስመስሎ ፡ ለጎጃም ፡ ሕዝብ ፡ የወ ደቀ ፡ አዋጅ ፡
፩ ፡ ከጠላት ፡ ለሸዋ ፡ ሕዝብ ፡ የወደቀ ፡ አዋጅ ፡ በጃንሆይ ፡ ስም ፡
፩ ፡ ማርቆስ ፡ ላይ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ የዋሹት ፡ የስብከት ፡ ቃል ፡ ከሰው ፡ የደረሰን ፡
፩ ፡ ልጅ ፡ በላይ ፡ ዘለቀ ፡ ከራስ ፡ ኃይሉ ፡ የተጻጻፈው ፡ ረቂቅ ፡ ግልባጭ ፡ የላከልን ፡
፩ ፡ ዲማ ፡ ላይ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ በስምምነት ፡ የቆመ ፡ ማኅ በር ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ የሚሠራ ፡ ስለራስ ፡ ኃይሉ ፡ ታሪክ ፡ የጻፈልኝ ፡ በማተሚያ ፡ ታትሞ ፡ እንዲወጣ ፡ ሲል ፡
፩ ፡ የልጅ ፡ ደምሴ ፡ ዓለማየሁ ፡ ወረቀት ፡ ጎጃም ፡ ክፍል ፡ ቢቡኝን ፡ የሚገባ ፡

ከበደ ፡ ተሰማ ፡

የተላኩ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ዝርዝር ፡

ከኔ ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተጻፈ ፡ ማመልከቻ ፡
ከጥንታዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጀግኖች ፡ ማኅበር ፡ የተጻፈ ፡ ማመልከቻ ፡
ከዚሁ ፡ ማኅበር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ወደኔ ፡ የተላከ ፡



ከነደጃዝማች ፡ አውራሪስ ፡ የተጻፈ ፡
ከበጅሮንድ ፡ ለጥይበሉ ፡ የተጻፈ ፡
ከፊታውራሪ ፡ ዳምጠው ፡ መሸሻ ፡ የተጻፈ ፡
ከባሻ ፡ ከፍ ፡ አለ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ ከመንዝ ፡ የተጻፈ ፡
ከባሻ ፡ ገሊታና ፡ ከባላምባራስ ፡ ሃብተ ፡ ማርያም ፡ ከመራ ፡ ቤቴ ፡ የተጻፈ ፡
ከግራዝማች ፡ ተሾመ ፡ ሸንቁጥና ፡ ከልጅ ፡ አበበ ፡ ሸንቁጥ ፡ የተጻፈ ፡
ከፊታውራሪ ፡ ጓንጉል ፡ የተጻፈ ፡
ከጌታ ፡ ሸረፍ ፡ አፈንዲ ፡ ከደራ ፡ የተጻፈ ፡
ከባላምባራስ ፡ ሃብተ ፡ ማርያም ፡ የተጻፈ ፡ ግጥም ፡
የባንዳ ፡ ቁጥር ፡ የተጻፈ ፡ የርሳስ ፡ ጽሕፈት ፡ አበበ ፡ ሸንቁጥ ፡ ከላምዋሻ ፡
የዳምጠው ፡ መሸሻና ፡ የአበበ ፡ አውራሪስ ፡ አገር ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡
የመንግሥቴ ፡ ሸህአምጥ ፡ ከመርሃ ፡ ቤቴ ፡ ከደራ ፡ የተጻፈ ፡ ፩ ።
እኔ ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ የጻፍኩት ፡ ረቂቅ ፡
የራስ ፡ ኃይሉ ፡ ደብዳቤ ፡ መልስ ፡
የደጃዝማች ፡ ይመር ፡ ጎሹ ፡ ደብዳቤ ፡ ከበጌምድር ፡

## ደብዳቤ ፡ እንዲጻፍላቸው ፡ የጠየቅሁት ።

፩ኛ/ ለፊታውራሪ ፡ ዘውዱ ፡ አባኮራን ፡
፪ኛ/ ለደጃዝማች ፡ አውራሪስ ፡
፫ኛ/ ለበጅሮንድ ፡ ለጢበሉ ፡
፬ኛ/ ለባሻ ፡ ገሊታ ፡
፭ኛ/ ለልጅ ፡ አበበ ፡ ሸንቁጥ ፡
፮ኛ/ ለግራዝማች ፡ ተሾመ ፡ ሸንቁጥ ፡
፯ኛ/ ለባላምባራስ ፡ ሃብተማርያም ፡
፰ኛ/ ለጥንታዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጀግኖች ፡ ማኅበር ፡
፱ኛ/ ጎጃም ፡ ዲማ ፡ ለማኅበሩ ፡
፲ኛ/ ለደብረ ፡ ወርቅ ፡ ለማኅበሩ ፡
፲፩ኛ/ ዲማ ፡ ላይ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ በስምምነት ፡ ለቆመው ፡ ማኅበር ፤

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከጠላት ፡ የተለዩ ፡ ናቸውና ፡ በቶሎ ፡ ተጽፎ ፡ ይላክ ልኝና ፡ እንዲደርሳቸው ፡ እንዳደርግ ።

ከበደ ፡ ተሰማ ።